በትህትና የተሞላ አገልጋይ "ይህን ሠርቷል" ወይም "ይህን ሠርቻለሁ" ብሎ በማወጅ አይታበይም፤ የእግዚአብሔርንም ክብር አይሻማም። ምስጋና ሲቀርብለት፥ ምስጋናውን ቶሎ ወደሚመለከተው ጌታ ያስተላልፋል። በትህትና የተሞላ አገልጋይ፥ ሌሎች ሲመሰገኑ፥ ሌሎች ሲታወቁ ደስ ይለዋል እንጂ ይህን ያህል አይቆረቆረውም። ሌሎችን ማመስገንና ማደንቅ አይከብደውም።

## ምዕራፍ ፲

# የፍቅር አገልግሎት

*"ልጆቼ ሆይ! ፍቅራችን እውነተኛና በሥራ የሚገለጥ ይሁን እንጂ*
*በቃል ወይም በንግግር ብቻ አይሁን።"*
*(1 ዮሐ. 3፥18)*

በጣም የታወቁት ስኮትላንዳዊው ሰባኪ፣ *አንድሪው ቦናር፣* አንድ ቀን ከአንድ ትልቅ ስብሰባ ላይ ተገኝተው በዘመኑ ተደናቂ የነበሩትን ታላቅ ሰባኪ ስብከት ካዳመጡ በኋላ፣ ሰባኪው ስብከታቸውን ጨርሰው ከመድረክ ሲወርዱ ጠጋ ብለው፥ *"መስበክ ትወዳለህ! አይደለም?"* ብለው ጠየቋቸው። እኛም ታዋቂ ሰባኪ *"አዎን! መስበክ በጣም እወዳለሁ"* የሚል መልስ ሰጧቸው። *አንድሪው ቦናርም* በመቀጠል፣ *"የምትሰብክላቸውንስ ሰዎች ለመሆኑ ትወዳቸዋለህ?"* ብለው ጠየቋቸው። *የአንድሪው ቦናር* ጥያቄ ይህን ያህል ከመስመር የወጣ ጥያቄ አልነበረም። በመሪነት ደረጃ ላይ ሆነው ማገልገል የሚወዱ፣ የሚያገለግሉትን ሕዝብ ግን እንደሚገባው የማይወዱ ብዙ አገልጋዮች አሉ። እረኛው በጎቹን ከመውደዱ በፊት የበጎቹን ባለቤት መውደድ እንዳለበት ግልጽ ነው። የበጎቹን ባለቤት ሳይወድ በጎቹን መውደድ አስቸጋሪ ይሆንበታል። ስለዚህ ነው ኢየሱስ ለበጎቹ እረኛ እንዲሆን ሲያስ ማራው የጠራውን ጴጥሮስ "በጎቼን ትወዳቸዋለህን?" ብሎ በመጠየቅ ፈንታ "ትወደኛለህ?"

በማለት ከአንዴም ሦስቴ ደጋግሞ የጠየቀው (ዮሐ. 21፥15-17)። በ1757 ዓ.ም. (እ.አ.አ.) "አሜዚንግ ግሬስ" (Amazing Grace) የሚለውን የታወቀውን የእንግሊዝኛ መዝሙር የጻፈው ጆን ኒውተን፣ ለታወቁት ወንጌላዊ ለጆርጅ ኋይትፊልድ አንድ ጊዜ ከዚህ በታች ያቀረብነውን ቃል ጻፉላቸው፦

*"ብዕድሜዬ እየገፋሁ ስመጣ፣ ግጭታችን ምን ያህል የክርስትና መንፈስ የጎደለው ና ከንቱ እንደሆነ፣ እንዲሁም በእምነታችን ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነገር እየገደለው እንደሆነ እየታየኝ መጣ። የራሴን ችሎ ብዬ፣ ማስተካከል ይኖርብኝ ይሆናል ብዬ በማሰብ የሌላውን ሰው የወይን እርሻ ለማስተካከል ለሞከርኩት ትዕግሥቴን እንዳጣሁ፣ ምን ያህል ጊዜዬን እንዳባከንኩ ሳስብ ውስጤ ያዝናል። ጌታ ኢየሱስ ከክህደቱ በኋላ የተመለሰውን ጴጥሮስ "...ማስተዋልህ ጨምሯል?... ከስህተትህ ተምረሃል?..ጥበበኛ ሆነሃል? ጤናማ አስተሳሰብ አለህ? የእምነት አቋምህ ትክክል ነው? ብሎ አልጠየቀውም። ነገር ግን ጌታ የጠየቀው፣ 'ትወደኛለህ?' የሚል ነው። በዚያን ወቅት ጴጥሮስ የሰጠው መልስ በቂ ነበር። ያ መልስ ዛሬስ ለእኛ በቂ የማይሆነው ለምንድነው?"*[21]

ማንኛውም የጌታ አገልጋይ ለማገልገል የተነሳበት ዓላማ ወይም ምክንያት ትክክል ካልሆነ፣ እንደሚገባው ማገልገል አይችልም። ለማገልገል የተነሳበት ምክንያት ዝና፣ ክብር፣ ገንዘብ፣ ሥልጣን ወዘተ. ከሆነ፣ በመንገዱ አንዳንድ ፈታኝ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥሙት፣ ሁሉን ታግሶ እስከ መጨረሻው በመዝለቅ እግዚአብሔርን የሚያከብርና የሚያስከብር አገልግሎት መስጠት አይችልም። በአገልግሎቱ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለመወጣት ጉልበት ሊሆነው የሚችለው ሌላ ነገር ሳይሆን የክርስቶስ ፍቅር ብቻ ነው። ጳውሎስ ክርስቶስን ለማገልገል የተነሳበትን ምክንያት ሲገልጽ፣ ***"የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል"*** ይላል (2 ቆሮ. 5፥14)። ዳዊት የግል ድካም ቢኖርበትም፣ ለእስራኤል ሕዝብና እንዲሁም ለጌታው ልዩ የሆነ ፍቅር የነበረው ሰው ነበር። የእውነተኛ እረኛ ልብ የነበረው ንጉሥ ዳዊት፣ በእርሱ ኃጢአት ምክንያት ሕዝቡ ላይ የደረሰውን ታላቅ መቅሰፍት በማሰብ፣ ***"እነሆ ኃጢአት የሠራሁትም የተገነጠልሁትም እኔ ነኝ፤ እነዚህ ግን በጎች ናቸው፤ ምን አጠፉ? እጅህ በእኔና በአባቴ ቤት ላይ ትሁን"*** (2 ሳሙ. 24፥17) በማለት ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። የእውነተኛ እረኛ ልብ ያለው እውነተኛ መሪ፣ ሕዝቡን በጣም ስለሚወድ፣ የሚመራቸው ሕዝቦች መከራ ሲደርስባቸው፣ በመከራ ውስጥ ሲያልፉ ሳይቆረቆረው ዝም ብሎ ማለፍ አይችልም። በአገራችን፣ ***"ሰውን ውደደው እንጂ፣ አትመነው"*** የሚል አባባል አለ። ይሄን ዓይነቱ የአገራችን አባባል ትክክል ነው ወይ? የወደድነውን እንዴት አናምነውም? የአመንነውንስ እንዴት አንወደውም? አንዳንድ ጊዜ እውነት ሳይሆን እንደ እውነት የተቀበልናቸው ነገሮች አሉ። ከብዙዎቹ

[21] John Newton, Voice of the Heart (Chicago: Moody Press, 1980.)



መካከል አንደኛው ይሄ ከላይ የጠቀስነው አባባል ነው። ከዚህኛው ደግሞ ላይ ለየት ያለ አባባል አለ። ይኸውም፣ *"እንዴት ልውደድ?" – "እመን!" –"እንዴት ልመን?" – "ውደድ"።* የሚል ነው። በዚህ ዓይነት አነጋገር "ውደድ!" የሚል ትዕዛዝ ስንሰማ፣ *"እንዴት ልውደድ?"* ብለን መጠየቃችን አይቀርም። የምናገኘው መልስ፣ *"እመን"* የሚለውን ነው። መልሰን *"እንዴት ልመን?"* ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው መልስ፣ *"ውደድ"* የሚል ነው። በዚህ ዓይነት አባባል፣ *"ለመውደድ"* ማመን፣ *"ለማመን"* ደግሞ *"መውደድ"* እንዳለብን እንረዳለን። ይሄኛው አባባል ከላይኛው የተሻለና እውነትነት ያለው ነው። *የወደድነውን እናምነዋለን፤ ያመንነውን እንወዳለን።*

*ጀረሚ ቴይለር የተባለ ጸሐፊ፤*

*"እግዚአብሔር ራሱ ፍቅር ስለሆነ ሊሰጠን የሚችለው ትልቅ ስጦታ ቢኖር፣ 'ፍቅር' ነው፤ እኛም ለእግዚአብሔር ልንሰጠው የምንችለው 'ፍቅርን' ነው። ሐዋርያት ፍቅርን 'የፍጹምነት ማሠሪያ' ብለው ይጠሩታል፤ እርግጠውም፣ አዲሱም፣ ትልቁም ትዕዛዝ ይሄ ነው፤ ይህንን የሚፈጽም ሕግን ሁሉ ይፈጽማል" አለ።*

*ኳርለስ የተባለው ጸሀፊ ደግሞ፤*

*"ኃጢአትህን ሳትወድ፣ 'እግዚአብሔርን እወዳለሁ' ማለትህ ዋጋ የለውም (ከንቱ ነው)፤ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር፣ ኃጢአታችንን ማፍቀርን ይወልዳል፤ ኃጢአታችንን ማፍቀር ደግሞ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ያረስርሳል (ያለመልማል)"* አለ።

በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ዓለም 'በመሪውና በተመሪው፣ በአገልጋዩና በተገልጋዩ' መካከል መተማመን ሲጠፋ፣ መሪው ለመምራት፣ ተመሪውም ለመመራት አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። ማንኛውም ዓይነት ድርጅትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ሆኖ ለማደግ፣ በሁለቱ መካከል መተማመን ያስፈልጋል። ተመሪው የሚወድደውን ሰው መከተል አስቸጋሪ ስለማይሆንበት፣ መሪው ተከታይ እንዲኖረው የፍቅር ሰው መሆን አለበት። ያለፍቅር መምራት የሚሞክሩትን መንፈሳዊ መሪዎች፣ ምዕመናኑ አምነው መከተል አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። ይህንን እውነት ባለመረዳት፣ አንዳንድ መሪዎች ተከታይ ሲያጡ፣ "ዝናቸውን... ሀብቱ... ወይም ሥልጣናቸውን በማሳየት..." ለመምራት ሲሞክሩ ይታያሉ። መስመር የለቀቀውን አቋማቸውን በማስተካከል ፈንታ፣ ኮንፍራንስ አዘጋጅተው፣ የውጪ ሰባኪ አስመጥተው፣ "አገልጋዮቻችሁን አክብሩ... መሪዎቻችሁን ተከተሉ... በተቀባው ላይ እጃችሁን አታንሱ..." ብለው ሕዝቡን እንዲገሰጹላቸው፣ ወይም እንዲመክሩላቸው ይፈልጋሉ። ይሄ በጊዜው በውቅቱ ያለባቸውን ውጥረት ሊያቃልልላቸው ይችል ይሆናል። ነገር ግን በሳቢ የሆነ መፍትሄ ሊሰጥላቸው አይችልም። የሚያስፈልጋቸው ነገር ቢኖር፣ "ሥር ነቀል ለውጥ" ነው። ያም ሌላውን መለወጥ ስላማይችሉ፣ ራሳቸውን መለወጥ አለባቸው። ራሳቸውን የሚለውጡትም፣ ከሁሉም የበለጠ "የፍቅር ሰው"

በመሆን ነው። "እንዴት የፍቅር ሰው ልሁን?" ለሚለው ጥያቄያችን ምሁራን የሚሰጡን መልስ፣ "ተወዳጅ ለመሆን፣ 'መውደድ' ነው" ይሉናል። መንፈሳዊ መሪው "ሳይወዱኝ፣ እንዴት እወዳለሁ?" ብሎ መጠየቁ አይቀርም። ሄር የተባለ ጸሀፊ ባጸፈው ጽሁፍ ለዚህ ጥሩ መልስ የሚሆነንን ሰጥቶናል፥

> "ፍቅር የሚፈሰው ወደታች ነው' ይባላል። ወላጆች ለልጆቻቸው ያላቸው ፍቅር፣ ልጆች ለወላጆቻቸው ካላቸው ፍቅር የበለጠ ኃይለኛ ነው፤ከእግዚአብሔር ልጆች ውስጥ፣ እግዚአብሔር ለልጆቹ ካለየው ፍቅር የበለጠ፣ ፍቅሩን ለእግዚአብሔር መግለጽ (ማሳየት) የቻለ ማን ነው?" ይላል።

መንፈሳዊ መሪ፣ የእባት ልብ እንዲኖረው ያስፈልጋል። "የወንድ ልብ እንደ ድንጋይ የጠጠረ ቢሆንም፣ የአባት ፍቅር ግን ለሰላሳ ነው" ስለሚባል፣ መንፈሳዊ መሪ ለመንፈሳዊ ልጆቹ የአባት ልብ እንዲኖረው ያስፈልጋል። አባት የሆነውን እግዚእብሔር የምንወደው፣ እርሱ አስቀድሞ ስለወደደን ብቻ ነው። ስለዚህ፣ መንፈሳዊ መሪም 'ሳይወዱኝ አልወድም' ከማለት፣ እንደ እግዚእብሔር አብ አስቀድሞ የሚያገለግላቸውን መንፈሳዊ ልጆቹን መውደድ አለበት።

## 1. መንፈሳዊ መሪ፥ ለአገልግሎቱ መሳካት ያለው "ፍቅር" ወሳኝነት አለው

ጴጥሮስና የተቀሩት ደቀ መዛሙርት፣ ፈታኝ የሆነ ነገር ሲያጋጥማቸው፣ ቀደም ሲል ከክርስቶስ የተቀበሉትን የወንጌል አደራ ጥለው ወደ ዓሣ ማጥመድ ሥራቸው የተመለሱበት ጊዜ ነበር። ያም ሆኖ የዓሣ ማጥመድ ሥራው የተሳካ አልሆነላቸውም። በዚያ ሁኔታ እያሉ ኢየሱስ በሥፍራው በመገኘት፣ መረባቸው እስኪቀደድ ድረስ ብዙ ዓሣዎችን መያዝ አስቻላቸው። ከጠመዱት ዓሣ "በልተው ከበቁ በኋላ" ጴጥሮስንና ደቀ መዛሙርቱን ወደ ታላቁ የወንጌል ተልእኮ ከማስማራቱ በፊት ክርስቶስ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ ደጋግሞ "...የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ! እነዚህ ከሚወድዱኝ ይበልጥ ትወደኛለህን?" ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስ ጴጥሮስን የጠየቀው ጥያቄ አስፈላጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ውስጥ ዘልቆ የሚገባ፥ ዛሬም ቢሆን መንፈሳዊ መሪ የሆነ ሁሉ መጠየቅ ያለበት አስፈላጊ ጥያቄ ነው። የበጎቹ ባለቤት የሆነውን ጌታ ሳይወድ፣ በጎቹን መውደድ የሚችል እረኛ የለም። ለበጎቹ የሚኖረው ፍቅር ደግሞ የሚጀምረው፣ ስለ በጎቹ ሲል የሞተውን ዋናውን የበጎቹን እረኛ (ባለቤት) በመውደድ ነው (የዮሐ. 10፥11)። መንፈሳዊ መሪ ወደ አገልግሎት የመጣው ምስጋና፥ ገንዘብ፥ ሥልጣንና ታዋቂነትን ለማግኘት ብቻ ከሆነ፥ ለማገልገል የተነሳበት ዓላማ ትክክል ስላልሆነ፥ በአገልግሎቱ ውስጥ እንዳንድ ውጣ ውረድ ሲደርስበት፥ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት፣ ጸንቶ በመቆም ፈንታ በጎቹን



ሜዳ ላይ በትኖ እንደሚሄድ፣ አገልግሎቱን ትቶ እንደሚወጣ የታወቀ ነው። ለበጎቹና ለበጎቹ ባለቤት ፍቅር የሌለው አገልጋይ በአገልግሎቱ ላይ ለረጅም ጊዜ የቆየ ቢሆንም፣ እንዲሁም ምንም ያህል ብርቱና ታታሪ አገልጋይ ቢመስልም፣ የሚሰጠው አገልግሎት እግዚአብሔርን የሚያከብርና የሚያስከብር ሊሆን አይችልም። መንፈሳዊ መሪ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትክክል መምራት የሚችለው፣ መጀመሪያ ለሕዝቡ ሲል ራሱን ለሞት አሳልፎ ለሰጠው ጌታ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛና ተለዋዋጭ ያልሆነ ፍቅር ሲኖረው ብቻ ነው።

እኔና እናንተ የሚወደድ ነገር ባይኖረንም፣ አስቀድሞ የወደደንን ጌታ እንወደዋለን? ልባችን በእርሱ ፍቅር የተሞላ ከሆነ፣ ራሱን እስከ መስጠት ድረስ የወደዳቸውን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች የሚወድ ልብ ይኖረናል። መንፈሳዊ መሪ በልቡ ያለውን፣ ከክርስቶስ የተቀበለውን ፍቅር እርሱ ለሚወዳቸውና ሕይወቱን ለሰጣቸው ልጆቹ ማካፈል ይገባዋል። ፍቅሩም በቃላት ብቻ ሳይሆን፣ በእውነትና በተግባር የሚገለጽ መሆን አለበት። የክርስቶስ ፍቅር ልባችንን ከሞላው፣ ሙሉ በሙሉ ለአገልግሎት የተሰጠን እንሆናለን። በጌታ አገልግሎት ውስጥ የተሰማራን አገልጋዮች ሁሉ፣ "የማገለግለውን ሕዝብ በእውነት እወደዋለሁ ወይ?" ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። መሪ መሆን ይቻላል፤ ያለፍቅር ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ፣ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው መምራት አይቻልም። በጎቹን የሚወድ እረኛ በቅድሚያ የበጎቹ ባለቤት የሆነውን ጌታ መውደድ አለበት። ፍቅር የሌለበት አገልግሎት፣ አገልጋዩ ምንም ያህል ብርቱ ቢሆን አጥጋቢ የሆነ ውጤት እንደማያገኝ ቀደም ሲል ገልጸናል። ለዚህ ነው ወደ ታላቁ የወንጌል ተልእኮ ከማሰማራቱ በፊት ክርስቶስ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ ደጋግሞ "...የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ! እነዚህ ከሚወድዱኝ ይበልጥ ትወደኛለህን?" ብሎ የጠየቀው። ጴጥሮስም ቀደም ሲል የነበረውን የራሱን ትምክህተኛነት ጥሎ በትህትና፣ "... አዎ ጌታ ሆይ! እኔ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ ሲል መለሰለት።" በእርግጥ ጌታውን እንደሚወድ ጴጥሮስ በሰጠው አገልግሎቱና በኖረው ሕይወቱ አስመስክሯል። ሰው ማየት የማይችለውን የሰው ውስጣዊ ሕይወት ማየት የሚችለው ጌታ፣ ጴጥሮስ ራሱን መስዋዕት አድርጎ እስከ መስጠት ድረስ የሚወደው መሆኑን ስላወቀ ነው፣ "... ግልገሎቼን መግብ ...ጠቦቶቼን ጠብቅ... በጎቼን አሰማራ" በማለት አደራ ያለው (የዮሐ. 21፥15-17)።

ኢየሱስ ጴጥሮስን የጠየቀው ጥያቄ እንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን "...ትወደኛለህ/ትወጂኛለሽ..." ብለው እንደሚጠይቁት ዓይነት ተራ ጥያቄ ሳይሆን፣ አስፈላጊና ወደ ውስጥ ሠርጎ በመግባት የጴጥሮስን ልብ እውነተኛነት የሚመረምር ነበር። የበጎች እረኛ፣ የበጎቹን ባለቤት ሳይወድ በጎቹን ብቻ መውደድ እንደማይችለው ሁሉ፣ መንፈሳዊ መሪም፣ እውነተኛ እረኛ የሆነውን ክርስቶስን ሳይወድ፣ ክርስቶስ የሞተላቸውን ልጆቹን መውደድ አይችልም። የበጎቹ ባለቤት ለሆነው ጌታና እንዲሁም ለሚያገለግሉት ሕዝብ እውነተኛ ፍቅር የሌላቸው፥ የአገልግሎት ፍቅር ብቻ ያላቸው ሰዎች እንዳሉ

የታወቀ ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ በስ አገልግሎታቸው ይጋደላሉ። አንድ ጊዜ አንዱ "አገልግሎቴን ይወስድብኛል" ብሎ የፈራውን ሰው፣ *"በአገልግሎቴ ቀልድ አላውቅም፤ አፍንጫህን ነው የምልህ! ተጠንቀቅ"* አለው። ስለሆኑ በዚህ ዓይነት መንፈስ እውነተኛ የሆነ አገልግሎት መስጠት ይቻል ይሆን? *"ትወደኛለህ?"* የሚለው ጥያቄ ልማዳዊና ለሥርዓት ብቻ ተብሎ የሚቀርብ ተራ ጥያቄ ሳይሆን፣ በአገልግሎት ውስጥ የተሰማራ ማንኛውም መንፈሳዊ መሪ ራሱን ሊጠይቅ የሚገባው አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ ነው። እውነተኛው እረኛ ስለ በጎቹ ሲል ሕይወቱን እስከ መስጠት ድረስ የወደዳቸውን በጎች፥ ፍቅር በሌላቸው አገልጋዮች እንዲገለገሉ፣ እንዲሁም ሀሰተኛ በሆኑ አገልጋዮች እጅ ወድቀው እንዲበዘበዙ አይፈልግም። ክርስቶስን በወደድነው መጠን፥ ልባችን በእርሱ ፍቅር ይሞላል፤ ይህንን ከእርሱ የተቀበልነውን፣ በውስጣችን ያለውን ፍቅር፥ ለሌሎች እናከፋፍላለን። ክርስቶስን በወደድነው መጠን፥ በልባችን ውስጥ በዚያው መጠን ለበጎቹ ልዩ የሆነ ፍቅር ይኖረናል።

"ትወደኛለህ?" የሚለው ጥያቄ፣ በጥንት ዘመን ብቻ ሳይሆን፣ በአሁኑ ዘመን ላለነውም አገልጋዮችም ውስጣችንን የሚመረምር አግባብነት ያለው ጥያቄ ነው። *ዛሬ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየቦታው የሚፈጠሩት ችግሮች ከምክንያቶቹ አንደኛውና ዋናው፣ ለበጎቹም ሆነ ለበጎቹ ባለቤት እውነተኛ የሆነ ፍቅር የሌላቸው መሪዎችና አገልጋዮች የመሪነቱን ሥፍራ በመያዛቸው ነው።* መንፈሳዊ መሪ፣ የሚመራውን ሕዝብ ወደ ክርስቶስ የበለጠ ማስጠጋት የሚችለው፣ ክርስቶስ ያለውን ዓይነት ፍቅር ሊኖረው ብቻ ነው። የፍቅር ሰው መሆን የሚያስፈልገው መንፈሳዊ መሪ ለሆኑት ብቻ አይደለም። ማንኛውም እውነተኛ አማኝ፣ በክርስቶስ ፍቅር ሌላውን ማፍቀር እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (1 ዮሐ. 3፥10, 14, 4፥8)። "ፍቅር" የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆናችንን የሚያሳይ ምልክት ነው። ክርስቶስ *"አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ይኸውም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው፤ እንግዲህ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደ ሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ"* (ዮሐ. 13፥34-35) ይላል። የክርስቶስ ፍቅር ፍጹምና ወሰን የሌለው ሲሆን፣ የሰው ፍቅር ግን በጣም ውስንና ተለዋዋጭነት ያለው፣ ከፍጹምነት ደረጃ ለመድረስ ገና ብዙ የሚቀረው ነው። ይሁን እንጂ፣ አማኝ በግል ሕይወቱ ከክርስቶስ ጋር በጣም እየተቀራረበ ሲመጣ፣ *የክርስቶስን ዓይነት ፍቅር፣ ይኸውም ተግባራዊ የሆነ፣ ቅድስና ያለው፣ እንዲሁም መስዋዕትነት ያለው ፍቅር በሕይወቱ መታየት ይጀምራል።* በውስጡ ያለው ፍቅር፣ እንደ ክርስቶስ ፍቅር ፍጹምና ንጹህ ሲሆን፣ የክርስቶስ ውበትና ክብር በሕይወቱ ከምንጊዜውም የበለጠ ጎልቶ መታየት ይጀምራል። እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው፣ ከእርሱ ጋር የቀረብ ግንኙነት ያላቸው ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ከሌሎች ተለይተው የሚታወቁት፣ ለነፍሳት ባላቸው ፍቅርና ርህራሄ እንደሆነ ታሪካቸው ይመሰክራል።



- ***ጆን ኖክስ (John Knox)*** –ስለ እስኮትላንድ ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት፣ ትልቅ ሸክም የነበረው ሰው ነበር። ከነበረው ከፍተኛ ሸክም የተነሳ፣ ሁልጊዜ ማታ ደረቅ ወለል ላይ በደረቱ ተደፍቶ ሲጸልይ ያድር ነበር። ሚስቱ ሁኔታውን እያየች "እባክ ህን ትንሽ እንኳን ተኛና እረፍ" ስትለው፣ *"የአገሬ ሕዝብ እየጠፉ እያየሁ እኔ እን ዴት መተኛት እችላለሁ?"* ይላት ነበር። ሌሊቱን ሙሉ *"ጌታ ሆይ! እባክህን እስኮትላ ንድን ስጠኝ፤ ካልሆነ ግን ሞትን እመርጣለሁ"* በማለት ለእስኮትላንድ ሕዝብ በእግዚ አብሔር ፊት ይማልድ ነበር።
- ***ጆን ዌስሊ (John Wesley)*** በጊዜው በእርሱ አካባቢ የነበሩትን የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችን በአገሪቱ ውስጥ ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንዲነሳ በጸሎት እንዲ ተጉ አጥብቆ አደራ ይላቸው ነበር። *"ሁላችንም አንድ ዓላማ፣ አንድ አሳብ ይኑረን። በሕይወት የምንኖረው ለራሳችን ደህንነት ብቻ ሳይሆን፣ የሚጠፉትን ሰዎች ሕይ ወት ለማዳን ጭምር ነው"* በማለት በአገልግሎታቸው እንዲተጉ አደራ ይላቸው ነበር። ጆን ዌስሊ ስለ ሕዝቡ መጥፋት በጣም ያስብና ይጨነቅ ስለነበረ፣ *"ጌታ ሆይ! ከኃጢአት በስተቀር ማንንም የማይፈሩ፣ የእግዚአብሔርን ነገር እንጂ ሌላ ነገር የማይፈልጉ አንድ መቶ መጋቢዎችን ስጠኝ። እነዚህ የሲኦልን በር ያንቀጠቅጣሉ። የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ይመሠርታሉ"* ብሎ ወደ እግዚአብሔር ይጮኽ ነበር።
- ***ዴቪድ ብሬንርድ (David Brained)*** ለሕንድ አሜሪካውያን ወንጌልን ለመስበክ የተላከው የወንጌል መልዕክተኛ ሲሆን፣ በየቀኑ በሚጽፈው ማስታወሻ ላይ፣ *"ለአገልግሎት የበለጠ እንዲያዘጋጀኝ የዛሬውን ቀን ለጸሎትና ለጾም መድቤዋለሁ። በዚህ ቀን ከሰዓት በፊት ለሚጠፉት ነፍሳት እንድማልድ፣ ከሰዓት በኋላ ደግሞ. በጸሎት እንድቃትት አስችሎኛል። ያለሁበት ሥፍራ ቅዝቃዜና ንፋስ የበዛበት ቢሆንም፣ ከጭንቀቴ የተነሳ በላብ ተጥለቅልቄአለሁ። ነፍሴ ለዓለም ደህንነት ትጮኻለች። ስለ እግዚአብሔር ልጆች ከማስበው ይልቅ ለሚጠፉትና ለኃጢአተኞች አስባለሁ። ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ እስካመጣሁ ድረስ፣ ምቾት ስለሌለው ኑሮዬና ስለማልፍበት መከራና ችግር ፍጹም ግድ የለኝም"* አለ።
- ***ፊልፕ ዶድሪጅ (Philip Doddridge)*** *"ከማንኛውም ነገር የበለጠ ለነፍሳት መዳን እጨነቃለሁ። ማሰብ ብቻ ሳይሆን እምትለታለሁ"* አለ።
- ***ጆን ስሚዝ፣ (John Smith)*** እንግሊዛዊ ሰባኪ፣ *"ልቡ የተሰበረብኝ ሰው ነኝ። ይኸም ስለ ራሴ በማሰብ ሳይሆን፣ ስለ ነፍሳት በማሰብ ነው። የነፍሳት ዋጋ ምን*

*ያህል ውድ እንደሆን ጌታ ስላሳወቀኝ፣ ነፍሳት ሲድኑ ካላየሁ መኖር አልችልም። ነፍሳትን ስጠኝ፤ ካልሆን ግን መኖር አልፈልግም" አለ።*[22]

## 2. እውነተኛ ፍቅር ምንድን ነው?

ፍቅር ትክክለኛውን ትርጉም ያጣበት ብቻ ሳይሆን፣ እየቀዘቀዘም የመጣበት ዘመን ይሆን እኔና እናንተ ያለነው? ከ200 ዓመት በፊት የተዘጋጀ፣ ለማንኛውም ነገር መረጃ የሚሰጥ መጽሐፍ (encyclopedia)

- "አቶም" (atom) የሚለውን ቃል የገለጸው በአራት መስመር ሲሆን፥ "ፍቅር" የሚለውን ቃል ለመግለጽ 5 ገጽ ሰጥቶታል። በቅርቡ የተዘጋጀው "ኢንሳይክሎፒድያ" ግን "አቶም" የሚለውን ቃል ለመግለጽ 5 ገጽ ሲሰጠው፣ "ፍቅር" የሚለውን ቃል ግን ዘሎታል።

እውነተኛ ፍቅር ምንድነው? *"የፍቅር ሰው"* የሚባለውስ እንዴቱ ዓይነቱ ነው? በፍቅር ውስጥ ያለውን ኃይል የበለጠ ለመረዳት፣ ራሱ ፍቅር የሆነውን ጌታ ኢየሱስንና ያሳየውን ፍቅር ማወቅ ይጠቅማል። ዓለምን ለመግዛት የሞከሩ ታላላቅ ሰዎች በዘመናት ተነስተው እንደ ነበረ ታሪክ ይመሰክራል። አብዛኞዎቹ ኃይልና ሥልጣን፥ ዝናና እምባ ገንንተን እንደ ውሃ የተጠሙ፥ በዓለም ያለውን ወርቅና ልዩ ልዩ ዕንቁ አግበስብሰው ለመያዝ የሞከሩ ናቸው። ዓለምን በእጃቸው ለመጨበጥ፥ በእግራቸው ሥር ለመርገጥ፥ ትናንሽ እግዚአብሔሮች ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ያድረጉ ናቸው። ሺ፥ አስር ሺ፥ መቶ ሺ፥ ከዚያም በላይ ወታደሮች አሰልፈዋል። ጦር መዘዋል፤ ጥይት፥ መድፍና መትረየስ ተኩሰዋል፤ ቦንብ ወርውረዋል። ሺ፥ መቶ ሺ፥ ሚሊዮን ገድለዋል፤ ህጻን፥ ወጣት፥ ሽማግሌ፥ ነፍሰ ጡር ሳይመርጡ ብዙዎችን አጥፍተዋል። ከብዙዎች መካከል ሂትለር፥ ናፖሊዮን፥ ምሶሎኒ፥ ኔሮ፥ አሌክሳንደር ይገኙበታል። እነዚህ ሁሉ ታሪካቸውን በሰው ደም አያጠቀሱ የጻፉ ናቸው። ይሁን እንጂ ምኞታቸው ባይሳካላቸው፥ ዓለምን በመግዛት ፈንታ ተዋርደው የሞቱ ናቸው።

ከ2 ሺ ዓመት በፊት በፓላስታይን አንድ ልዩ ሰው ተነስቶ ነበር። ይህ ሰው የጦር መሣሪያ የያዙ ወታደሮችን አላሰለፈም። ጥይት አልተኮሰም፤ ቦምብ አላፈነዳም፤ የጦር ዓይሮፕላን አላበረረም፤ ሌላው ቀርቶ ማንንም በጥፊ አልመታም፤ የማንንም ንብረት አልነጠቀም። የለበሰውን ልብስ ከላዩ ገፍፈው ሲወስዱና ዕጣ ሲጣጣሉበት እንኳ ምንም አላለም። ይሄን ሰው ኢሳያስ ሲገልጸው *"መልክና ውበት የለውም፤ ባየነው ጊዜ እንወደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። የተናቀ ከሰውም ዘንድ የተጠላ የህማም ሰው፥ ደዌንም*

---

[22] Duewel. L. Wesley. Ablaze For God, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, Michigan. c1989.



*የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሠውርበት የተናቀ ነው፤ እኛም አላከበርነውም"* ይለዋል (ኢሳ. 53፥2-3)። ይሄ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ደካማ ሳይሆን ዓለምን የገዛ ኃያል ሰው ነው። ዓለምንም የገዛው በጦር ኃይል ወግቶ ሳይሆን በፍቅር ነው። የዚህን ሰው ፍቅር ዮሐንስ ሲገልጽ፣ *"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና፤ በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል"* ይላል (1 ዮሐ. 3፥16)። ፍቅር እግዚአብሔር በክርስቲያኖች ሕይወት ላይ የሚያትመው ማህተም ሲሆን፣ በተለይ በመንፈሳዊ መሪዎች ሕይወት ላይ ጎልቶ መታየት ያለበት ምልክት ነው። ጥሩ የአመራር ችሎታ ኖሮት ፍቅር ከሌለው ግን፣ መሪ ለመሆን ብቃት ያለው አይደለም (1 ቆሮ. 13)።

እኛ ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን በመሆናችን፣ የፍቅር አምላክ የሆነውን ጌታ በፍቅሩ እንመስለዋለን። በፍቅሩ እርሱን መስለን ከተፈጠርን፣ ፍቅርን በመስጠትም ሆነ ለመበቀል የሚያስችል ዝንባሌና አቅም አለን። ሕይወታችን በመንፈስ ቅዱስ ሲዳሰስ፣ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ፍቅር፣ ወደ ሌሎች ማስተላለፍ እንችላለን። የፍቅርን ትክክለኛ ትርጉም የበለጠ ለማወቅ በግሪክ ቋንቋ *"ፍቅርን"* የሚገልጹትን አራት የተለያዩ ቃላት መመልከት ይጠቅማል።[23]

- *1ኛው፥ "ኤሮስ" የሚለው ቃል ነው።* ይሄም በወንድና በሴት መካከል ያለውን ፍቅር የሚገልጽ ነው። ይህን ዓይነቱ ፍቅር መሠረቱ ስሜት ሲሆን፣ በወንድና በሴት መካከል ባለው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ወይም መነካካት የሚታይ ነው። ይህን ዓይነቱ ፍቅር በጋብቻ ክልል ውስጥ እስከ ሆነ ድረስ በጣም ጥሩ ነው። ከጋብቻ ክልል ውጪ ከሆነ ግን ኃጢአት ነው።

- *2ኛው፥ "ፊልዮ" የሚለው ቃል ነው።* ትኩስ፥ በሥጋ፥ በአዕምሮና በመንፈስ ከሌላው ጋር ያለውን በጣም የተቀራረበውን ወዳጅነት ይገልጻል። ይህን ዓይነቱ ፍቅር ከፍተኛም ቢሆን ወዳጅነቱ እንቅፋት አጋጥሞት ሲቀዘቅዝ፥ ፍቅሩም እየደበዘዘ ይሄዳል። ይህን ዓይነቱ ፍቅር ሁሉን የሚያቅፍ ሳይሆን ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ነው።

- *3ኛው፥ "ስቶርጂ" የሚለው ቃል ነው።* ወላጆች ለልጆቻቸው፥ ልጆች ለወላጆቻቸው የሚኖራቸውን ፍቅር የሚገልጽ ነው። ይሄ የቤተሰብ ፍቅር እንጂ ሁሉን የሚያጠቃልል አይደለም።

- *4ኛው፥ "አጋፔ" የሚለው ቃል ነው።* ለማይገባው ሰው እግዚአብሔር ፍቅሩን የሚገልጽበት ነው። ጳውሎስ ሲገልጸው *"ነገር ግን ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ*

---

[23] Hocking, L. David. Be a Leader People Follow, G/L Publications, Glendale, California, 1979.

*ሲሆ እኛ ሞተልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል"* ይላል (ሮሜ 5፥8)። "አጋፔ" ፍቅር እንጂ ስሜት ብቻ አይደለም። የአጋፔ ፍቅር ያሰው ራሱን መሰዋዕት የሚያደርግና በርህራኄ የተሞላ ነው። ፈቃዱን የሚቆጣጠረው ሌላ ነገር ሳይሆን ፍቅር ነው። የአጋፔ ፍቅር ያሰው ሰው ሌሎችን የሚወደው፥ ተወዳጆች ሲሆኑ ብቻ ሳይሆን የማይወደዱም በሚሆኑበት ጊዜም ነው። ምንም ዓይነት ዋጋ ቢያስከፍል የአጋፔ ፍቅር ያሰው ሌላውን ይወዳል። መንፈሳዊ መሪ የሚመራውን ሕዝብ መውደድ ያለበት፣ በአጋፔ ፍቅር ነው።

በዘመናችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናየው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነውን 'ፍቅርን ሳይሆን፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንአት፥ ቁጣ፥ አድመኝነትና መከፋፈልን ነው። ዛሬ በዓለም ካሰው የበለጠ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሰው "ጥርሰ መሳበር" እንዲሁም "የእርስ በርስ ጦርነት" እይሎ ይታያል። የዘመኑ ክርስቲያኖች በጥላቻ፥ በመራራነት፥ በቂም በበቀል ተሞልተን ራሳችንን "ክርስቲያን" ብለን መጥራቱ ከባድ አይሆንብንም። ሰመሆኑ ክርስቲያኖች መሆናችንን ሌሎች የሚለዩበት በምን ይሆን? ክርስቶስ እንዳለው "በፍቅራችን" ይሆን? ዓለማውያን በዘመኑ ያስነውን ክርስቲያኖች የሚያውቁን በፍቅራችን ሳይሆን፥ በመከፋፈላችን፥ ወገን ለይተን በመቧቀሳችን ነው። ያለፍቅር ክርስቲያን መሆን እንደማንችለው ሁሉ፥ ፍቅር የሌለበት አገልግሎትም ዋጋ የሰውም። ይህንን እውነት ብናውቅም፣ የሕይወታችንን አቅጣጫ ሰመለወጥ እርምጃ እንዳንወስድ አዕምሯችንን የቆሰፈው ምን ይሆን? መንፈሳዊ መሪዎች፣ ራሳቸው ፍቅር ምን እንደሆን ካልገባቸው፥ በፍቅር ካልተመላለሱ፥ ሌሎች ምዕመናን ስለ ፍቅር እንዴት ማስተማር ይችላሉ?

መንፈሰ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍቅር (አጋፔ) በውስጣችን ያፈሳል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ እውነት ሲገልጽ፣ *"...እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና"* ይላል (ሮሜ 5፥5)። በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላን፣ ቅዱስ የሆነውን ፍቅሩን ያስማቋረጥ በብዛት ወደ ውስጣችን ለማፍሰስ ነው። መውደድ የምንችለው፣ ፍቅር የሆነው ጌታ፣ የራሱን የፍቅር ባሕሪ በውስጣችን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሲያፈስ ልባችንን ከፍተን የተቀበልነው እንደሆን ነው። በውስጣችን ያሰውን የእግዚአብሔርን ፍቅር በሌሎች ሕይውት ውስጥ ባፈሰስን ቁጥር፣ የበሰጠ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ፍቅሩን ይሞላናል። ይህ እውነት ከሆነ፣ መንፈሳዊ መሪ ከተራ አማኝ የበለጠ በሚመራቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ ፍቅሩን ማፍሰስ ይገባዋል። የፍቅር ምሳሌ መሆን ካልቻለ፣ ወይም የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች ማሳየት (መስጠት) ካልቻለ፣ የእግዚአብሔር አምባሳደር ለመሆን አይበቃም። ጳውሎስ *"...እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን፤ እግዚአብሔርም በእኛ አማካይነት ጥሪውን ያቀርባል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን"* ይላል ( 2 ቆሮ. 5፥20)። ፍቅርን የማይሰጥ መንፈሳዊ መሪ፣ "የእውነተኛ ፍቅር እንደራሴ" መሆን አይችልም። "ፍቅር" ለመንፈሳዊ አገልግሎት መሰክት ዋና ቁልፍ ነው። ፍቅር መሪውን እውነተኛ እረኛነቱን ያሳያል።



## 3. ጥሩ መሪ ተለይቶ የሚታወቅበት ምልክቱ "ፍቅር" ነው

መንፈሳዊ መሪን "ጥሩ መሪ" የሚያሰኘው ትልቁ ነገር ለሚያገለግላቸው ምዕመናን ያለው ርህራሄና ፍቅር ነው። ያለፍቅር ደቀ መዝሙርነት አይገኝም። የሚያገለግላቸውን ምዕመን መውደድ ከባድ የሚሆንበት መንፈሳዊ መሪ፥ "በሕይወቴ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር አለ ወይ?" ብሎ ራሱን መመርመርና መጠየቅ አለበት። ዮሐንስ *"እግዚአብሔር ፍቅር ነው"* ይላል (1 ዮሐ. 4፥8)። ስለዚህ ሰው ፍቅርን ከእግዚአብሔር ያገኛል እንጂ፣ ከራሱ አያመነጭም። የእግዚአብሔር ፍቅር የተለየና ከማንኛውም ዓይነት ፍቅር የበለጠ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር በተግባር የሚገለጥ እንጂ፣ ተራ ስሜት ብቻ አይደለም። ጊዜ፥ ቦታና ሁኔታ አይወስነውም። ሰደስታ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ በችግርና በመከራም ጊዜ ይኖራል። ታይቶ የሚጠፋ ሳይሆን፥ ዘላለማዊነት ባህሪ ያለው ነው። መንፈሳዊ መሪ ወይም ፓስተር መሆን ቀላል አይደለም። ከምክንያቶቹ አንደኛው የሚወደድ ባህሪ የሌላቸውን፥ በጣም አስቸጋሪ የሆኑትን ሰዎች ሁሉ መውደድ ስላለበት ነው። ያ ደግሞ ከማንኛውም ነገር የበሰጠ ከባድ ነው። ይሁን እንጂ፥ በአንድ ቀን ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥሩ እረኛ (መጋቢ) መሆን ስለማይችሉ ተስፋ ሊቆርጡ አይገባም። በአጭር ጊዜ ተምረን የምንደርስባቸው ብዙ ሙያዎች አሉ። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጥሩ አድርጎ በፍቅር ለማገልገል ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተምረን የምንደርስበት አይደለም። መንፈሳዊ መሪ ወይም እረኛ፥ ጥሩ አገልጋይ መሆን የሚችለው ቀስ በቀስ፥ "የመስቀልን መንገድ" በትዕግሥት ከተራመደ በኋላ ነው። ብዙ መንፈሳዊ መሪዎች የእረኞች አለቃ ለሆነው ክርስቶስ ፍቅር አላቸው። ያንን የመሰለ ፍቅር ግን ለሚጠብቋቸው ለእግዚአብሔር በጎች የላቸውም። ብዙዎች አገልግሎታቸውን መፈጸም አቅቷቸው ከአገልግሎት የሚወጡበት አንደኛውና ትልቁ ምክንያት፥ "አስቸጋሪ ናቸው" ብለው የሚያስቧቸውን ሰዎች መቀበልና ማፍቅር ከባድ ስለሚሆንባቸው ነው።

እውነተኛ እረኛ ያልሆነው በግል ሕይወቱ የችግር ማዕበል ሲነሳበት፥ መንጋውን ጠላት ሲመታው፥ አገልግሎቱን ሲጀምር የነበረው ደስታ ይጠፋና፥ ልቡ በመራራነት የተሞላ ይሆናል። አንዳንዶቹም *"አገልግሎቴ ከሰው ጋር ጨርሶ የማያገናኝ ቢሆን ኖሮ በጣም ጥሩ ነበር"* ሲሉ መስማት እየተለመደ መጥቷል። ይሄን ዓይነቱ አባባል መጋቢዎች በሚያገለግሉት ሕዝብ ምክንያት ልባቸው ምን ያህል እንደሚያዝን ያሳያል። በዚህ ምክንያት አንዳንድ መጋቢዎች ከአገልግሎት ውስጥ ከሰው ጋር የማያገናኛቸውን አንዱን ወይም ሁሉቱን ዓይነት አገልግሎት አጥብቀው ይዘው ሌላውን ችላ ሲሉ ይታያሉ። የመጋቢ ኃላፊነት ቃሉን መስበክና ማስተማር፥ እንዲሁም ለሕዝቡ የምልጃ ጸሎት ማቅረብ ብቻ ነው ብለው የሚከራከሩ አሉ። ምዕመናኖቻቸው ከአገልጋዮቻቸው ጋር የተቀራረበ ግንኙነት መፍጠር እንደማይፈልጉ ይናገራሉ። ለሚያገለግሏቸው ሰዎች ፍቅርና ርህራሄ የሌላቸው፣ እውነተኛ "መንፈሳዊ መሪ" (መጋቢ) መሆን በጣም አስቸጋሪ ይሆንባ

ችዋል። በዓለም ውስጥ ያለው የአስተዳደር ወይም የአመራር ሥልት፥ "ፍቅር" የሚለውን አሳብ አይጨምርም። የመንፈሳዊ አስተዳደር ግን ያለፍቅር ሊንቀሳቀስ አይችልም።

ሰዎችን መውደድ፣ በተለይ አስቸጋሪ የሆኑብንን መውደድ "ቀላል ነው" ባንልም፣ ሁሉን በሚያስችለው ጌታ እንችላለን። ብዙ መንፈሳዊ መሪዎች ይህን እውነት ቢያውቁትም ለምን ቀላል እንዳልሆነ ግን አይረዱትም። አንዳንዶች ፍቅር ለማሳየት ቢሞክሩም፣ አንድ ትንሽ በጎ ያልሆነ ነገር ሲያጋጥማቸው፣ በቀላሉ ተስፋ ይቆርጣሉ። በዓለም አስተዳደር ውስጥ ያሉ መሪዎች ከሥራቸው ሆነው ከሚያገለግሉት ጋር በብዙ ነገር ይለያያሉ። መሪዎች ከሌሎች ሠራተኞች የተለየ መብትና የተመቻቸ ሁኔታ ይኖራቸዋል። በሠራተኞችና በአለቆቻቸው መካከል የተቀራረበ ግንኙነት ወይም ወዳጅነት አይኖርም። መቀራረቡ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል ተብሎ ስለሚታመን በመካከላቸው መቀራረብ አይኖርም። እርግጥ ነው መሪ የሆነ ሰው ብቻውን መሸከም ያለበት ኃላፊነት አለ። አንዳንዱን ነገር ለሠራተኞች ማካፈል ቢፈልግ እንኳን አይችልም። ይሁን እንጂ፥ ራሱን ከሥሩ ካሉት ሠራተኞች ፍጹም ማሸሹ ወይም ማራቁ ትክክል አይደለም። በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ ያለው አመራር ግን ይህን አይመስልም። አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊነታቸውን በጥንቃቄ ሳትመረምር፥ በዓለም ውስጥ ያላቸውን ሥልጣንና ደረጃ፥ እንዲሁም ያላቸውን ትምህርት በማየት ብቻ ሽማግሌዎች መርጣ የምትሾምበት ጊዜ አለ። እነዚህም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ በዓለም ውስጥ ያለውን የአስተዳደር ሥልት ተከትለው ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ሲሞክሩ ትልቅ ችግር ይፈጠራል። በመሪዎችና በምዕመናኑ መካከል የተቀራረበ ግንኙነት እንዲኖር በመፍቀድና በመጣር ፈንታ፥ መሪዎቹ የማይደረስባቸው፣ ሌላው ቀርቶ እጃቸውን ለመጨበጥ እንኳን ደጅ የሚያስጠኑ ይሆናሉ። አንዳንዶቹ ጥሩ ያደረጉ መስሏቸው፣ ሕይወታቸውን ሰጥተው የሚያገለግሉትን አገልጋዮችን፣ በመሥሪያ ቤታቸው ቅጥር ሠራተኞችን እንደሚሉት "...ተጠንቀቁ! እኛ የእሳት ልብ የለንም... በሰዓት ገብታችሁ በሰዓት ካልወጣችሁ፣ በቀላሉ እንሊታችሁም" የሚሉ አሉ። አንዳንዶችም ተገልጋዩ ሕዝብ ዕርዳታ ፈልጎ ሲመጣ፣ "ሁሉንም ማነጋገር አልችልምና እየመረጣችሁ አቅርቡልኝ" የሚሉም አሉ። ይሄን ዓይነቱ አመራር ለቤተ ክርስቲያን ዕድገትም ሆነ ጤንነት አይጠቅምም። ይህን ስንል በዕለታዊ ሥራቸው ጥሩ ደረጃና ሥልጣን ያላቸው፥ እንዲሁም የተማሩ ክርስቲያኖች ለመሪነት መመረጥ የለባቸውም ማለታችን ሳይሆን፥ ልባቸው በክርስቶስ ፍቅር ያልተሞሉ ፍቅር የሚያስፈልገውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አይምሩ ማለታችን ነው።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ቢጠራቸው በቅርብ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ነበር (የማር. 3፥14)። ጥሩ መንፈሳዊ አመራር ሊኖር የሚችለው በመሪዎችና በምዕመናን መካከል የተቀራረበና እንዲሁም ጥሩ ግንኙነት ያለ እንደሆነ ነው። በመካከላቸው እውነተኛ አንድነት፥ ጥሩ ሕብረት፥ ከሁሉ የበለጠ ፍቅር ሲኖር ነው። ምዕመኑ መንፈሳዊ መሪያቸው እንደሚወዳቸው፥ ለእነርሱም በጎነት እንደሚሠራና እንደሚለፋ ማወቅ



አለባቸው። እርግጥ ነው አንዳንድ ሰዎችን መውደድ ከባድ ነው። የፍቅር አምላክ የሆነው፣ ችግራችንን የሚረዳው ጌታ፥ እውነት የማይናገሩትን፥ በጣም አስቸጋሪ የሆኑብንን አንዳንድ ሰዎች መውደድ የምንችልበትንና የምንታገስበትን ጸጋውንና ኃይሉን ይሰጠናል። የእግዚአብሔር ፍቅር ሕይወታችንን የሚቆጣጠረው ከሆነ፥ ፍቅር ሳይኖረን ፍቅር ያለን ለመምሰል አንሞክርም። በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ስንሆን፥ እውነተኞች፥ ታማኞች፥ እንዲሁም ሕይወታችንን ሌሎች በግልጽ እንዲያዩት መፍቀድ ከባድ አይሆንብንም። ሌሎች ስለ እኛ ምን ያስቡ ይሆን? ብለን አንጨነቅም። መንፈሳዊ መሪዎች፣ የሚያገለግሏቸው ሰዎች ስለ መሪዎቻቸው የራሳቸው የሆነ አስተያየትና ግምት እንዳላቸው በመገንዘብ፣ "ሰዎች ምን ይሉኝ ይሆን?" የሚለው ጥያቄ ሁልጊዜ አዕምሯቸውን ሊያስጨንቀው አይገባም። ሕይወታቸው ሁልጊዜ በሌሎች ፊት የተከፈተ መዝገብ ስለሆነ፥ ሰዎች በእነርሱ ላይ የሚሰጡት ግምትም ሆነ አስተያየት ሊያሳስባቸው አይገባም። መንፈሳዊ መሪዎች ልዩ የሆነ የተፈጥሮ ጠባይ ካላቸው ሰዎች ጋር ሕይወታቸው የተያያዘ መሆኑን አውቀው፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለመደገፍ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

## 4. መንፈሳዊ መሪዎች "ሰዎችን ለመውደድ" ያለባቸው ችግር

ለስኬታማ አገልግሎት ፍቅር ዋና ቁልፍ ከሆነ፣ አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ መሪዎች የሚያገለግሉትን ሕዝብ መውደድ በጣም አስቸጋሪ የሚሆንባቸው ምክንያት ምን ይሆን? ለችግሮቻቸው መፍትሄ ለመፈለግ፣ በቅድሚያ ችግሮቻቸውን ለይተው ማወቅ አለባቸው።

### 4.1. አንዳንድ መሪዎች በብዙ ሥራ ይጠመዳሉ

መንፈሳዊ መሪ ወይም አስተዳዳሪ የሆኑ ሰዎች፣ "ከሌሎች የበለጠ ወይም ነገር ከእኛ ይጠበቅብናል" ብለው በማሰብ፣ ወይም በሌላ ምክንያት ከተቻላቸው መጠን ብዙ ለመሥራት፥ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት በኃይል መሥራት ክፉ ባይሆንም፣ የሚያሳዝነው ግን መንፈሳዊ መሪዎች በልዩ ልዩ ሥራዎች በስሚጠመዱ፥ የሚያገለግሏቸውን ሰዎች ፍላጎት ለማሟላት በቂ ጊዜ የሌላቸው መሆናቸው ነው። ባለባቸው የሥራ ብዛትና እንዲሁም ኃላፊነት ምክንያት ከሰዎች ጋር ለመወያየትም ሆነ ለመቀራረብ በቂ ጊዜ አይወስዱም። የትኛውን ማስቀደም፥ የትኛውን ማስከተል፥ ወይም በየትኛው ነገር ላይ የበለጠ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ለይተው አያውቁም። አንዳንድ መሪዎች የሕዝቡን ችግር ከማቃለል፥ የሕዝቡን ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ፥ ከሰው ፍላጎትና ጥያቄ ጋራ ግንኙነት በሌለው ነገር ላይ ብዙውን ጊዜያቸውን ያጠፋሉ። እርግጥ ነው አንዳንድ ሥራዎች የግድ መሠራት አለባቸው። ይሁን እንጂ፥ የሰዎችን ፍላጎት አለማሟላት፥ ለጥያቄያቸው አስፈላጊውን

መልስ አለመስጠት፣ ከተጠሩበት ዓላማ ውጪ እንዲሚያደርጋቸው መዘንጋት የለባቸውም። ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ ለአንድ ሰውም ሆነ ለብዙ ሕዝብ፣ አስፈላጊውን ጊዜ ይሰጥ እንደነበረ እናስታውሳለን። መንፈሳዊ መሪዎች "ቅደም-ተከተላቸውን" (priority) መጠበቅ ወይም ማስተካከል አለባቸው። ከሚያገለግሏቸው ሰዎች ጋር ጊዜ ማሳልፍ ጠቃሚ እንዳልሆነ፥ ወይም ጊዜን እንደማባከን አድርገው መመልከት የለባቸውም። ዩአንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማነጋገር፣ ለድስት ወር እንደሚያስጠብቅ ሰምቼ አለደንቆኛል።

እርግጥ ነው በተፈለጉ ቁጥር፥ ወይም በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ለሚፈልጋቸው ሁሉ በቀላሉ የሚገኙ፥ ሰዎች ራሳቸው ሊያቃልሉት የሚችሉትን፣ ጥቃቅኑን ነገር ሁሉ በመሪዎች ላይ ይጣሉ ማለት አይደለም። ሁሉንም ነገር በመሪዎች ላይ እንዲጥሉ የሚፈቀድላቸው ከሆነ፥ ሕዝቡ የራሱን ችግር መፍታት እንዳይማር፥ ለእድገቱ የሚረዳውን ነገር መከልከላቸው ብቻ ሳይሆን፥ የተቀረውን ሥራቸውንና ኃላፊነታቸውን እንደሚገባው እንዳይፈጽሙ ለራሳቸው መሰናከያ መፍጠራቸው ይሆናል። ይሁን እንጂ መንፈሳዊ መሪ የሚያገለግለውን ሕዝብ ፍላጎትና ጥያቄ፥ ሊሠራው ካቀደው ፕሮጀክት የበለጠ መሆኑን ለማሳየት፥ ችግሩን ለማዳመጥም ሆነ ለመምከር ጊዜ መስጠት አለበት። ፍቅርና ታማኝነት አብረው የሚሄዱ ወይም የተያያዙ ናቸው። ሰመሪውና በሚመራው ሕዝቡ መካከል ፍቅር ባየለ ቁጥር፥ በመካከላቸው ያለው መተማመንና ግንኙነታቸው የበለጠ እየጠነከረ ይመጣል። በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ የገለጽነው፣ *"እንዴት ልውደድ?" – "እመን" – "እንዴት ልመን?" – "ውደድ"* የሚለው አባባል ጥሩ ትምህርት ይሰጠናል።

## 4.2. አንዳንድ መሪዎች በራሳቸው ላይ ሸክም ያበዛሉ

ብዙ ጊዜ የመንፈሳዊ መሪዎች ችግር ዋና ምንጩ ከውጪ ሳይሆን፣ ከራሳቸው ነው። ከማንኛውም ሰው የበለጠ፣ "ፍጹምነትን" ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛ ውጤትን ከራሳቸው ይጠብቃሉ። የሚመሯቸው አገልግሎትም ሆነ ቤተ ክርስቲያንን ዝቅ ተደርጎ እንዳይገመትና እንዳይወቀስ፣ ማንኛቸውም ነገሮች ያለአንዳች ስህተት መሠራት አለባቸው ብለው ያምናል። በዚህ ምክንያት ራሳቸውን ከመጠን በላይ ያስጨንቃሉ። "ከዚህ በላይ መሥራት አቅሜ አይፈቅድም" በማለት ራሳቸውን መግታት አይፈልጉም። በዚህ ዓይነት ቀስ በቀስ ከዚህ በፊት ሲሠሩት ደስ የሚላቸው ሥራ ሁሉ ሸክም እየሆነባቸው ይመጣል። ይህን ዓይነቱ ሁኔታና ስሜት በዚህ ዓይነት ከቀጠለ፣ ወደ ከፋ ችግር ውስጥ የሚከታቸው መሆኑን አይገነዘቡትም። በራሳቸው ላይ የሚጭኑት ሸክምም ሆነ ግፊት፥ ከሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት፥ የሚያገለግሏቸው ሰዎች ፍላጎትና ጥያቄ የሚመልሱበት ጊዜ እያጡ ይመጣሉ። ከሥራ ብዛት የተነሳ፥ ያለበቂ ምክንያት በቀላሉ የሚቆጡ፥ ትዕግስት የሌላቸው፣ የሚያዝኑና የሚበሳጩ ሰዎች ይሆናሉ። ምዕመናኑም ሁኔታቸውን አያዩ በመቅረብ ፈንታ ቀስ በቀስ እየሸሿቸው ይመጣሉ። ራሳቸውን በብዙ



ሥራ ውስጥ የሚከቱት፥ ብዙ በመሥራታቸው ሰዎች የሚያደንቋቸውና የሚያከብሯቸው ሊመስላቸው ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ከሚያገለግሉት ሕዝብ እየራቁ እንደሚሄዱ ግን አይገነዘቡትም።

የሚያገለግሉት ሕዝብ፣ ከሚያገለግላቸው መንፈሳዊ መሪ ፍቅርን ማየት ይፈልጋል። የሚያሳዝነው ግን፣ መሪዎች በተለያየ ምክንያት በራሳቸው ላይ ሸክምና ኃላፊነት በማብዛቱ፥ ለሕዝቡ አስፈላጊውን ፍቅርና እንዲሁም የማበረታቻ ቃል የሚሰጡበት ጊዜ ያጣሉ። መንፈሳዊ መሪዎች ለሕዝቡ ሊሰጡት የሚገባውን ጊዜ፣ በሌላ ነገር ላይ በማዋላቸው ምክንያት፥ የበደለኛነት ስሜት እየተሰማቸው ይመጣል። ራሳቸውን ከጭንቀትና ከውጥረት ነጻ ማድረግ ሲችሉ፥ ለሚያገለግሏቸው ሰዎች በቂ ጊዜና ፍቅር መስጠት ይችላሉ። ስለዚህ መንፈሳዊ መሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል። ከሚያገለግሏቸው ሰዎች ጋር አብሮ ለመሆን፥ ፍቅር ለማሳየትም ሆነ ለመቀበል፥ እንዲሁም ሌሎችን ሥራዎች በፕሮግራም ለመሥራት ጊዜውን በአግባቡ ማከፋፈል መቻል አለባቸው። የጊዜ አጠቃቀምንና በእነርሱ ኃላፊነት ሥር ያሉትን ነገር ማወቅ አገልግሎቱን በአግባቡ መፈጸም ያስችለዋል። መንፈሳዊ መሪዎች በአመራራቸው ጥሩ ውጤት ለማግኘት፣ ራሳቸውን አንዳንድ ጥያቄ መጠየቅ አለባቸው፥

*(1) አሁን ከምሠራቸው ሥራዎች ውስጥ ሌሎች ሊሠሩት የሚችሉት ሥራ አለ?*

*(2) አሁን ከምሠራቸው ሥራዎች ውስጥ "ተው አትሥራ" ብባል ልተወው የምፈልገው ሥራ የትኛው ነው?*

*(3) ስሠራው ደስ የማይለኝ፥ ተስፋ የሚያስቆርጠኝና ግፊት የሚሆንብኝ ሥራ የትኛው ነው?*

*(4) አሁን የምሠራው ሥራ ምን ያህል አስፈላጊ ነው?*

እነዚህንና እነዚህን ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መሪው ትክክለኛ መልስ ሲያገኝ፣ ለሥራው ቅደም ተከተል ለመስጠት፣ እንዲሁም "ሥራውን ሁሉ እኔ ብቻ ልሥራው" ከማለት መሥራት ለሚችሉት ሰዎች ሥራውን እንዲያከፋፍል ይረዳዋል። ይህ አሳብ ምዕራፍ 7 ላይ በሰፊው የገለጽን ስለሆነ፣ ምዕራፉን በጥንቃቄ ማንበብ ይጠቅማል።

## 4.3. አንዳንድ መሪዎች ለሰዎች ትዕግስት የላቸውም

አንዳንድ መሪዎች የሚያገለግሏቸውንና እንዲሁም አብረዋቸው የሚያገለግሉትን ሰዎች መታገስ የማይችሉበት ጊዜ አለ። ምንም ዓይነት ምክንያት ይሁን፥ መንፈሳዊ መሪ ትዕግስት የሌለው መሆን የለበትም። ትዕግስተ-ቢስነት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው የሚያሳየው ባሕሪ አይደለም። ትዕግስት የሌለውን መንፈሳዊ መሪ ሌሎች ሰዎች የሚመለከቱት ትዕግስት የሌለው ብቻ ሳይሆን፣ ፍቅር የሌው መሆኑን ጭምር ነው።

ትዕግስተ ቢስ መሆኑ በንግግሩም ሆነ በፊቱ ገጽታ ይታወቃል። ሲናገር መቸኮሉ፥ እን ዲሁም ሌላው ሰው እያነጋገረው እየደጋገመ በዓቱን ማየቱ አንደኛው ምልክቱ ነው። ይህን ሲያደርግ የሚያነጋግረውን ሰው "ለአንተ ጊዜ የለኝም፤ የምትናገረው ነገር ቁም ነገር የለውም" የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ መሆኑን የሚረዳው አይመስልም። በመቸኮሉ ምክንያት ሌላው እንዲሠራው የተመደበለትን ሥራ ራሱ ሲሠራው ይታያል። ይሄም ባህሪው ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እያሻከረው ይመጣል። አንዳንድ ጊዜ ለአንዳንድ ሰው ትዕግስት ማጣት የሚመስለው፥ ለሌላው ጥበበኛ መሆን ሊመስል ይችላል። እርግጥ ነው አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ጊዜ ማባከናቸውን የማይገነዘቡ አሉ። ለምሳሌ፣ ከመንፈሳዊ መሪው ቢሮ ሄደው ተዝናንተው በመቀመጥ፥ ትንሹንም ትልቁንም ነገር ማውራት የሚፈልጉ አሉ። የስንፍና ባህሪ ያለባቸውን አንዳንድ ሰዎች ከእነርሱ ጋር የሚኖረውን ጊዜ ለማሳጠር ዘዴ ቢጠቀሙ፥ ጥበበኞች እንጂ "ትዕግስት የሌላቸው" ሊባሉ አይገባም። መንፈሳዊ መሪዎች ጊዜ አጥኚዎችን ሰዎች በአግባቡ መያዝ የሚያስችል ጥበብ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። መንፈሳዊ መሪዎች፣ ትዕግስት በማጣት ምክንያት ብቻ ረጅም ጊዜ የሚጠይቀውን ነገር፥ "አሁን ይድረስ" በማለት አብረዋቸው ከሚያገለግሉት ሰዎች ጋር መቃቃር እንዳያደርስባቸው አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። እርግጥ ነው አንዳንድ ሰዎች ሰነፎችና "እሺ ነገ" የሚሉ ናቸው። መሪው የፍቅር ሰው ከሆነ፥ እንዲህ ዓይነት ባህሪ ያላቸውን ሰዎች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲፈጽሙ በጥንቃቄና በጥበብ እንዲያውቁት ማድረግ ያስፈልገዋል። አንዳንዶች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ባለመፈጸ ማቸው ምክንያት የበደለኛነት ስሜት ተሰምቷቸው ከነጭራሹ እንዳይሸሹ፥ መንፈሳዊው መሪ በፍቅርና በጥንቃቄ ሊይዛቸው ይገባል።

## 4.4. አንዳንድ መሪዎች በራሳቸው የመሪነት ችሎታ የማይተማመኑ ናቸው

አንዳንድ መሪዎች በአካባቢያቸው በትምህርትም ሆነ በችሎታ ከእነርሱ የተሻለ ሰው ካለ፣ በዚያ ሰው በመጠቀም ፈንታ፣ በቀላሉ ይበረግጋሉ ወይም ይፈራሉ። ይሄም የሚሆነው፥ መሪነታቸውን ሌላው ሰው ያልተቀበለው ስለሚመስላቸው ነው። እንዲሁም በመሪነት ሥፍራ የተቀመጠው ሰው፥ ከሚመራቸው ሰዎች የሚጠብቀውን ዓይነት ምሲጋና ካላገኘ፥ "መሪነቴን አልተቀበለውም ይሆናል" የሚል ፍርሃት ስለሚኖራቸው፥ ያንን ሰው መጠራጠርና መፍራት ይጀምራሉ። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ይህን የመሰለ ፍርሃትና ስጋት ስለሚኖራቸው ነው፥ ከሌላ ሥፍራ አገልጋይ የነበረ ወይም የቆየ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው ሲመጣ፥ በፍቅር በመቀበል ፈንታ በተለያየ መንገድ ገፍተው ሲያስወጡት የሚሞከሩት። ይህን ዓይነቱ ስሜት በምንም ዓይነት



ምክንያት ይምጣ፥ ሁኔታው የሚያሳየው መንፈሳዊ መሪው (መጋቢው) የፍቅር ሰው አለመሆኑ ነው። በራሳቸው የመሪነት ችሎታ የማይተማመኑ መሪዎች፥ ከብዙዎች ጋር በቀላሉ ይጋጫሉ። "ያ ሰው ከእኔ የተሻለ ስለሆነ አንድ ቀን ሥፍራዬን ይወስድ ይሆናል" ብለው ስለሚፈሩና ስለሚሰጉ፥ ምንም ዓይነት በጎ ሥራ ቢሠራ ያንን ሰው ምክንያት ፈልገው ሲነቅፉት ይታያሉ። በራሱ የመሪነት ችሎታ የማይተማመን መሪ ይህ ችግር እንዳለበት የሚታወቀው፥ ሁልጊዜ ምክንያት እየፈለገ ሲነቅፍ፥ ሌሎች ሲያመሰግኑት ቅር የሚለው፥ ሌላውን ማድነቅና ማመስገን የማይሆንለት ሲሆን ነው። ሌሎችን የሚነቅፈው፥ ነቀፋው ትክክል ሆኖ ሳይሆን፥ የራሱን ደረጃ ለማጠናከር፥ ራሱን ከፍ አድርጎ ለማሳየት ሲል ዘዴ አድርጎ መጠቀሙ ነው። ይሁን እንጂ፥ ሌላውን በመጉዳት ፈንታ የተኮሰው ጥይት ተፈናጥሮ ራሱን ሲጎዳው ይታያል።

## 4.5. አንዳንድ መሪዎች "ሰዎች ምን ይሉኛል?" በማለት ይሰጋሉ

አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች የአገልግሎታቸውን ውጤት የሚመዝኑት ሰዎች በሚሰጡት አስተያየት በመሆኑ፥ ሰዎች ስለሚሰጡት አስተያየት ከመጠን በላይ ይጨነቃሉ። መንፈሳዊ መሪ ወይም መጋቢ መጀመሪያ ተጠያቂነቱ ለእግዚአብሔር እንደሆነ ማወቅ አለበት። ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል ከሆኑ፥ ሰዎች ስለሚሰጡት አስተያየት ይህን ያህል ሊጨነቁ አይገባም። የክርስቶስን ፍቅር ለሌሎች ማካፈላቸው ብቻ፥ ያ ልዩ ጉልበትና ኃይል ሊሆንላቸው ይገባል። መርሳት የሌለባቸው ምንም ያህል ጥሩ ቢሰሩ፥ በአንድም ሆነ በሌላ ምን ጊዜም ቢሆን የሚነቅፏቸው ሰዎች የሚኖሩ መሆናቸውን ነው። ሌሎች ለሚሰጡት አስተያየት የሚጨነቁ መጋቢዎች ወይም መንፈሳዊ መሪዎች፥ ስለ እነርሱ ጥሩ አስተያየት የላቸውም ብለው የሚያስቧቸውን መቀበልና ማፍቀር አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። ከላይ እንደገለጽነው ፍቅር የሌለበት አገልግሎት ምን ጊዜም ቢሆን በጌታ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። አገልጋዩም ደስ ብሎት ለረጅም ጊዜ አገልግሎቱን መቀጠል አይችልም። በሚሰጠው አገልግሎቱ እንደ ሞተር ሆኖ የሚያንቀሳቅሰው፣ ለጌ ታና እንዲሁም ለሚያገለግላቸው ሰዎች ያለው ፍቅር ነው። "ሌሎች ስለ እኔ ጥሩ ነገር አያስቡም" በማለት ፍቅር መስጠትም ሆነ መቀበል የማይሆንላቸው መንፈሳዊ መሪዎች በአገልግሎታቸው ፍሬያማ እንደማይሆኑ የታወቀ ነው።

## 5. መንፈሳዊ መሪ "ፍቅርን" መለማመድ ይገባዋል

መንፈሳዊ መሪ፣ የሚያገለግላቸውን ሰዎች ማፍቀር ተቀዳሚ ኃላፊነቱ ነው። በፍቅር የተሞላ አገልጋይ ለፈተናና በችግር ወቅት ደራሽ ነው። ግድ የሚለውም ሌላ ነገር ሳይሆን ፍቅር ነው። እውነተኛ ፍቅር ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አይደለም። ደስ

ሲለውና ሲሰማው ብቻ ሳይሆን፣ ሁልጊዜ ያፈቅራል። የፍቅር ሰው ለሌሎች ፍቅርን የሚሰጠው፣ ችግራቸውና እጦታቸው በስሚታየው ነው። ሌላው ሲቸገር እያዩ ዝም ማለት ፈጽሞ አይችሉም። ዮሐንስ *"ነው በዚህ ዓለም ሀብት ኢያለው ችግረኛውን ሲራብ ቢያራራለት እግዚአብሔርን እወዳለሁ' ማለት እንዴት ይችላል?"* (1 ዮሐ. 3፥17) ብሎ ይጠይቃል። መንፈሳዊ መሪ በፍቅር ሰጪነቱ የሚታመን መሆን አለበት። መንፈሳዊ መሪ አገልግሎቱን እንደሚገባው መፈጸም የሚችለው፣ መለኮታዊ ኃይል ሲያገኝ፣ በፍቅር የተሞላ ልብ ኖሮት ለእግዚአብሔር ክብር የሚያገለግለውን ሰው ፍላጎት ማሟላት ሲችል ነው። አገልጋይ አገልግሎቱን እንደሚገባው መፈጸም የሚያስችለው ምክንያት፤ ክርስቶስ ለእርሱ ያለው ፍቅር፣ እንዲሁም እርሱ ለክርስቶስ ያለው ፍቅር ነው። ይህ ካልሆነ ግን፣ የሰውን ፍላጎት ማሟላትና እንዲሁም አገልግሎቱን ለእግዚአብሔር ክብር ሊያውል አይችልም። ጳውሎስ እንዲያገለግል የሚገፋፋው ምን እንደሆነ ሲገልጽ፣ *"...የክርስቶስ ፍቅር ለሥራ ይገፋፋናል"* ይላል (2 ቆሮ. 5፥14)። መንፈሳዊ መሪ፤ መለኮታዊ ኃይል የሚተላለፍበት መሣሪያ ወይም ዕቃ ነው። ይህን ስንል፣ ግዑዝ፣ የራሱ ፈቃድ የሌለው ነው ማለታችን አይደለም። አገልጋዩ በሚሠራው ሥራ እርሱ ራሱ እርካታን ወይም በረከትን የማያገኝ ከሆነ፣ አንድ ልክ ያልሆነ ነገር በአገልግሎቱ ውስጥ አለ ማለት ነው። መንፈሳዊ መሪ በአገልግሎቱ ትልቅ ኃላፊነት ያለበት ሰው ቢሆንም፤ እግዚአብሔርን ማገልገሉ ቅጣት ሳይሆን፣ መንፈሳዊ በረከትና እርካታን የሚያገኝበት እንደ ሆነ መዘንጋት የለበትም።

እግዚአብሔርን ማገልገል፤ ከሰው ሕይወት ጋር የተያያዘ ነው። ሰዎች ብዙ ችግር ያለባቸው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ፍላጎታቸውን ለሟሟላት የሚወስዱት ምርጫና እርምጃ አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪዎች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ሌሎች ሰዎች እንዳይቀርቧቸው በራሳቸው ዙሪያ የሚያጥሩት፤ በሌላው ሰው ዓይን የማይታይ የራሳቸው የሆነ አጥር አላቸው። አገልጋዩ እንደነዚህ ዓይነቶቹን መውደድ ካልቻለ፤ እንደሚገባው ሊያገለግላቸው ፈጽሞ አይችልም። መንፈሳዊ መሪ በሚያገለግላቸው ሰዎች ጉድለት አማካኝነት የራሱን ፍላጎት ለማሟላት ወይም መጠቀሚያ ለማድረግ ምንም ዓይነት ዝንባሌ ሊኖረው አይገባም። መንፈሳዊ መሪ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሌሎች የሚያስተላልፍ መሣሪያ ወይም ዕቃ መሆኑን ምንጊዜም ቢሆን መዘንጋት የለበትም። መንፈሳዊ መሪ፣ ከሚያገለግላቸው ሰዎች ባሳነሰ ሁኔታ የእግዚአብሔር "ጸጋ" እንደሚያስፈልገው ካላወቀ፤ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሌሎች እንዴት ማስተላለፍ ይችላል? ብዙዎቻችን ክርስቶስ ሰዎችን የሚወድውን ያህል የመውደድ አቅምም ሆነ ችሎታው የለንም። 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13ን በሕይወታችን ስመለማመድ እንሞክራል። ይሁን እንጂ፣ እንደተጻፈው ስመኖር ብዙ ድካም አለብን። ይሁን እንጂ፤ በሚያስፈልገን ጊዜ እግዚአብሔር በውስጣችን ፍቅሩን ስለሚያፈስልን፣ በራሳችን ጥረትና ጉልበት ሁልጊዜ በፍቅር የተሞላን እንድንሆን አይጠብቅብንም። የእግዚአብሔር ፍቅር በሰዎች ልብ እንዴት እንደሚፈጠር ሐዋርያው ጳው



ሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች በጻፈው መልዕክቱ *"በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋው አያሳፍርም"* ይላል (ሮሜ 5፥5)።

መንፈሳዊ መሪ በአገልግሎቱ ውስጥ የሚያስፈልገው "ፍቅር" ከራሱ የሚገኝ፣ ወይም ከተፈጥሮ ችሎታ የሚሆን ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ራሱ የሚሰጠው ነው። የምናገለግላቸው ሰዎች ተስፋ ሲያስቆርጡን፣ ወይም ሲያበሳጩን፣ ብዙ ጊዜ የምናደርገው ለእነርሱ መጸለይና እንዲሁም እንዲለውጣቸው እግዚአብሔርን መጠየቅ ነው። መሆን ያለበት ግን እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለን ፍቅር እንዲጨምር መጸለይ ነው። ይህን ካላደረግን ግን ለጠላታችን መግቢያ እንዲሆን የልባችንን በር መክፈታችን ይሆናል። እግዚአብሔር የሚፈልገው፣ "ሥራው እንዲሠራለት" ብቻ አይደለም። ከሥራው የበለጠ ለሠራተኛው ግድ ይለዋል። እግዚአብሔር የሚፈልገው ሥራው እንዲሠራለት ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ ከሰው በተሻለ ሁኔታ ሊሠሩ የሚችሉትን መላእክትን ይልክ ነበር። እግዚአብሔር በእኛ አማካኝነት ሥራው እንዲሠራለት ብቻ አይደለም። እኛም በምንሠራው ሥራ በረከት እንድናገኝ፣ መንፈሳዊ ዕድገት እንዲኖረን ይፈልጋል። ለዚህ ነው በአገልግሎታችን አልፎ አልፎ አንዳንድ ዕንቅፋቶች እንዲያጋጥመን የሚፈቅደው። በችግሮቻችንም ውስጥ እንድንጸልይ ሲያነቃቃን፣ በቃሉ እንድንተማመን፣ ለፍቅሩና ለጸጋው በመንፈስ ቅዱስ እንድንተማመን ነው። ማደግ እንድንችልና እንዲሁም ክርስቶስን እንድንመስል መንፈስ ቅዱስ አስቸጋሪ ሰዎችና አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚጠቀምበት ጊዜ አለ። ይሁን እንጂ፣ ብዙዎቻችን ብዙ ጊዜ ለዕድገታችን ምክንያት እንዲሆን በመፍቀድ ፈንታ፣ ከችግራችን እንድንወጣ እንጸልያለን። *"ከዚህ ውስጥ ለዕድገቴ የሚሆን ምን አገኝበታለሁ"* ብለን በመጠየቅ ፈንታ *"ከዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ የምወጣው እንዴትና መቼ ነው?"* ብለን እንጠይቃለን። ይህን ስናደርግ፣ ለመንፈሳዊ ዕድገት የሚጠቅመንን ነገር እንስታለን።

አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ ሰዎችና ሁኔታዎች ሲያጋጥሙን፣ ከአገልግሎታችን ሸሽተን ስመሄድ ወይም ከአገልግሎት ለመውጣት እንፈልጋለን። ይህን ስናደርግ በሕይወታችን ትልቅ ስህተት እንሠራለን። *"ከዚህ አገልግሎት እወጣለሁ... ከእከሌ ጋር ማገልገል አልፈልግም... ከዚህ ቤተ ክርስቲያን መውጣት አለብኝ..."* ማለቱ ችግራችንን አያቃልለውም፤ ወይም የልባችንን ፍላጎት አይሟላም። አገልግሎት ብንለውጥ፣ ቤተ ክርስቲያን ብንቀይር፣ በሌላ ጊዜም ሆነ በሌላ ሥፍራ ተመሳሳይ ችግር ሊያጋጥመን እንደሚችል መዘንጋት የለብንም። እግዚአብሔር አገልጋዮቹ በምንም ዓይነት ከተሰጣቸው ኃላፊነት ሸሽተው እንዲሄዱ አይፈልግም። ልጆቹ ክርስቶስን እንዲመስሉ ስለሚፈልግ፣ ያ ውበት በሕይወታቸው እስኪቀረጽ ድረስ፣ ዓላማው እስኪፈጸም ድረስ መሥራቱ አይቀርም (ሮሜ 8፥29)። ችግር ሲያጋጥም መሸሽ የሰው ሁሉ የተፈጥሮ ባሕሪ ስለሆነ፤ ብዙዎች ከተጠሩበት አገልግሎት ለመሸሽ ሞክረዋል። ሙሴን እስራኤላውያን ብዙ ጊዜ ስላስመረሩት ሞትን የተመኘበት ጊዜ ነበር (ዘሁልቁ 11፥10-15)። ኤልያስም ተስፋ የቆረጠበትና ሞትን የተመኘበት ወቅት ነበር (1ኛ ነገ. 19)። መንፈሳዊ መሪዎች፤ አስቸጋሪ ሰዎችና

አስቸጋሪ ሁኔታዎች በሚዱበት ሥፍራ ሁልጊዜ ሊያጋጥማቸው ይችላልና በአዕምሯቸው "ይደርስብኛል" ብለው መጠበቅና እንዲሁም እግዚአብሔር ለጥቅማቸው እንዲያውለው መፍቀድና ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው። ሰይጣን አስቸጋሪ ሰዎችን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ከአገልግሎታቸው ሊያስወጣቸው ሲሞክር፥ መንፈስ ቅዱስ ግን እነዚሁኑ መጥፎ ሰዎችንና ሁኔታዎችን በመጠቀም በሕይወታቸው እንዲያድጉበት እንደ መሣሪያ ይጠቀምበታል። እንግዲህ ምርጫው የራሳቸው ነው። ጳውሎስ *"የምሕረት አባትና የመጽናናት ሁሉ አምላክ ለሆነውና እንዲሁም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ለሆነው አምላክ ምስጋና ይሁን። እኛ ከእግዚአብሔር በምናገኘው መጽናናት በመከራ ላይ ያሉትን ሁሉ ማጽናናት እንድንችል፥ እግዚአብሔር እኛን በመከራችን ሁሉ ያጽናናል"* (2 ቆር. 1፥3-4) ይላል።

## 6. መንፈሳዊ መሪ በሕይወቱ ያለው ፍቅር በሚያደርገው ተግባር ይመዘናል

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፍቅራቸውን በተግባር ገልጸው ያሳዩ፣ ጥሩ ምሳሌዎች የሚሆኑን ብዙ ሰዎች አሉ። ከብዙዎቹ መካከል የሁለቱን ብቻ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

### 6.1. ማርያም መቅደላዊት ፍቅሯን የምትገልጽበት መንገድ አገኘች

ማርያም ብዙ ገንዘብ አውጥታ በጣም ውድ የሆነ የአልባስጥሮስ ሽቶ ገዝታ፥ ብልቃጡን ሰብራ ሽቶውን በሙሉ በክርስቶስ ራስ ላይ አፈሰሰችው። ይህን ስታደርግ ምን ተሰምቷት እንደሆነ አላውቅም። ማርያም "ለኢየሱስ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ" ብላ ምን ያህል ጊዜ እንዳሰበች አይታወቅም፤ በልቧ ውስጥ ግን ፍቅሩ እንደሚነድ እርግጠኞች ነን። ያ ውድ የሆነ የአልባስጥሮስ ሽቶ ሦስት መቶ ዲናር ያህል የሚያወጣ ነበር። ያ ሦስት መቶ ዲናር በዘመኑ ገንዘብ ቢተመን እጅግ በጣም ብዙ ብር እንደሚሆን እንገምታለን። ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ ካደረገላት ውለታ ጋር ስታስተያየው፣ እንኳን ሊበዛበት በጣም እንደሚያንስበት በልቧ ታውቃለች። ማርያም የአልባስጥሮስ ሽቶ በውድ ዋጋ ገዝታ በኢየሱስ እግር ላይ ያፈሰሰችው ላገኘችው "ይቅርታ" ዋጋ ለመክፈል፣ ወይም ብድር ለመመለስ ሳይሆን፣ ፍቅሯን ለመግለጽ ብቻ ነው። ሙሉ ነጻነቷን ለሰጣት ጌታ፣ በልቧ ውስጥ ለሚነደው ፍቅር ዓይነተኛ መግለጫ ሆኖላታል። በድርጊቷ ትርፏን እንጂ፥ ኪሣራዋን አላሰበችም። *"ብዙ ዋጋ ያወጣሁበት ስለሆነ ብዙ ቀዳዳ ይሸፍንልኛል"* ብላ ይህን በማድረጓ አልተጸጸተችም።

አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ጌታን በማገልገላቸው ምክንያት የደረሰባቸውን መከራ፣ እንዲሁም ጉድለታቸውን ይቆጥራሉ። ጥቂት በጎ ያልሆነ ነገር ሲደርስባቸው፣



የሚያገለግሉትን ጌታ ባለ ዕዳ ሊያደርጉት ይከጅላሉ። ጌታውንና እርሱ የወደዳቸውን የሚወድ እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ መሪ፣ የሠራውን እየቆጠረ "ይህን ያህል ዓመት አገልግዬህ፣ ይህን ያህል ሠርቼልህ ችግር ሲደርስብኝ እንዴት ዝም አልከኝ" አይሉትም። ብዙ ዓመት ቢያገለግሉም፣ "ዘመኔ እንዲሁ ተቃጠለ... የትምህርት ጓደኞቼ ሀብታሞች ናቸው፣ እኔ ግን ምንም የለኝም" በማለት አያጉረመርሙም። ጌታን በማገልገል ያሳለፉትን ጊዜ እንደ ኪሳራ ሳይሆን እንደ ትልቅ ትርፍ አድርገው ይቆጥሩታል። ፍቅሩ ግድ ብሏቸው ጌታን በማገልገላቸው ምክንያት "ጎደለብኝ... አነሰኝ..." አይሉም። ማርያም ብዙ አማራጮች ነበሯት፥

(1) ሽቶውን የገዛችበትን ገንዘብ ጥቂቱን ለድሆች ሰጥታ ብዙውን ለራሷ የሚጠቅማትን ነገር ልታደርግበት፥

(2) ገንዘቡን ወደፊት መጠሪያ እንዲሆናት ልታስቀምጠው፥

(3) በገንዘቡ ጌጣ ጌጥ ገዝታ ልታጌጥበት ትችል ነበር። ማርያም ግን ይህን አላደረገችም።

እንደ ማርያም ጊዜያቸውን፥ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን በራሳቸው ላይ በማጥፋት ፈንታ፥ የራሳቸውን ፍላጎት ትተው በመስዋዕትነት ለጌታ የሚሰጡ፥ ለሚያገለግሉት ጌታ እውነተኛ ፍቅር ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። ታሪካቸው እንደ ማርያም በመጽሐፍ ተጽፎ ሰው ባያውቃቸውም፣ ጥሩምባ ባይነፋም፣ ጌታ ኢየሱስ ግን ያውቃቸዋል። አንድ ጊዜ አንዲት ክርስቲያን እናት፥ ልጇ ሚስዮናዊ ሆና ለመሄድ በምትዘጋጅበት ወቅት፣ ድንገት በካንሰር በሽታ ተያዘች። ይህንን ስታውቅ "እኔን ጥበሽ... አስታመሽ ሳትቀብሪኝ የትም መሄድ የለብሽም" በማለት ፈንታ፥ ጌታዋን እንድታገለግል አሰናበተቻት። ይሄም ለጌታዋ ያላትን ፍቅር ይገልጻል።

ማርያም ያደረገችው የፍቅር መግለጫ በሌሎች ዓይን ሲታይ፥ *"ቅብጠት... ብኩንነት... ያለአግባብ ገንዘብ ማባከን... ሌላ የተሻለ ነገር ሊሠራበት ሲገባ... ገንዘቡ አጉል ቦታ ያዋለችው..."* ሊመስል ይችላል። ማርያም ለኢየሱስ በስጦታዋ ፍቅሯን በመግለጿ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስቆጣ እናውቃለን። *"እዚያ ከነበሩት አንዳንዶቹ በድርጊቱ ተቆጥተው 'ይህ ሽቶ በከንቱ መባከኑ ለምንድን ነው? ይህ ሽቶ ከሦስት መቶ ብር በላይ ተሸጦ ገንዘቡ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበር እኮ' ተባባሉ፤ ሴቲቱንም ነቀፏት"* (ማር. 14፥4-5) ይላል። ማርያም ይህን የመሰለ ነቀፋ ስትሰማ ምን ተሰምቷት ይሆን? ደቀ መዛሙርቱ በወቅቱ ትኩረት ያደረጉት፣ በትርፍና በኪሳራ ላይ ነው። ማርያም ግን ንጹህ ፍቅሯን ለኢየሱስ የገለጸችበት ዕድል ያገኘች መሆኗን ነው። "ሽቶ ራሱን ለመቀባት ከፈለገች፥ ሁሉንም አንዴ በመድፋት ፋንታ ጥቂት ጠብታ ለምን አልበቃትም?" እንል ይሆን? ማርያም ለእርሱ ያላት ፍቅር ጠብታ ሳይሆን፣ የተትረፈረፈ መሆኑን የሚገልጽ

ነው። ዛሬ በፍቅር ተነሳስተን ለምናደርጋቸው ነገሮች ዳር ቆመው የሚተቹን አሉ። ለእኛ ያሰቡና የተቆረቆሩ መስለው፣ *"እሁንስ አበዛኸው... በመጠኑ ለምን አታገለግልም... ሌሎች አገልጋዮችን ለምን አታይም... ራስህን ለምን ትጥላለህ?.."* የሚሉን አይጠፉም። ለማርያም ሌላ አገልግሎት ሲመሠርቱላት ሲቃጣቸው እናያለን። "ሽቶው ለምን በከንቱ ይባክናል? ከሦስት መቶ ዲናር በላይ ተሸጦ፣ ገንዘቡ ለድኾች መሰጠት ይቻል ነበር" (የማር. 14፥8) ሲሉ፣ *"...የድሆች ሚኒስትሬ... ለምን አታቋቁሚም?"* የሚሏት ይመስላሉ። ለክርስቶስ ሦስት መቶ ዲናር ይበዛበት ይሆን?

- *እንግሊዛዊው ሄንሪ ማርቲን ከታወቀው ካምቢሪጅ ዩኒቨርሲቲ በማቲማቲክስ በከፍተኛ ውጤት የተመረቀው፥ በዓለም ላይ ተደናቂ ይሆናል ተብሎ የተጠበቀ ሰው ነበር። በዓለም ላይ ያለውን ክብርና ማዕረግ አርግፎ አድርጎ በመተው "ሩቅ ምሥራቅ" ሚሲዮናዊ ሆኖ ሲያገለግል፥ "ያንን የመሰለ ጭንቅላት ይዞ እንዴት ሚሲዮናዊ ይሆናል... ያለአግባብ አንጎሉ ባከነ.." ያሉ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ፥ ሚስዮናዊ ሆኖ በሄደ በሰባት ዓመት ውስጥ በሦስት ቋንቋዎች አዲስ ኪዳንን ተርጉሞ ሕዝቡ በራሱ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖረው አደረገ።*
- ***ዊሊያም** ቦርደን፥ በውርስ ሊያገኝ የሚችለውን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ትቶ፥ ወንጌልን ለእስላሞች ለመስበክ፥ ሚስዮናዊ ሆኖ ሄደ። የሚያሳዝነው ካሰበበት አገር ሳይደርስ መንገድ ላይ ሞተ። ለብዙዎች "...ሕይወቱ ያለአግባብ የባከነ..." ሊመስላቸው ይችላል። ይሁን እንጂ፥ በእርሱ ምክንያት ተቀስቅሰው ብዙዎች ሚስዮናውያን ሆኑ።*

እኔና እናንተ ዛሬ በአገልግሎታችን ሙሉ በሙሉ፥ አንድም ነገር ሳናስቀር ያለንን ለእርሱ እንሰጠዋለን? ወይስ የሚያስከፍለንን ዋጋ ቁጭ ብለን እንተምናለን? ሕይወቱን ለሰጠን ጌታ፣ እኛ የምንሰጠው አገልግሎት ያንስበታል እንጂ አይበዛበትም። ደቀ መዛሙርቱ ማርያምን እንደ ገሰጿት፥ ኢየሱስም እነርሱን በኃይል ገሰጻቸው። ***"ተዉአት ስለምን ታስጨንቋታላችሁ? እርሷ ለእኔ መልካም ነገር አደረገችኝ.."*** አላቸው (የማር. 14፥6)። ማርያም ለኢየሱስ ይህን የመሰለ ስጦታ ያደረገችለት፣ ከምንጊዜም የበለጠ ከጎኑ የሚቆሙ፣ ፍቅራቸውን የሚገልጹለት ሰዎች በሚያስፈልገው ትክክለኛው ወቅት ነበር። የሃይማኖት መሪዎች ሊገድሉት በሚመካከሩበት ክፉ ጊዜ ነበር። እኔና እናንተ ገንዘብ በተረፈን ጊዜ፥ ሁሉ ነገር ልክ ሲመጣልን፥ ለንሽም ብዙ ጠያቂዎች አሉን። በመከራ ስንከበብ ግን ከአጠገባችን ብዙዎች ይሸሻሉ። በችግራችን ጊዜ የረዱንን፣ አጠገባችን ሆነው ያጽናኑንን፣ ጥቂቶችም ቢሆኑ ፈጽሞ አንረሳቸውም። ማርያም ለፍቅሯ መግለጫ የምትችለውን ስላደረገች ኢየሱስ አደነቃት። ***"እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በሚሰበክበት በማንኛውም ስፍራ እርሷ ያደረገችው መታሰቢያ ሆኖ ይነገርላታል"*** (ማር. 14፥9) በማለት ባለታሪክ አደረጋት።



## 6.2. ዳዊት ለአምላኩና ለሕዝቡ ልዩ ፍቅር ነበረው

ዳዊት ብዙ ድካም የነበረበት ሰው ይሁን እንጂ፥ ከበግ እረኛነት አውጥቶ ንጉሥ አድርጎ የቀባውን ጌታ እጅግ በጣም ይወደው እንደነበረ እናውቃለን። የሥጋ ድካሙን፥ ይኸውም በድብቅ ከሰው ሚስት ጋር ማመንዘሩ፣ ሥልጣኑን መከታ አድርጎ ባሏን አስገ ድሎ የሰው ሚስት መውሰዱ በእኛ ግምት ይቅርታ የማያሰጥ ወንጀል ነው እንላለን። እግ ዚአብሔር ግን ለዚህ ሁሉ በደሉና ወንጀሉ ይቅርታ መስጠቱ ብቻ ሳይሆን፥ ደካማነቱን እያወቀ ከነበረበት የክብር ሥፍራ ያላወረደው በመሆኑ የይቅርታው ስፋት፣ የጸጋው ብዛት ያስደንቀናል። ዳዊት እውነተኛ እረኛ የሆነውን እግዚአብሔር እያደነቀ ብዙ መዝ ሙሮችን አውጥቶ ዘምሯል። ከመዝሙሮቹ አንደኛው፣ ከአምላኩ ጋር ያለውን ቅርበት የሚያሳይ፣ መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 23 ላይ *"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝ ምንም የለም"* ሲል የዘመረው፥ ለጌታው ያለውን ፍቅር የገለጸበት መዝሙር ነው። ዳዊት ሕዝቡን እንዲመራ በአደራ ከእግዚአብሔር መቀበሉን ያምናል። ሕዝቡ የእግዚአብሔር መሆኑን ስላወቀ፥ ያያቸው የነበረውም እግዚአብሔር በሚያያቸው ዓይን ነበር። በአንድ ወቅት ዳዊት እንደ ልማዱ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ኃጢአት በመሥራቱ በሕዝቡ ላይ እግዚአብሔር መቅሰፍት አምጥቶ 70 ሺ እስራኤላውያን አለቁ። ዳዊት ለሕዝቡ ልዩ ፍቅር ስለነበረው ልቡ በሀዘን ተሞልቶ፥

> *"በደል የፈጸምሁት እኔ ነኝ፤ እኔም ራሴ ክፉ ነገርን አደረግሁ፤ ታዲያ ይህ ምስኪን ሕዝብ ምን በደለህ? ይህ መቅሰፍት በእነርሱ ላይ ከሚወርድ ይልቅ በእኔና በቤተሰቤ ላይ ይሁን ሲል ጠየቀ"* (2 ሳሙ. 24፥17)።

እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ የሚመራቸው (የሚያገለግላቸው) ሕዝብ በመከራ ውስጥ ሲያልፉ፥ ስሜቱን ለመግለጽ አይፈራም። ከራሱ ሕይወት ይልቅ ለሚመራቸው ሕዝቦች ደህንነት የበለጠ ይጨነቃል። እውነተኛ መሪ ለሕዝቡ የሚራራ ልብ ያለው ነው።

ፍቅር የሌለበት አገልግሎት መስጠት ይቻላል? አገልግሎቱ እግዚአብሔርን የሚያ ከብር፣ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም እንጂ፣ አዎን! ያለፍቅር ማገልገል ይቻ ላል። የአገልግሎት መሠረቱ "ፍቅር" ቢሆንም፥ እግዚአብሔርንና የሚያገለግሉትን ሕዝብ ሳያፈቅሩ፥ እንዲሁ የሚያገለግሉ መንፈሳዊ መሪዎች ጥንት ብቻ ሳይሆን፥ ዛሬም አሉ። ለምናገለግለው ሕዝብ ፍቅር ሊኖረን የሚችለው እንዲሁ ባይሆን፥ ፍቅር በሆነው ጌታ ሕይወታችን ሲሞላ ነው። ፍቅር ከሌለን "ፍቅር" የሆነውን ጌታ ልንወክለው አንችልም። ጌታን ያለፍቅር ለማገልገል ከሞከሩት ሰዎች መካከል ጎልቶ የሚታየው ዮናስ ነው። ያለፍቅር ማገልገል ሁልጊዜ አድካሚና አሰልቺ ሲሆን፥ ፍቅር የሌላቸው አገልጋዮቹ አገልግሎታቸውን የሚያዩት እንደ ሸክም ነው። ዮናስ ወደ ነነዌ ሄዶ ሕዝቡን ወደ ንስሀ እንዲጠራ እግዚአብሔር ሲልከው፥ ለጌታውና ለነነዌ ሕዝቡ ፍቅር ስላልነበረው፣ ከጠ ራው ጌታ ለመሸሽ ሞከረ። እግዚአብሔር ማንንም በግድ አገልግሉኝ የሚል አምላክ

ባይሆንም፥ ለዮናስ ሁለተኛ ዕድል ለምን እንደሰጠው ግን አይገባንም። ለሁለተኛ ጊዜ ለሕዝቡ እንዲሰብክ ሲላክ፥ "እምቢ" ቢል የሚደርስበትን ቅጣት ስለፈራ ብቻ አድርግ የተባለውን ያደረገ ይመስላል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ልዩ ፍቅርና ርህራሄ ስለ ነበረው፥ አመጸኛ በነበረው በዮናስ ተጠቅሞ የሚወደውን ሕዝቡን ከጥፋት አዳነ። የእግዚአብሔር ዓላማ ምንጊዜም ፍቅር በሌላቸው መንፈሳዊ መሪዎች አይጨናገፍም። የተጠራው ሰው "እምቢ!" ቢል፣ እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም ሌላ ሰው አስነስቶ ይልካል እንጂ፣ ዓላማው ሳይፈጸም አይቀርም። ዛሬም ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሚያገለግሉት ሕዝብ ፍቅር የሌላቸው ብዙ መንፈሳዊ መሪዎች አሉ። ቸልተኞችና ሰልቺዎች ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሲል ብቻ ይሠራል። ያ ሊደንቀን ይችል ይሆናል። ዮናስ የነነዌ ሕዝብ መዳናቸውን ስላልፈለገ፣ ለእነርሱ መስበክ አስፈላጊ መስሎ አልታየውም ነበር። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ለነነዌ ሕዝብ የነበረው ፍቅር፣ ከዮናስ እምቢታ የበለጠ ኃይል ነበረው። ጌታም ልባቸውን ስላለሰለሰው ሕዝቡ በንስሀ ስለተመለሰ፣ ከጥፋት አዳናቸው። ይሄም ዮናስን አስቆጣው። ዮናስ አገልግሎቱ በፍቅር የተሞላ ስላልነበረ፥ ውሃ ቀጠነ እያለ ይነጫነጭና ያጉረመርም ነበር። ዛሬም እንደ ዮናስ ያለፍቅር እያጉረመረሙ፣ ደስታ የሸሻቸው ሆነው የሚያገለግሉ ብዙ መንፈሳዊ መሪዎች አሉ።

ኢየሱስ "ስለ ኮብላዩ ልጅ" በምሳሌ የተናገረው፣ የኮብላዩ ልጅ ታላቅ ወንድም በአባቱ ቤት እንደ ዮናስ ያለፍቅር የሚያገለግል ሰው ነበር። እርግጥ ነው ያ የኮብላዩ ልጅ ታላቅ ወንድም ከአባቱ ጋር ብዙ ዓመት፣ እርሱ ራሱ እንደ ገለጸው በታማኝነት አገልግሏል። ግን "ግዴታዬ ነው!" ብሎ እንጂ በፍቅር ተነሳስቶ ያደረገው አይመስልም። ከአባቱ ጋር ይሥራ እንጂ፥ አባቱ የነበረውን ዓይነት ፍቅር አልነበረውም። የጠፋው ልጅ አባቱን ሲያሳስበው፥ ወንድምየውን ግን አሳስቦውም ነበር። በመጥፋቱ "ዕዳ ቀለለ" ያለ ይመስላል። ኮብላዩ ልጅ ከጠፋበት ሲመለስ አባትየውን ደስ ሲያሰኘው፥ ወንድምየውን ግን አስቆጣው፤ አስከረፈው። "እቤት አልገባም" እንዲል አደረገው። ከግብግቡ ሸሸ። ዛሬም ቢሆን ሌላው ሲባረክ፣ ሌላው ሲመሰገን በቀላሉ የሚቆጡና የሚያኮርፉ መንፈሳዊ መሪዎች በየቤተ ክርስቲያኑ ብዙ አሉ። እነርሱ እንደሚፈልጉት ካልሆነላቸው፥ "ለምን እኔ በምፈልገው ዓይነት አልሄደም?" ብለው የሚያኮርፉ… ተንኮል የሚሸርቡ መንፈሳዊ መሪዎች መኖራቸው ይታወቃል።

ፍቅር የሌላቸው አገልጋዮች ሕዝቡን መጠቀሚያ ያደርጉታል። ሕዝቡን በመጠበቅ ፈንታ ራሳቸውን ይጠብቃሉ፥

*(1) ወተቱን ይጠጣሉ፥ ከጠጉራቸው የተሠራውን ሱፍ ይለብሳሉ፥*

*(2) የሰባውን አርደው ይበላሉ፥*

*(3) በጎችን በማሠማራት አይጠብቁም፥*

*(4) ለደከሙት እንክብካቤ አያደርጉም፥*



*(5) የታመሙትን አያድኑም፥*

*(6) የተሰበሩትን አይጠግኑም፥*

*(7) የባዘኑትን አይመልሱም፥*

*(8) የጠፉትን አይፈልጉም፥*

*(9) አጠገባቸው ያሉትን በግፍና በጭካኔ ገዚቸው* (ሕዝ. 34፥2-5)።

እርግጥ ነው አንዳንድ ሰዎችን መውደድ ከባድ ነው። ይህን የተረዳው ጌታ የማይወደዱትን የምንወድበትን ልዩ ኃይል፥ ጉልበትና መንገድ ይሰጠናል። ሰውን መውደድ ማለት የውሸት ፈገግታ ማሳየት ማለት አይደለም። መውደድ ለሌሎች የምናደርግላቸውን ጥቃቅን ነገሮችን ሁሉ ያካትታል። ልባችን በእግዚአብሔር ፍቅር ሲሞላ፥ እኛም በፍቅር የተሞላን ስለምንሆን፥ እውነት ያልሆነ ወይም የማስመሰል ፈገግታ ማሳየት አያስፈልገንም። መንፈሳዊ መሪ ለሕዝቡ እውነተኛ ፍቅር እንዲኖረው፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር እርሱ ራሱ በሕይወቱ መለማመድ አለበት። ሐዋርያው ዮሐንስ *"እግዚአብሔር ፍቅር ነው"* ይላል (1 ዮሐ. 4፥8)። ስለሆነም ፍቅር የሚመነጨው ከእርሱ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ስሜታዊ ብቻ አይደለም፤ የሰዎች ፍቅር ሲያልቅና ሲቀዘቅዝ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ግን በመልካም ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመከራም፣ በችግርም ጊዜ ዘላቂነት ያለው ነው።

## ፲፩ኛ ምዕራፍ ፲፩

# ባለራዕይነት

***"ራዕይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል፤ ሕግን የሚጠብቅ ግን የተባረከ ነው"*** (ምሳሌ 29፥18)።

ኢየሱስ፥ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ፊት ለሚኖራቸው በፊ አግልግሎት፥ ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል ጠቃሚ የሆነ ስልጠና ሰጥቷቸዋል። ያስተማራቸውም እንደ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አንድ ክፍል ውስጥ ተቀምጠው፣ የሚያስተምረውን ትምህርት በማስታወሻ ደብተራቸው እየጻፉ ሳይሆን፣ የራሱን የግል ሕይወት በምሳሌነት እያዩ እንዲማሩ ዕድል በመስጠት ነው። የኢየሱስ *መሠረታዊ የሆነ የሕይወት መመሪያ (principle)፥ እንዲሁም በሰው ሕይወት ውስጥ 'ትልቅ ዋጋ አለው የሚለው' ነገር (value)* ምን እንደሆነ ደቀ መዛሙርቱ አብረውት በመሆን በየቀኑ ከሕይወቱ መማር እንዲችሉ ዕድል ሰጥቷቸዋል። የተማሩትንም በተግባር ላይ እንዲያውሉት ሁለት ሁለት አድርጎ ለአገልግሎት ይልካቸው ነበር (የሉቃ. 10፥17-24)። ደቀ መዛሙርቱ መማር ያለባቸውን ትምህርት የተማሩትም ከስህተት ሁሉ ነጻ ሆነው ሳይሆን፥ አልፎ አልፎ እያበላሹም ጭምር ነበር (የማር. 9፥14-29)። ከአቅማቸው በላይ የሆነ፥ ወይም ሊሠሩት የማይችሉትን *ሥራ*፣ ሊሸከሙት የማይችሉትን ኃላፊነትንና *ሥልጣንን* አይሰጣቸውም ነበር። ዛሬም እግዚአብሔር ዓላማውን እንደሚገባው ሊፈጽሙ ይችላሉ ብሎ የሚያስባቸውን መንፈሳዊ መሪዎች፥ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ዕውቀቱንና ጥበቡን እንዲሁም በአገልግሎት ውስጥ የሚሰጣቸውን ኃላፊነት ለመሸከም የሚያስችላቸውን አቅም (ጉልበት)፣ እንዲሁም



የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን በመስጠት አስቀድሞ ያዘጋጃቸዋል። ዓላማውን የሚፈጽሙበትን ችሎታና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ይሰጣቸዋል።

በአገልግሎታቸው የብዙ ሰዎችን ሕይወት በሚያስደንቅ ሁኔታ በዘመናት የነኩ፣ የብዙ ሰዎች የሕይወት መለወጥ ምክንያት የሆኑ ታላላቅ ሰዎች፣ "ጥሩ መሪዎች" ከሚያሰኛቸው ነገሮች መካከል አንደኛውና ትልቁ፥ *"የራዕይ"* ሰዎች መሆናቸው ነው። ራዕያቸውን የሚያገኙት ለመሆኑ ከየት ነው? *"ራዕይ"* ለመሪውም ሆነ ለተመሪው ሕዝብ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። በታሪክ ውስጥ ያየናቸው ታላላቅ እንቅስቃሴዎች ጅማሬያቸው በሰው ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር አሳብ ውስጥ ቀደም ሲል የነበሩ ናቸው። ለአንድ መንፈሳዊ መሪ አገልግሎቱን ለመፈጸም ከእግዚአብሔር ጥሪ ማግኘቱ ብቻ በቂ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፣ የራሱን ሕዝብ ወዴት ማድረስ እንዳለበት አስቀድሞ የሚያውቅ መሆን አለበት። *ከዮሴፍ ጀምሮ እስከ ማርቲን ሉተር ኪንግ ድረስ መጥተው ያለፉት ታላላቅ መሪዎች ሁሉም፣ "ሕልም አለኝ" (I have a dream) በማለት ሕልማቸውን ያወጁ ናቸው።*[24] "አለን.." ያሉትም ሕልም ከራሳቸው የመነጨ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ከራሱ የተሰጣቸው ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም አሳዛኝ የሚሆነው ነገር የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ (መሪ) "ለቤተ ክርስቲያኔ ምንም ዓይነት ራዕይ የለኝም" ያለ እንደሆነ ነው። ራዕይ በሌለው መሪ የሚመራ ሕዝብ፣ መነሻና መድረሻውን የማያውቅ፣ መረን የተለቀቀ፣ ለአደጋ የተጋለጠ ሕዝብ ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል ***"ራዕይ በሌለበት ሕዝቡ መረን ይሆናል..."*** (ምሳሌ 29፥18) ያለው ለዚህ ነው። ራዕይ የሌለው መሪ፣ በግል ሕይወቱም ሆነ በአመራሩ፣ ከውስጥም ሆነ ከውጪ አንዳንድ ግፊት ሲደርስበት፣ በቀላሉ ዓላማውን በመሳት ሕዝቡን በትኖ ይሸሻል።

ራዕይ ያላቸው መሪዎች ሌሎች ከሚያዩት የበለጠ በርቀት የሚያዩ የእምነት ሰዎች ናቸው። የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለማስገባት ሕዝቡን የመራው ተደናቂ የነበረው ሙሴ የራዕይ ሰው ስለነበረ፣ ሌሎች ማየት ያልቻሉትን እርሱ ማየት የቻለ ሰው ነበር። ***"...ወደ ፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ ተመልክቶአልና"*** (ዕብ. 11፥26) ሲል፣ 'የማይታየውን ማየት' የቻለ፣ የራዕይ ሰው እንደነበረ እናያለን። የኤልሳ አሽከር፣ ግያዝ ዓይኖቹ "በፈረሶችና በሠረገሎች የተጠናከረ፣ ሊያጠቃቸው የመጣውን ታላቅ ሠራዊት" ማየት ሲችሉ፥ የኤልሳዕ ዓይኖች ግን ያዩት የእሳት ፈረሶችና ሠረገሎችን፣ የሰማያዊውን ሠራዊት ነበር (2 ነገ. 6፥15-17)። ባለ ራዕይ የሆነ ሰው በሕይወት ዘመኑ፥ በዙሪያው ያሉት ሰዎች የማያዩትን፣ በሙላትና በስፋት ማየት የሚችል ሰው ነው። *"ራዕይ"* በርቀትም ሆነ በጥልቀት ሌሎች የማያዩትን የማየት ችሎታ ነው። መንፈሳዊ መሪ ጠቃሚ ነው የሚለውን መሠረታዊ መመሪያና የአሠራር ዘዴ የሚያ

---

[24] Philip Greenslade. Leadership, Greatness & Servanthood, Bethany House Publishers, Minneapolis, MN, 1984.

ስገኘውን ውጤት አስቀድሞ የማየትና የማወቅ ችሎታ ሊኖረው ይገባል። ኃላፊነት የሚሰማቸው መሪዎች ዛሬ የሚያወጡት መሠረታዊ መመሪያ የሚመጣውን ትውልድ ምን ያህል ይጠቅማል ወይም ይጎዳል? በማለት አስቀድመው ያስባሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ የወንጌሉን ቃል ለሕንዳውያን ለመስበክ *የሄደው ዊልያም ኬሪ፥ "የራዕይ" ሰው ነበር።* በአካባቢው የነበሩት ክርስቲያኖችም ሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች በወቅቱ የሚታያቸው ቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ያለው ሁኔታ ብቻ ነበር። እርሱ ግን ከውቂያኖስ ባሻገር የሚጠፉት ነፍሳት ይታዩት ነበር። *ብዙዎች ያያሉ፥ ጥቂቶች ግን "ይመለከታሉ፤" እነርሱም ባለ ራዕዮች ናቸው።* ባለራዕይ የሆነ ሰው ልቡ በተ ስፋ የተሞላ ስለሆነ፣ "አይቻልም" በሚባል በት ውስጥም እንኳን፣ "ይቻላል" ብሎ በተስፋ ይጠብቃል። የራዕይ ሰው፣ የሚያዋጣ ባይመስልም የእምነት እርምጃ ለመውሰድ አይፈ ራም። ይሁን እንጂ፥ አደጋ ውስጥ አያ ወቀ ራሱን ይከታል ማለት አይደለም። ከሃያ አም ስት ዓመት በፊት፣ በዓለም ዙሪያ የተበተኑትን ኢትዮጵያውያንን በወንጌል መድረስ እን ድችል፣ "የኢትዮጵያ የወንጌል አገልግሎትን" እንድመሰርት እግዚአብሔር "ራዕይ" ሰጠኝ። በወቅቱ ራዕዩን ያካፈልኳቸው አንዳንድ ሰዎች ለእኔ የሚታየኝ ለእነርሱ ስላልታ ያቸው፣ *"ህልምህ ትልቅ ነው!...ከአቅምህ በላይ ነው ...አትደርስበትም... አትችለውም... ይሄ እንዴት ሊሆን ይችላል?...ቅዠት ነው..."* በማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተስፋ ሊያስቆርጡኝ የሞከሩ፣ የቅርቤ ናቸው የምላቸው ሰዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ ራዕዩን በሰጠኝ ጌታ ተማምኜ ወጣሁ። ጌታም አላሳፈረኝም። ስሙ ይባረክ!

## 1. ራዕይ ወይስ መገልበጥ?

አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች የራሳቸው የሆነ ራዕይ ስለሌላቸው፣ የሌላውን ሰው ራዕይ ገልብጠው በመውሰድ በዚያ ለመመራት ይሞክራሉ። ለምን በዚያን ዓይነት መንገድ መሥራት እንዳለበት ሳያውቁ፣ ከዚህ በፊት ሲሠራበት ስለቆየ ብቻ ያንን መንገድ ተከትለው ዝም ብለው ይሠራሉ። ከዚያ ውጪ ሌላ መንገድ እንዳለ አያውቁም። ከዚህ በፊት የተሠራበት መንገድ ከሆነ፣ በተለይ "ስኬታማ" መስሎ ከተገኘ ያንን ተከትሎ መሄድ (መሥራት) በጣም ቀላል ነው። ይሁን እንጂ ያለፈውን "ውጤት" አይቶ መራመድ (መሥራት)፣ የመንፈሳዊ መሪዎች ዕድገት የሚያሰናክል ዋና ጠላት እንደሆነ ብዙዎች የተረዱት አይመስሉም። ጥሩ ውጤት፣ አንዳንድ ጊዜ የመንፈሳዊ መሪን አመለካከት የማጨለም ኃይልም ሆነ ዝንባሌ አለው። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪ በአዲስ መንገድ ለመሄድ፣ አዲስ እርምጃ ለመውሰድ ከዚህ በፊት ጥሩ ውጤት ያስገኛል ብሎ ያመነበትን የቀድሞውን መንገድ ለመተው ይቸገራል። *ፒተር ድሩከር* ይህን እውነት ሲገልጹ፣

> *"ተሞክሮ ውጤት ያላስገኘውን አሠራር መተው ለማንም አስቸጋሪ አይሆንም፤ በቀላሉ መተው ይቻላል። ቀደም ሲል ጥሩ ውጤት ወይም "ስኬት" ያስገኘውን ግን፣ በወቅቱ ምንም ያህል ፍሬቢስ፣ እንዲሁም ጊዜ ያለፈበት ቢሆን እንኳን ያን ለመተው አስቸጋሪ ይሆናል" ብለዋል።*[25]



እግዚአብሔር አሠራሩ ሁልጊዜ ልዩ እንደሆነና፣ ትላንት በሠራበት መንገድና ሁኔታ ዛሬ መልሶ የማይሠራ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ለዓላማው የሚመርጣቸው ሰዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው ሁሉ፣ እግዚአብሔርም የሚጠቀምባቸው በተለያየ ሁኔታ እንጂ ሁሉንም በአንድ ዓይነት መንገድ አይደለም። ከአንዱ ጋር በሠራው ዓይነት፣ ከሌላው ጋር በዚያው ዓይነት አይሠራም። ከዚህ በፊት እግዚአብሔር "በዚህ ዓይነት አገልግሎት በኃይል ሠርቷልና ሁልጊዜ የሚሠራው በዚህ ዓይነት ነው" ብሎ የሌላውን ቤተ ክርስቲያን አሠራር መቅዳት (ኮፒ ማድረግ) አደገኛ እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓይነት መንገድ ተከትለው የሚሠሩት በወቅቱ ውጤት ማስገኘቱን አይተው ሳይሆን፣ ከዚህ በፊት በሌላው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያስገኘውን ጥሩ ውጤት በማየት ነው። ለዚህ ነው ሄንሪና ሪቻርድ ብላክአቢ የተባሉ ጸሐፊዎች አንድ ላይ ሆነው በጻፉት መጽሐፋቸው፥

> *"ስኬት" ከፍ ወዳለ ዕድገት እንዳይደረስ የሚያደርግ ዕንቅፋት ነው" ያሉት።*[26]

ያለፈውን "ስኬት" መሠረት በማድረግ የትላንትናውን ዓይነት መንገድ ተከትሎ መሥራት ዕንቅፋት እንደሆነው ሁሉ፣ የሌላውን አሠራር ኮርጆ (ገልብጦ) መሥራትም ከዚያ የበለጠ ዕንቅፋት ነው። የንግድ ድርጅቶች፣ ተወዳዳሪያቸውን በልጠው ለመገኘት ብዙ ጊዜ "የመሸጥ ጥበብ፣ የገበያተኛውን አያያዝ ብልሃት፣ ሌላው ቢቀር የሚሸጡትን ዕቃ ጥሩ ስምና ዝና አለው ብለው ከሚያስቡት የንግድ ድርጅት መኮረጅ (መገልበጥ)" በጣም የተለመደ ነው። ሌላው እንዳይኮርጃቸው በሕግ ለመከላከል እንዲያስችላቸው ነው ዛሬ በምዕራቡና በሰለጠነው ዓለም "የፈጠራ ሥራ ባለቤትነት ማረጋገጫ መብት" (*Patent Right*) የሚያወጡት። በአሁኑ ጊዜ በአብያተ ክርስቲያናትም መካከል ተመሳሳይ ውድድር (ፉክክር) እየታየ ነው። በአገራችን ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ከተለያየ ቤተ እምነት የወጡ ቢሆኑም፣ በተለይ በአሁኑ ጊዜ የሁሉም የአምልኮት ይዘታ፣ የሚከተሉት ሥርዓት፣ ሌላው ቀርቶ የሚጠቀሙበት ቋንቋ እንኳን ሳይቀር የሁሉም ተመሳሳይነት ያለው ሆኗል። ድሮ "ልዩ የፈውስ ፕሮግራም ቀን" የሚል ቋንቋ አልነበረንም። ወንጌልን ሰብከን፣ ወደ ጌታ ለሚመጡት አዳዲስ ነፍሳት ከጸለይን በኋላ፣ "ቀጥለን ለበሽተኞች ልንጸልይ ነውና የታመማችሁ ካላችሁ ወደ ፊት ውጡ" በማለት እንጠይቅ ነበር። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔርን የፈውስ ክንድ በሚያስደንቅ ሁኔታ ሲሠራ አይተናል። ለበሽተኞች የምንጸልየው ጌታ ይፈውሳል ብለን እንጂ ሕዝቡ ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን እንዲ

---

[25] Peter Drucker, The Effective Executive in The Executive in Action, Harper Business, New York, 1966.
[26] Henry & Richard Blackaby.

መጣ የምናባብልበት፣ ወይም የእኛ የሆኑት ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዳይሄዱብን የመያዣ ዘዴ አድርገን እንጠቀምበትም ነበር። ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በየቦታው እየሄደ ሲሰብክ፣ የሚመጡትን በሽተኞች ይፈውስ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በሽተኞች የሚፈወሱበት ልዩ ፕሮግራም ሲያዘጋጅ ግን አላየንም። አንዱ ቤተ ክርስቲያን "የፈውስ ፕሮግራም" ሲያወጣ፣ ሕዝቡ ያንን በመፈለግ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዳይሄድ፣ "እኛም የራሳችን የፈውስ ፕሮግራም ማዘጋጀት አለብን" በሚል አሳብ ሁሉም ማዘጋጀት ጀመረ። ዛሬ "ልዩ የፈውስ ቀን" ወይም ፕሮግራም የሌላቸው ቤተ ክርስቲያናት ቢኖሩ በጣም ጥቂቶች መሆን አለባቸው። "የፈውስ ፕሮግራም" ማዘጋጀት የሚለው ሀሳብ ትክክል አይደለም ለማለት ባይሆን፣ ሌላውን መኮረጅ (ኮፒ ማድረግ) በአሁኑ ጊዜ በሰፊው እንደሚታይ እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ብቻ ነው።

አንዳንድ ሰዎች አዕምሯቸውን ተጠቅመው፣ አስፈላጊውን ጥናትና ምርምር አድርገው አንድ ሥራ በመጀመር ፈንታ፣ ሌላው የሠራውን ሥራ (ቢያዋጣም፣ ባያዋጣም) ኮፒ የሚያደርጉ አሉ። ለምሳሌ አንዱ "እንጀራ ቤት" ቢከፍት፣ ሌላውም እንጀራ ቤት ይከፍታል። ሌላው ቀርቶ "እንጀራ ቤት መክፈት አያዋጣም፤ እኔም ሱቄን ልዘጋ ነው" ቢለው፣ እውነቱን የሚነግረው ስለማይመስለው ዘሎ ይገባበታል። ይሄ በዓለም ውስጥ ያለ ሁኔታ ሲሆን፣ በመንፈሳዊው ዓለምም ተመሳሳይ ችግር አለ። በአሁኑ ጊዜ ስንት እንደ ደረሰ አላውቅም፣ የዛሬ ስድስት ወይም ሰባት ዓመት ገደማ አንዱ ስለ አገራችን መንፈሳዊ ይዞታ ሲያጫውተኝ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በመንግሥት ፈቃድ ያገኙ ሁለት ሺ ስምንት መቶ አገልግሎቶች (ሚኒስትሪዎች) እንደተቋቋሙ ነገረኝ። የሚያስደንቀው ሲሠሩት ያሰቡት ሥራ የአብዛኞዎቹ አንድ ዓይነት ነው። መስራቾቹ ሁሉም ከእግዚአብሔር ራዕይ ተቀብለው ስላልሆነ፣ ከነዚህ ውስጥ ስንቶቹ አገልግሎታቸው እንደ ቀጠለ አይታወቅም። ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር ከእግዚአብሔር ራዕይ መቀበል ማለት ከሌላው ሰው መገልበጥ ማለት እንዳልሆነ ነው። ይህን ዓይነቱ አቋራጭ መንገድ ካለ፣ ማንም ከእግዚአብሔር እውነተኛ የሆነውን ራዕይ ለማግኘት በጌታ ፊት በጸሎትና በጾም መቆየት አስፈላጊነቱ ለብዙዎች አይታያቸውም። *"እከሌ ቤተ ክርስቲያን ከፍቶ፣ ይህንና ያንን በማድረጉ ዛሬ ተሳክቶለታልና እኛም እርሱ ያደረገውን ማድረግ አለብን"* በማለት አገልግሎታቸውን ለማሳደግ የሚሞክሩ መንፈሳዊ መሪዎች በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም።

በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በየሳምንቱ ተመሳሳይ የሆኑ ፕሮግራሞች ሲካሄዱ እናያለን። ምን እያደረጉ እንደሆኑና ለምን እነዚያን ፕሮግራሞች እንደሚያካሂዱ ለራሳቸውም ሆነ ለሚጠይቋቸው ሰዎች ምክንያታቸውንና ዓላማቸውን በትክክል መግለጽ የሚችሉ አይመስለኝም። ችግራቸው፥ ምዕመናኑን አንድ አድርጎ ሊያያዝ ወይም ሊያስተባብር የሚችል፥ *"ወደፊት ይህን ለማድረግ፥ ወይም እንዲህ ለመ*



*ሆን እንፈልጋለን"* የሚሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ *"ራዕይ"* ወይም *"ዓላማ"* የሌላቸው መሆኑ ነው። በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ የሚያካሂዱቸው አገልግሎቶች ምን ያህል ፍሬያማ እንደሆኑ የሚለኩበት ወይም የሚመዝኑበት መለኪያ የላቸውም። እንዲሁም *"ልንደርስበት የምንፈልገው ግባችን ወይም ዓላማችን ይሄ ነው"* የሚሉት ተጨባጭ የሆነ "ዓላማ" የላቸውም። ቢኖራቸውም ከሚፈልጉት ግብ እንዴት መድረስ እንደሚችሉ፥ እንዲሁም መሥመራቸውን ጠብቀው በቀጥተኛው መንገድ መሄድ፥ ወይም አለመሄዳቸውን የሚያዩበት ወይም የሚለኩበት መለኪያ (መመዘኛ) የላቸውም። የሚያባዝነው፥ ቢጠፉ እንኳን "ልክ አይደለንም፤ መንገዳችንን ስተናል" ብለው እንዳይመለሱ፥ መጥፋታቸውን እንኳን አያውቁም። እንዲህ ዓይነት አቋም ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት፥ *"የትም እንደማይሄድ፥ ባለበት ዝም ብሎ እንደሚሽከረከር ወይም እንደሚዞር መኪና (machine)"* ናቸው። ይንቀሳቀሳሉ፤ ግን የትም አይደርሱም። የፕሮግራሞቻቸው ብዛት ማደጋቸውን የሚያሳይ ስለሚመስላቸው ብዙ ፕሮግራሞችን ሲያካሂዱ ይታያሉ። ይሁን እንጂ ቀድሞ ከነበሩበት አንድም እርምጃ ወደ ፊት አይሄዱም።

## 2. ራዕይ ምንድን ነው?

*"የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባለ ራዕይ መሆን አለባቸው"* የሚለውን አሳብ ለመረዳት፥ በቅድሚያ "ራዕይ" ምን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልገናል። *"ራዕይ"* ምን እንደሆነ የተለያዩ ሰዎች በተለያየ ሁኔታ ይገልጹታል፥

- "ራዕይ ሕይወትን ይሰጣል። ራዕይ ከሌለ የሞትን ዘር መዝራት ነው። ለጊዜው ያህል ነው እንጂ መጨረሻ ላይ ጊዜውን ጠብቆ ሞት ማሸነፉ አይቀርም።"
- "ራዕይ (vision) ማለት ሕብረቱ ወይም ማሕበሩ ወደ ፊት ሊደርስበት ወይም ሊሆን የሚችለውን ሁኔታ ግልጽ ወይም ጉልህ በሆነ መንገድ የሚያሳይ ነው። ራዕይ "የግብን" አቅጣጫ የሚያመለክት፥ የሕብረቱ ተባታፊዎችን ትክክለኛ በሆነ ቦታቸው ላይ የሚያስልፍ፥ የጋራ የሆነውን ዓላማ ለመፈጸም ኃይልን የሚሰጥ ነው።"
- "አንድን ነገር ትክክልና ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ ለመግለጽ፥ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ፥ ከየት ተነስቶ የት ለመድረስ እንደሆነ በቅድሚያ ማወቅ ያስፈልጋል። የሕብረቱን ዓላማ የሚገልጽ፥ ወይም የሚያሳይ፥ ሕዝቡ ወዴት እየሄደ እንደሆነ የሚያመለክት፥—እነዚህ ሁሉ "ራዕይን" የሚገልጹ ናቸው።"

ቤተ ክርስቲያን *"ዓላማቢስነትን"* ለማሸነፍ፥ አጠቃላይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዕቅድ ውጪ ላለመሆን *"ራዕዮን"* ማዳበር ይገባታል። ቤተ ክርስቲያን ራዕይ ሲኖራት፥ የያዘችውን *"የእውነት ቃል"* መጠበቅ የሚያስችላት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ ዓለምን

ስወንጌሉ ቃል መድረስ ያስችላታል። "ራዕይ" የወደፊቱን የሚያሳይ ወይም ዓላማ አድርገን የተነሳንበትን አገልግሎት ለመፈጸም የሚያስችል ዓይነተኛ መመሪያን ይበጣል። ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መሪዎቿ እንዲሆኑ አንዳንዶቹን ስትጠራ፥ ውስጥ ያሉትን ምዕመናንን ማገለግል ብቻ ሳይሆን፥ ባላቸው ራዕይ ምክንያት ሊደርሱባቸው የሚችሉትን አንዳንድ ችግሮች አብረዋቸው እንዲካፈሉም ጭምር ነው። ቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማዋ አድርጋ መነሳት ያለባት ነገር ቢኖር፣ የሰዎች ሕይወት በበጎ እንዲለወጥ መሆን አለበት። እርግጥ ነው ለውጡም መጀመር ያለበት ከውጪ ባይሆን በሕብረቱ ውስጥ ካሉት ሰዎች ነው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ሲለወጡ፥ በእነርሱም አማካኝነት ከውጪ ያሉትን መድረስ ይቻላል። መንፈሳዊ መሪዎች "ባለራዕይ" መሆን እንዳለባቸው እናውቃለን። ነገር ግን ሌሎችን የሚያነቃቃ፣ ፍሬያማ ሥራ ለመሥራት እንዲችሉ በሕብረቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች እርስ በርስ የሚያያዝ "ራዕይ" የሚያገኙት ከየት ነው? ነው ብለን መጠየቃችን አይቀርም። "ራዕይ" በተለያየ ምክንያት፣ ከተለያየ ምንጭ ሊፈጠር ይችላል። "ራዕይ" ትኩረት የሚሰጠው "በትላንትና" ወይም "በዛሬው" ላይ ሳይሆን ወደፊት በሚሆነው ነገር ላይ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን የግብጽ ንጉሥ ወደ ፊት በምድሪቷ ላይ የሚደርሰውን የጥጋብና እንዲሁም የረሀብ ዘመን የሚመጣ መሆኑን አስቀድሞ አየ። የጥጋቡን ዘመን በመጠቀም ወደ ፊት ስለሚመጣው የረሀብ ዘመን አስቀድሞ መደረግ ያለበትን ዝግጅት ማድረግ እንዲችሉ እግዚአብሔር ዮሴፍን ተጠቀመበት። በዚህ ዓይነት የወደፊቱን ለመስወጥ፥ ወይም ሊመጣ ያለውን ክፉ ነገር ለማስተካከል በወቅቱ ያለውን መልካም ጊዜ መጠቀም ጥሩ ውጤታ እንደሚያስገኝ ይሄ ሁኔታ ያሳያል።

"ራዕይ" በዓላማ ላይ የሚያተኩር ነው። በቃላት ገልጦ አይናገረው እንጂ፣ በው ሁሉ የራሱ የሆነ የሕይወት ዓላማ አለው። ካሰበበት ዓላማ ለመድረስ ያቅዳል፤ እንዲሁም ያቀደውን በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ እንዴት በተግባር ላይ እንደሚያውለው መንገድና ብልሃት ይፈልጋል። "ዓላማ" ፈጽሞ አይለዋወጥም። የሰው ፍላጎት ግን ስለሚለዋወጥ፥ በዚያው መጠን ራዕዩም ይለዋወጣል። አንዳንድ መሪዎችን ትልቅ ሥራ ለመሥራት ያላቸው ጥማት ወይም "ቀስቃሽ ምክንያት" (motive) የራዕያቸውን ዓይነት ይወስናል። ለምሳሌ፣ የአንድ የንግድ ድርጅት ሥራ መሪ ድርጅቱን ለማሳደግ የሚገፋፋው የራሱ የሆነ ምክንያት አለው። ለድርጅቱ ብዙ ትርፍ ማስገኘት፣ ስሙንና ዝናውን ለማሳደግ ነው? ይህ ካልሆነ፣ የሚያሰበው የድርጅቱን ዕድገት ሳይሆን፣ ሌላ ውስጣዊ የሆነውን ፍላጎቱን ለማሟላት ይሆናል። የመንፈሳዊ መሪዎችስ ብዙ ሕዝብ የሚይዝ በጣም ትልቅ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ለመሥራት፣ ትምህርታቸው በቴሌቪዥን እንዲቀርብ ብዙ ዋጋ የሚከፍሉት፣ የሬዲዮ ፕሮግራም የሚያቋቁሙት፣ ለሚጠፉት ነፍሳት በእርግጥ ተቆርቁረውና ተጨንቀው፣ ከእግዚአብሔር ራዕይ ተቀብለው ነው? ከሆነ፥ እግዚአብሔር በሚሰጡት አገልግሎት ደስ ይለዋል። የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲሰፋ፣ ነፍሳት በብዛት እንዲድኑ ሳይሆን፣ "ታላቅ አገልጋይ" ተብለው እንዲታ



ወቁ በሆነ፣ ራዕዩ የመጣው ከእግዚአብሔር ሳይሆን፣ የራሳቸውን ድብቅ የሆነውን ምኞታቸውንና ፍላጎታቸውን ለመፈጸም ራሳቸው የፈጠሩት ራዕይ ነው። ስለዚህ መንፈሳዊ መሪዎች አንድ ትልቅ ነገር ለመሥራት ሲያቅዱ፣ ራዕዩን እግዚአብሔር ሰጥቷቸው እንደሆነና እንዳልሆነ በቅድሚያ ራሳቸውን በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው። የፈረንሳዩ ናፖሊዮን ቦናፓርት ፈረንሳይን በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ የከተታት መሪ ነበር። ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው መላውን አውሮፓን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ለመግዛት ነበር። በጦርነቱ ከተሸነፈ በኋላ፣ "እንዳሰብኩት በአካሄድኳቸው ጦርነቶች ማሸነፍ ብችል ኖሮ፣ ታሪክ የሚያደንቀኝ ታላቅ ሰው እሆን ነበር" አለ። በድል አድራጊነት ባይሆንም፣ ናፖሊዮን በታሪክ ውስጥ ትልቅ ሥፍራን አገኘ። ይሁን እንጂ፣ በጦርነቱ ውስጥ ሕይወታቸውን ያጡት፣ የቆሰሉት ወታደሮች የናፖሊዮን ዓላማ ወይም ምኞት ያ መሆኑን አስቀድመው ቢያውቁ ኖሮ ያንን ዓይነት ከፍተኛ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኞች ይሆኑ ነበር ወይ? ዛሬም በመንፈሳዊው ዓለም መሪዎች፣ የሚመሩት ሕዝብ ያለውን ጉልበት፣ ጊዜና ገንዘብ መስዋዕት አድርጎ እንዲሰጡ የሚቀሰቅሱት በእርግጥ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ለማስፋፋት ነው? ወይስ መሪዎች ከሚመኙት የዕድገት፣ የዝና ደረጃ ለመድረስ ነው? ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ መስጠት የሚችሉት መሪዎች ብቻ ናቸው።

"ራዕይ" ስንል፥ ተኝተን የምናልመው ሕልም፥ ወይም ድንገት ወደ አዕምሯችን ብቅ የሚል አሳብ ይሆን? ሰዎች የሚያስፈልጋቸው ነገር ምን እንደሆን በማጥናት፣ ጉድለታቸውን ለማሟላት፣ በዚያ ዙሪያ ራዕይን ማበጀት የእግዚአብሔር አሳብ አለበት ብሎ መቀበል ይቻላል? ለምሳሌ፥ በአንድ ከተማ ውስጥ የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ "የሕዝቡን ፍላጎት ምን እንደሆን አውቀን፣ የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎት እንሰጣለን" በማለት መጠይቅ አዘጋጅተው፣ ባደረጉት ጥናት መሠረት፣ "ይህን ዓይነት አገልግሎት እንጀምራለን" ብለው ቢነሱ፣ "ያ አሳብ የእግዚአብሔር ሀሳብ ነው፤ ራዕዩን የተቀበሉት ከእግዚአብሔር ነው" ብሎ ማለት ይቻላል? በዚህ ዓይነት ጥናት የተገኘውን ውጤት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ራዕይ ነው ብሎ መቀበል አስቸጋሪ ነው። እርግጥ ነው "ራዕይ" በአገልግሎት አካባቢ የሰዎች ፍላጎት ምን እንደሆን በመገንዘብ፥ በሕይወታቸው የሰውጥ ዕድል የሚሰጥ መንገድ ከፋች ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ኃላፊነት የማሕበረሰቡን ጥያቄ ወይም ፍላጎት ሁሉ እንድታሟላ ላይሆን ይችላል። እግዚአብሔር ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አንድ ዓይነት ሳይሆን፣ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የተለያየ አገልግሎት እንዲፈጽሙ ኃላፊነት የሚሰጥበት ጊዜ አለ (1 ቆሮ. 12፥12-31)። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ራዕዩዋን የምታገኘው ምን እንደሚፈልግ ሕዝቡን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመጠየቅ መሆን አለበት። መንፈሳዊ መሪዎች የሕዝቡን ፍላጎት ለሟሟላት ጥረት ሲያደርጉ፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ ከሆነው ኢየሱስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እያጡ ይሄዳሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከኢየሱስ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ከማንኛውም ነገር የበለጠ ቅድሚያ ሊሰጡት ይገባል። ኢየሱስ አገልግሎቱን የመራው በሕዝቡ ፍላጎት ላይ በማተኮር ሳይሆን፣ በእግዚአ

ብሔር ፈቃድ ላይ ነበር። መንፈሳዊ መሪዎች በሰዎች ፍላጎት ሳይሆን፤ በመንፈስ ቅዱስ የሚቀሰቀሱ መሆን አለባቸው።

ትክክለኛ (እውነተኛ) የሆነ "ራዕይ" ሌሎችን የመሳብ ኃይል አለው። ብዙዎች የራዕዩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍላጎታቸውን ይቀሰቅሳል። ሕዝቡ የራዕዩን ጠቃሚነት ማየት ከቻሉ፥ በመንፈሳዊ መሪያቸው ላይ ብርቱ እምነት ካላቸው፤ ራዕዩን ተግባራዊ ለማድረግ መሪው "እድርጉ" የሚላቸውን ወይም ከእነርሱ የሚጠበቀውን ነገር ለማደረግ፤ እንዲሁም ትብብራቸውን ለማሳየት፤ ፈቃደኞች ይሆናሉ። የራዕዩን ሂደት ወይም ዕድገት ሲመለከቱ፥ በክርስቶስ ውስጥ ማድረግ የሚችሉት ነገር እየታያቸው ሲመጣ፤ ራዕዩን ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ አንድ ዓይነት ሥፍራ እንዲኖራቸው ፍላጎታቸው የበለጠ ይቀሰቀሳል። "ራዕይ" ተከታዮቹን በኃይል ማሲታጠቅ ይችላል። ይኸውም፥ በሌሎች ሕይወት ውስጥ እውነተኛ ለውጥ ለማምጣትና እንዲሁም ጌታን ለማገልገል ያላቸውን መክሊት ወይም የጸጋ ስጦታ እንዲጠቀሙ ስለሚያስችላቸው ነው። ከዚህ በፊት አይተውትና አድርገውት የማያውቁትን ትልቅ ነገር ለማድረግ ዕድል፥ እንዲሁም የሕይወት እርካታን ይሰጣቸዋል። የሚጠበቅባቸውን ነገር ለመፈጸም በራዕይ እንጂ በኃፍረት፥ በበደለኛነት ስሜት፤ ወይም በሌሎች ግሳጼና ግፊት ምክንያት የሚቀሰቀሱ አይሆኑም።

## 3. መንፈሳዊ መሪ "ራዕይ" ያለው መሆን አለበት

ራዕይ ለአመራር በጣም አስፈላጊ ነው። ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ሁሉም "ባለ ራዕዮች" እንደነበሩ ታሪካቸው ይመሰክራል። ባለ ራዕይ ሰው እርቆ ማየት፥ ወይም ወደፊት መሆን የሚችለውን ወይም መሆን ያለበትን አስቀድመው የማየት ችሎታ ያለው ነው። ባለ ራዕይ ሰው አቅሙና ችሎታው ምን ያህል እንደሆነ መገመት የሚችል ነው። ጥሩ መንፈሳዊ መሪዎች ባለራዕዮች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ ያላቸውን ራዕይ የሚመሯቸው ሰዎች ራዕያቸውን እንዲቀበሏቸውና እንዲተባበሯቸው የመቀስቀስ ወይም የማሳመን ችሎታ ያላቸው ናቸው። የራሳቸውንም ሆነ የሚመሯቸውን ሰዎች፥ "ወደፊት" የሚኖራቸውን ተስፋና ምኞት በአንድ ራዕይ ሥር እንዲሆን የማድረግ ችሎታ አላቸው። "ራዕያቸው" ግልጽና ማንንም የማያደናግር ሲሆን፥ የተነሱበት ዓላማ ፍጻሜ እንዲያገኝ ወይም ራዕያቸው በተግባር ላይ እንዲውል ሕዝቡን መቀሰቀስ ይችላሉ። ሕዝቡ መሪያቸውን እንዲከተሉ የሚቀሰቅሳቸው "ራዕይ" ሲኖር ነው። "ራዕይ" በሰው ልብ መተማመንን ያሳድራል፤ ሰዎች በራሳቸው እምነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። መሪዎች ለሚከተሏቸው ሰዎች "አቅጣጫ" ማሳየት አለባቸው።



እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች ምን ዓይነት መሆን እንዳለባቸው "ቢል ሎረንስ" (Bill Lawrence) "ኢፌክቲቭ ፓስተሪንግ" (Effective Pastoring) በሚለው መጽሐፋቸው ሲገልጹ አምስት ዋና ዋና ችሎታዎችን ጠቁመዋል።[27] ይኸውም፥

*1ኛ/ "ባለ ራዕይ" መሆን አለበት። ሕዝቡ በአገልግሎቱ ተሳታፊነት እንዲኖረው ፍላጎቱን የሚቀሰቅስ "አጠቃላይ ዓላማ" ማሳየት አለበት።*

*2ኛ/ በሕብረቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች "ራዕዩን" አይተው እንዲቀበሉትና እንዲከተሉት አሳቡን በደንብ ገልጾ ማስረዳት የሚችል መሆን አለበት።*

*3ኛ/ ጽኑ መሆን አለበት። ምንም ዓይነት እንቅፋትና ችግር ቢያጋጥመውም ጸንቶ መቆም የሚችል መሆን አለበት።*

*4ኛ/ ከሚፈለገው ዓላማና ውጤት ለመድረስ አብሮት ካለው ሕዝብ ኃላፊነት ማከፋፈል የሚችል መሆን አለበት።*

*5ኛ/ የሕብረቱን እንቅስቃሴ መቆጣጠር፥ ስሀተት ቢኖር ከስሀተቱ በመማር የሕብረቱን ዕድገት መጨመር የሚችል መሆን አለበት።*

በዘመናት ውስጥ መጥተው ያለፉት ታላላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች፥ ጽንሰ አሳቡ ከሰው አዕምሮ የፈለቀ ሳይሆን ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግልጽ ነው። አማኝ አገልግሎቱን ለመፈጸም ከእግዚአብሔር "ጥሪን" መቀበል ብቻ በቂ አይደለም። ነገር ግን ፈቃዱን እንዲፈጽም የጠራው እግዚአብሔር ምን ዓይነት አምላክ እንደሆነና፥ እንዲሁም እንዲገለገል የሚፈልገው ሕዝብ ከየት ተነስቶ የት እንዲደርስ እንደሚፈልግ አስቀድሞ ማወቅ አለበት። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ታሪኩን በሰፊው ያነበብነው ዮሴፍ፥ እንዲሁም በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር፥ ሁለቱም የራሳቸው የሆነ ራዕይ ወይም ሕልም እንደነበራቸው እናውቃለን። እግዚአብሔር እንደ መሣሪያው አድርጎ በሕይወቱ ሊጠቀምበት ያሰበው ሰው፥ የእግዚአብሔርን ዓላማና ዕቅድ በደንብ ካወቀ፥ በመልካም ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜም ውስጥ ቢሆን ሕዝቡን መቀሰቀስና መምራት ይችላል። የታወቀው ዋችማን ኒ (Watchman Nee) ስለ መንፈሳዊ ራዕይ ሲጽፍ፥

> *"በሕይወታችን እውነተኛ የሆነው የእግዚአብሔር ሥራ የሚጀምረው፥ ራሳችንን ለእርሱ የተቀደሰ መስዋዕት አድርገን ስንሰጥ ሳይሆን፥ እጥርተን "ማየት" ስንችል ነው። ይኸውም፥ ራስን የተቀደሰ መስዋዕት አድርጎ መስጠት የሚጀምረው ከመንፈሳዊ ራዕይ በመሆኑ ነው። ካልሆነ ፍጹም አይቻልም" አለ።*

[27] Bill Lawrence. Effective Pastoring, Word Publishing, Nashville, TN.1999.

ጠቢቡ ሠሎሞንም "ራዕይ ባይኖር ሕዝቡ መረን ይሆናል" ያለው ይህንኑ አባብ የሚደግፍ ነው። ይህም ማለት መንፈሳዊ መሪው ትክክል የሆነ ራዕይ ከሌለው፣ የሚመራው ሕዝብ የተደናገረ፣ ግራ የተጋባና እንዲሁም የአመጽ ሰው ይሆናል ማለት ነው። መሪ ባለ ራዕይ መሆን እንዳለበት ሄንሪ ኪሲንጀር (Henery Kissinger) እንዲህ ሲሉ ተናገሩ።

> *"የመሪ ሥራ የሚመራውን ሕዝብ በወቅቱ ካለበት ሥፍራ አንስቶ ከዚህ በፊት ካልደረሰበት ሥፍራ ማድረስ ነው። የሚመራው ሕዝብ ወደፊት የሚደርስበትን ዓለም አያውቀውም። መሪዎች ለጊዜው የታወቁና ዝነኞች ቢሆኑም፣ መጨረሻ ላይ እንደ ራዕያቸው ሕዝቡን ከሚፈለግበት ደረጃ ማድረስ ካልቻሉ፣ ተሸናፊዎች ይሆናሉ።"*

ብዙ ዓይነት ለውጦች በሚታዩበት፣ "ሁሉም ነገር በጣም ጥሩ መሆን አለበት" በሚባልበት ዓለምና ዘመን፣ የዘመኗ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናኑን ለማሳደግና ለአገልግሎት ለማስታጠቅ ራዕይ ያላቸው መሪዎች ያስፈልጓታል።

አንዳንድ አገልጋዮች ብዙ ጊዜ "ጌታ ይህን... ያን... እንዳደርግ ነገረኝ" ሲሉ ይሰማሉ። የሚገርመንና ጥያቄ የሚሆንብን እነዚሁ ሰዎች "ጌታ ነገረኝ" ያሉትን ነገር ጥቂት ጊዜ ከሠሩ በኋላ፣ ከዚሀ በፊት "እግዚአብሔር እንዳደርግ ነገረኝ" ማለታቸውን ረስተውት እንደሆን አናውቅም፣ የጀመሩትን አገልግሎት ይተውና ሌላ አገልግሎት ውስጥ ገብተው ይታያሉ። የእነዚህን ሰዎች እንቅስቃሴ የሚመለከቱ አንዳንድ ሰዎች "እግዚአብሔር በየጊዜው አሳቡን ይለዋውጣል እንዴ?" ብለው መጠየቃቸው አይቀርም። አንዳንዶች አገልግሎት መስዋወጡ ሰልችቷቸው፣ ተስፋ ቆርጠው ከአገልግሎት ጨርሰው የሚወጡም አሉ። በግል አገልግሎቴ ውስጥ ብዙ መሰናክሎች፣ ችግሮችና ፈተናዎች አጋጥመውኛል። ወደ አገልግሎት የገባሁት እግዚአብሔር ሳይጠራኝና ራዕይ ሳይሰጠኝ፣ በራሴ ፈቃድ ቢሆን ኖሮ፣ ገና ድሮ ከአገልግሎት ወጥቼ ነበር። በአገልግሎቴ መረጋጋትና ያለመታከት እንድሠራ ኃይልና ጉልበት ከሆኑልኝ ምክንያቶች መካከል አንደኛው፣ እግዚአብሔር የሰጠኝ ምን ጊዜም የማልጠራጠረው ራዕይ ነው። እግዚአብሔር በሕይወቴ እንድፈጽመው ለሚፈልገው ነገር ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍለኝም ያንን ለመፈጸም ፈቃደኛ ነኝ።

## 4. "ራዕይ ከሌለ ሕዝብ መረን ይወጣል"

ቤተ ክርስቲያንን የሚመራ መጋቢ (ፓስተር)፤ ለሚመራው ቤተ ክርስቲያን ግልጽ የሆነ "ራዕይ" ከሌለው፣ በጣም የሚያሳዝን ነው። መንፈሳዊ መሪ ራዕይ ከሌለው፣ ከውስጥም ሆነ ከውጪ ትልቅ ትግል ያጋጥመዋል። ከውስጥ ያሉት ምዕመናን፣ "ይህን



እንፈልግም፤.. የምንፈልገው ያንን ነው" ይሉታል። ለቤተ ክርስቲያኒቱ ተጨባጭ የሆነ ራዕይ የሌለው መጋቢ (ፓስተር) ከሆነ፣ ጥያቄያቸውን ለሟሟላት የሚፈልጓቸውን ዓይነት ሰባኪዎች እየጋበዘ ደስ ያሰኛቸዋል። ተጋብዞ የሚመጣውም ሰባኪ ስሌላ ጊዜ እንደገና እንዲጋበዝ በተቻለው መጠን ጠባዩን ያሳምራል።

ለቤተ ክርስቲያኒቱ ተጨባጭ የሆነ ራዕይ የሌለው መጋቢ ችግር የሚያጋጥመው ከውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ከውጪም ጭምር ነው። ከውጪ የሚመጣው እንግዳ ትምህርት፣ *"ቤተ ክርስቲያን ይህን ዓይነት እምነት መከተል፥ እንዲሁም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወይም መመሪያ መመራት አለባት"* የሚል ግፊት በመሪው ላይ ሊያመጣበት ይችላል። በዘመናችን የራሱ አቋም፣ የራሱ መመሪያ፥ የራሱ የሆነ አመራር ያለው ሰው ቁጥሩ አነስተኛ ነው። "ካርቦን ኮፒ" የበዛበት ዘመን ነው። ሌላው ካደረገው፣ "እኛም ማድረግ አለብን" የሚባልበት ዘመን ነው። አንዱ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንዳጋጣሚ አንድ የቆየ መጽሐፍ አግኝቶ ስሁተት የሆነ ትምህርት እንዳለበትና እንደሌለበት ሳይመረምር፣ ያንን መጽሐፍ ገልብጦ "ጌታ አዲስ የሆነ መገለጥ ሰጠኝ" በማለት ማስተማር ብቻ ሳይሆን፣ ምዕመኑ እንዲለማመድ ያደርጋል። የራሱን ቤተ ክርስቲያን ሕዝብ ማሳሳቱ ብቻ ሳይሆን፣ በየቦታው እየሄደ "ጌታ አዲስ መገለጥ ሰጠኝ" ያለውን ትምህርት ማስተማርና ሰዎች እንዲለማመዱ ያደርጋል። "ታላቅ መንፈሳዊ አገልጋይ ነው" የተባለውን ሰው መከተልና "አድርጉ" የሚለውን ማድረግ እንደ "ፋሽን" የሚታይበት ዘመን ነው። ይህንን የማይከተል፣ "በጸጋ ያገለግላሉ" የሚባሉትን አስተማሪዎች የማይጋብዝ፣ ትምህርታቸውን የማይቀበል የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ቢኖር፣ በቤተ ክርስቲያን አባላቱ ብዙ ችግርና ግፊት ይደርስበታል። "እነዚህን ልምምዶች አልቀበልም፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አላስገባም" በሚለው ውሳኔ ላይ የሚጸና ከሆነ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ በመጋቢነት አገልግሎቱ እንዳይቆይ ወይም እንዳይቀጥል ትልቅ ዘመቻ ይደረግበታል።

ለዚሀ ጥሩ ምሳሌ እንዲሆነን በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የሚለማመዱትን ልምምድ መጥቀስ እወዳለሁ። ኢየሱስ ስለ ምጽዋዕት አሰጣጥ ሲያስተምር፣ *"ለእነርሱ ትታዩ ዘንድ ጽድቃችሁን በሰው ፊት እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ካለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም"* (የማቴ. 6፥1) ካለ በኋላ ስምን ዓይነት ሁኔታ መስጠት እንዳለብን አስተምሮናል። *"አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ በስውር ያለው ምጽዋትህ ቀኝህ የምታደርገውን ግራህ አትወቅ፤ ምክንያቱም ምጽዋትህ በስውር መሆን አለበት፤ በስውር የተሠራውን የሚያይ አባትህም የመልካም ሥራህን ዋጋ ይከፍልሃል"* ይላል (የማቴ. 6፥3-4)። የምንሰጠውን ስጦታ "እያችሁልኝ ወይ?" በማለት ጥሩምባ እየነፋን መስጠት እንደሌለብን፥ ነገር ግን ሌላው ቀርቶ "ቀኛችን የሚያደርገውን፣ ግራችን እንዳያውቅ" የሚለውን የክርስቶስን ማስጠንቀቂያና ትምህርት በመጣስ፣ "እያሸበሸባ

ችሁ... መድረኩ ድረስ እየወጣችሁ ስጡ..." የሚል ልምምድ ተጀምሯል። በአሁኑ ጊዜ ስንቱ የኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ይህንን እንደሚለማመዱ አናውቅም። ብዙዎች እንደሆኑ እርግጠኞች ነን። ለመሆኑ ይህን ዓይነቱ ልምምድና ትምህርት ከየት ይሆን የፈለቀው? አሜሪካን አገር እንደመጣሁ አንድ ጊዜ አስር ሺ ሕዝብ ከተሰበሰበበት አንድ ትልቅ ስብሰባ ሄድኩ። በዚያ ስብሰባ ላይ ብዙ ጥያቄ የሆኑብኝን አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ልምምዶችን አይቼ በጣም አዘንኩ። ካየኋቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ ልምምዶች መካከል አንደኛው፣ "የምጽዋዕት አሰባሰብ" መንገዳቸው ነው። አሥር ሺውም ሕዝብ ምንም ያህል ጊዜ ቢወስድም ከመቀመጫ እየተነሳ መድረኩ አጠገብ ከተቀመጡት ትላልቅ ቅርጫቶች ውስጥ ስጦታውን እንዲሰጥ ተደረገ። "ገንዘብ ባይኖራችሁ እንኳን እየመጣችሁ ቅርጫቱን እየነካችሁ ተመለሱ" ስለተባሉ፣ ከመቀመጫችን ያልተነሳንና ያልሰጠን ከእኔና ይዞኝ ከሄደው ሰው በስተቀር ይሉኝታ ፈርቶ ሳይሰጥ የቀረ ሰው አልነበረም። ይህን ዓይነቱ መንገድ፣ ብዙ ገንዘብ ለመሰብሰብ ተብሎ የተፈጠረ ዘዴ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የሚደግፈው አለመሆኑን ለመረዳት፣ ይህን ያህል የሥነ መለኮት ምሁር መሆንን አይጠይቅም።

በዚያን ወቅት በአዕምሮዬ ይመላለስ የነበረው፣ "እንዲህ ዓይነቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አሠራር በቪዲዮ ተቀርጾ አገራችን ይገባ ይሆን?" የሚል ፍርሃትና አሳብ ነበር። በወቅቱ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደ አሜሪካ ገና ያልመጡበት ጊዜ ስለነበረ፣ በየአስቴቱ የኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ስላልተጀመሩ፣ ፍርሃቴ እነዚህ እንግዳ ልምምዶች ወደ ኢትዮጵያ ይደርሱ ይሆን? የሚል ነበር። አሜሪካ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሕዝቡን የሚያታልሉ እውነተኛ ያልሆኑ "ጌታ በፈውስና በተአምር ይጠቀምብናል" የሚሉ ብዙ አስተማሪዎች እንዳሉ በመጥቀስ "የአሜሪካ ክርስትና" በሚል አርዕስት፣ እነዚህ እንግዳ ትምህርት ከሚያስተምሩ አስተማሪዎች እንዲጠነቀቁ ለማድረግ ከሃያ ሁለት ዓመት በፊት ሙከራ ማድረጌን ጽሁፎቼ ደርሷችሁ ያነበባችሁ ታስታውሳላችሁ። ያ የፈራሁት ነገር ጊዜውን ጠብቆ መድረሱ አልቀረም። በአሁኑ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ልምምድ በጣም ከመብዛቱ የተነሳ፣ እውነተኞቹ እነርሱ ሆነው፣ ሀሰተኞቹ "ተጠንቀቁ!" ብለው ማስጠንቀቂያ የሚሰጡትና እውነቱን ለማስተማር የሚሞክሩት ሆኑ። በዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ትክክል የሆነ ራዕይ ከሌላት፣ መንፈሳዊ መሪውም ሆነ፣ ምዕመኑ ያገኘውን ሁሉ ስለሚያፍስና ስለሚቀበል፣ ሕዝቡ በእምልኮቱም ሆነ በግል መንፈሳዊ ሕይወቱ መረን የወጣ እንደሚሆን በጣም ግልጽ ነው።

ጠቢቡ ሠለሞን *"ራዕይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል..."* (ምሳሌ 29፥18) አለ። በአገልግሎት የተሰማራ ማንኛውም አገልጋይ ሠለሞን ይህን ለምን እንዳለ ይገባዋል። ኢየሱስ "ቀንበሬን በጫንቃችሁ ተሸከሙ" አለ (የማቴ. 11፥29)። ራዕይ እንደ ቀንበር ነው። ገበሬ ሁለት በሬዎችን በቀንበር ውስጥ በመያዝ መሬቱን ለማረስ እንደሚችለው



ሁሉ፣ "ራዕይም" ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን ሰዎች ይዞ በአንድ ላይ በማያያዝ ወደ አንድ አቅጣጫ መምራት ያስችላል። ያለ "ራዕይ ቀንበር" በግል ሕይወትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መረን ያስወጣል። አንድ ዓይነት ራዕይ ወይም ዓላማ የሌለው ሕዝብ ገደብ ሳይኖረው ወደ ፈለገው አቅጣጫ ይዘላል። የቤተ ክርስቲያን ምዕመን፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ሁሉም የራሱን አሳብ እየተከተለ የሚፈልገውን፣ ደስ የሚለውን የሚያደርግ ከሆነ፣ ሁከትና ግርግር እንጂ እውነተኛ የሆነ ሰላም አይኖርም። አንዱ በአንድ አቅጣጫ ሲጎትት፣ ሌላው ተቃራኒ በሆነ አቅጣጫ ይስባል። ይህ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትመራበት ራዕይ ስለሌላት፣ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሌላቸው ብዙ ራዕዮች ሲኖሩ ነው። እያንዳንዱ አባል የራሱን ራዕይ በሥራ ላይ ለማዋል ሲሞክር፣ ራዕይ ብለው የተቀበሉት አሳብ ከእግዚአብሔር መሆን አለመሆኑን መጠየቃቸውና መጠራጠራቸው አይቀርም። ራዕይን በሚመለከት አሳብ ላይ ሁለት ዓይነት ችግሮች እናያለን። ይኸውም፣

- *አንደኛው ችግር፣ ራዕይ ማጣት ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ራዕይ ከሌላት፣ ሕዝቡ የፈለገውን፣ ደስ ያለውን ስለሚያደርግ፣ እውነተኛ ዕድገት ስለማይኖር ሕዝቡ በቀላሉ ተሰፋ ይቆርጣል። ሌላው ችግር፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ እርስ በርሳቸው ያልተያያዙ ብዙ ራዕዮች ሲኖራት ነው። ይህ ሲሆን፣ ሕዝብ በአንድ አቅጣጫ በመመራት ፈንታ ሁሉም የመሰለውን መንገድ ይዞ ስለሚሄድ ትልቅ ሁከት ይፈጠራል።*

- *ሁለተኛው ችግር፣ ራዕዩ ከእግዚአብሔር ያልመጣ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ያልተያያዘ ሲሆን ነው።*

የአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች "የቤተ ክርስቲያኒቱ ራዕይ ምንድነው?" ተብለው ቢጠየቁ አብዛኛዎቹ መልስ እንደሌላቸው እርግጠኞች ነን። ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች አሏቸው። ይሁን እንጂ፣ እነዚያ ፕሮግራሞች የሚካሄዱት ለምን እንደሆነ ግን ብዙዎች የሚገባቸው አይመስለንም። ከየት ተነስተው፣ የት ለመድረስ እንደሆነ በደንብ አያውቁም። "ራዕይ" ሳይኖር፣ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን ማካሄድ ይቻላል። ምን ያህል ፕሮግራሞች እንደጀመሩና እንዳካሄዱ ይዘርዝሩ እንጂ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዕድገት መለካት አይችሉም። የሚያባዝነው አንዳንዶች ዕድገታቸውን የሚለኩት ባላቸው የፕሮግራም ብዛትና ዓይነት፣ እንዲሁም ባላቸው የሕዝብ ብዛት መሆኑ ነው። መንፈሳዊ መሪዎች የቤተ ክርስቲያኒቱን ራዕይ ካላወቁ፣ ከምዕመናኑ መካከል ስንቶቹ ከእነርሱ ጋር እንደሆኑና እንዳልሆኑ ማወቅ አይችሉም። ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የመጣ ራዕይ ያስፈልጋታል። መንፈሳዊ መሪዎች "ራዕይ" ... ን እንደሆነና እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ መረዳት ይኖርባቸዋል። ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ራዕይ መሠረት የሚያገለግሉትን ሕዝብ፣ እግዚአብሔር እንዲደርሱበት ከሚፈልግበት

ደረጃ ሊያደርሷቸው ይገባል። ምዕመናኑም ቤተ ክርስቲያናቸው ከእግዚአብሔር የተቀበለችው ራዕይ ምን እንደሆነ ሲያውቁ፣ የወንጌሉን አደራ ተቀብለው አንደ አንድ ሰው በመሆን፣ እግዚአብሔር በዓለም ላይ በቤተ ክርስቲያኑ አማካኝነት ሊያደርገው በወደደው ሥራ ላይ ተባባሪ ለመሆን ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለመስጠት ፈቃደኞች ይሆናሉ።

ያለ ራዕይ ሕዝብን በአንድ ሕብረት ውስጥ ይዞ መምራት በጣም አስቸጋሪ ነው። አንዳንድ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡበት ምክንያት ለማሕበራዊ ኑሮ፣ ከሰዎች ጋር ለመገናኘት፣ ቤተ ክርስቲያን በመሄዳቸው ብቻ መንፈሳዊ የሚያደርጋቸው ስለሚመስላቸው እንደሆነ መዘንጋት የለባቸውም። የቤተ ክርስቲያን ዓላማዋ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ ማድረግ ብቻ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። አማኞች ከእግዚአብሔር ልብ በወጣ ራዕይ መመራት፣ እውነተኛ የሆነ ሕብረት መፍጠር፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ጀምሮ ባወጣው መመሪያ ሥር ራሳቸውን ማስገዛት አለባቸው። ቀደም ሲል እንደገለጽነው የብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት ችግር፣ እውነተኛ የሆነ ራዕይ ማጣት፣ ወይም እውነት የሚመስሉ ራዕዮች መብዛት ነው። ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ የሆነ ራዕይ ባይኖራትና ራዕይ በማጣት ብዙ ችግር ውስጥ ብታልፍም፣ አባላቱ ግላዊ የሆነ የራሳቸው ራዕይ ሊኖራቸው እንደሚችል የታወቀ ነው። እርግጥ ነው አንዳንዱ ራዕይ “በራስ ላይ ያተኮረ ራዕይ” ሊሆን ይችላል። “በራስ ላይ ያተኮረ” ራዕይ ያለው ሰው፣ “በዚህ ዓለም ከሌሎች ጋር ተስማምቼ መኖር የሚያስችለኝን፣ ደስታና እርካታ ሊሰጠኝ ይችላል ብዬ የማስበውን ብቻ አደርጋለሁ” ይላል። ይሄም በራስ ላይ ያተኮረ ባህሪ እንዳለው ያሳያል። እግዚአብሔር ከሚሰጠው የራዕይ ቀንበር ውጪ ስንሆን፣ በራስ ላይ ያተኮረው ራዕይ በሕይወታችን ጎልቶ ይታያል። በራስ ላይ ያተኮረ ራዕይ ያላቸውን አማኞችን ማስደሰት ወይም ማርካት የሚችል መጋቢ ወይም መንፈሳዊ መሪ የለም። ምክንያቱም በራሱ ላይ ያተኮረ ሰው ምን ጊዜም ቢሆን መርካት የማይችል በመሆኑ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ያተኮረ ራዕይ ያለው፣ በራሱ ላይ ያተኮረ ራዕይ ካለው ሰው ጋር አብሮ መሄድ አይችልም።

## 5. እውነተኛ ራዕይ ያላቸው፣ የእግዚአብሔር ክብር የተገለጠላቸው ናቸው

እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ መሪ፣ በሕይወቱ በማያጠራጥር ሁኔታ የእግዚአብሔር የክብሩ ብርሃን የተገለጠለት መሆን አለበት። አብርሃም እግዚአብሔር እንዲያደርግ ያዘዘውን ነገር ከማድረጉ በፊት መጀመሪያ “የክብር አምላክ ተገለጠለት” (የሐዋ. 7፥2)። እግዚአብሔር በሕይወታቸው ታላላቅ ሥራን የሠራባቸው ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር በሙሉ ክብሩ የተገለጠላቸው ናቸው። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሀፊ የነበረው ጀድሰን



ኮርንዎል (Judson Cornwall) ታላላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴን ስለ መሩ ታላላቅ መንፈሳዊ አባቶች ሲጽፍ፣ እንዲህ አለ፣

> *“እነዚህ ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መምራት የቻሉ ታላላቅ መንፈሳዊ ሰዎች፣ በአገልግሎታቸው ትልቅ ውጤት ያገኙት፣ የንግግር ችሎታ ስላላቸው፣ ወይም በረቀቀ የሥነ መለኮት ችሎታቸው ተከራክረው ማሳመን በመቻላቸው ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ክብር ስለተገለጠላቸው ብቻ ነው።”*

የታወቀው ጆናታን ኤድዋርድ በ1737 ለብቻው እልም ካለ ጫካ ውስጥ ሆኖ አስደናቂ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር ተገልጦ ካየ በኋላ ነው ፍጹም የተለየ ሰው መሆን የቻለው። ቻርለስ ፊኒ፣ (Charles Finney) ዲ. ኤል. ሙዲም (D. L. Moody) ተመሳሳይ የሆነ ልምምድ ውስጥ እንዳለፉ ታሪካቸው ይመሰክራል። ሙዲ ልምምዱን ሲገልጽ፣

> *“እግዚአብሔር ራሱን ገለጠልኝ። እኔም ከንዱን ከእኔ ላይ እንዲያነሳ ተማጽንኩት”* አለ።

ይህን ዓይነት ልምምድም ያገኙት ሌላ ነገር ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ በኃይል በሚሞሉበት ጊዜ እንደሆነ ግልጽ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም ሲገልጸው፣ ***“ታዲያ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚገኘው አገልግሎት እንዴት የበለጠ ክብር ይኖረውም”*** ይላል (2 ቆሮ. 3፥8)። በእግዚአብሔር ክብር ላይ ያተኮረ ሕይወት ሲኖረን፣ እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ያኖረውን የአገልግሎት ራዕያችንን የበለጠ ብሩህ ያደርግልናል። እግዚአብሔርም ራሱን ለእኛ በመግለጽ ጸጋውን ያበዛልናል። ጳውሎስ ***“...በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ፣ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም..”*** ይላል (ገላት. 1፥15-16)። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ራሱን ለእኛ ሲገልጥ፣ በሕይወታችን የተቀበልነውን የእግዚአብሔርን ጥሪ የሚያረጋግጥልን ከመሆኑም በላይ፣ ራዕያችንን የበለጠ ያሰፋልናል። እግዚአብሔር ለሙሴ የእግዚአብሔር ተራራ እየተባለ በሚጠራው ኮረብታ ላይ በተቀጣጠለ የእሳት ነበልባል መካከል ከተገለጠለት በኋላ፣ ለእስራኤል ያለውን ዓላማ፣ እንዲሁም እርሱ ማድረግ ያለበት ነገር ገለጸለት። ሙሴም በእግዚአብሔር መገለጥ ውስጥ ጥያቄ ለሆኑበት ነገሮች አጥጋቢ መልስ አገኘበት።

(1) እግዚአብሔር ሲገለጥለት፣ ሙሴ የራሱን ማንነት አወቀ። እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መሪ እንዲሆን እንደሚፈልገው ሲሰማ፣ ለዚህ ከፍተኛ ዓላማና ጥሪ ብቃት የለኝም ብሎ የሚያስበው ሙሴ፣ “..የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ አለው” (ዘጸ. 3፥11)። እግዚአብሔርም ለሙሴ ሊገልጽለት የፈለገው፣ “ድል የምታገኘው በአንተ ማንነት ሳይሆን፣ በእ/

ኃይልና ሥልጣን" ነው የሚል ነበር። የራሳቸውን ብቁነት የተጠራጠሩ ሳሙኤልን፥ ኢሳያስንና ኤርምያስን የመሳሰሉ ነበሩ። የኃይሉ ባለቤት ወይም ምንጭ ማን እንደሆነ ሲረዱ፥ "እነሆኝ ጌታ ሆይ! እኔን ላከኝ.." ይላሉ።

(2) እግዚአብሔር ሲገለጥለት፥ ሙሴ ሥልጣኑ በማን እጅ እንዳለ አወቀ። እግዚአብሔር ሙሴን ሲጠራው የጠየቀው ጥያቄ "የላከህ ስሙ ማነው ብለው ቢጠይቁኝ ምን እመልሳለሁ?" የሚል ነበር። ለማድረገው ነገር "ሥልጣን የሰጠኽ ማን ነው?" ቢሉኝ ምን ዓይነት መልስ መስጠት እችላለሁ? በማለት እግዚአብሔርን ጠየቀው። እግዚአብሔርም "ያለና የሚኖር እርሱ ወደ እናንተ ልኮኛል በላቸው" አለው (ዘጸ. 3፥14)። ዛሬም እግዚአብሔር ራሱን ከገለጠልንና ካኛው የራሱ የሆኑት ሕዝቦቹ ምን መሆን እንዳለባቸው፥ ከምን ዓይነት ደረጃ ላይ መድረስ እንዳለባቸው መመሪያ የሚሆነንን ራዕይ ይሰጠናል። በሕዝቡ መካከል የምንሆነው የእግዚአብሔር ወኪሎች ሆነን ነው። ከዚህ የበለጠና የተሻለ ሌላ ምን ዓይነት ሥልጣን እንፈልጋለን?

(3) እግዚአብሔር ሲገለጥለት፥ "ያላመኑኝስ እንደሆነ" የሚለው ፍርሃት ጠፋለት። እግዚአብሔርን ሙሴ "እስራኤላውያን እግዚአብሔር አልተገለጠልህም ብለው ባያምኑኝና ቃሌን ባይሰሙ ምን እላቸዋለሁ? አለው" (ዘጸ. 4፥1)። ይህን ዓይነቱ ጥያቄ በሙሴ አዕምሮ ብቻ የሚፈጠር አይደለም። በአሁኑም ዘመን ያሉት መሪዎች አንዳንድ ትግል የሚጠይቅ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው የሚጠይቁት ጥያቄ ነው። "ይህን ባደርግ፥ የተጠበቀውን ዓይነት ውጤት ባያመጣስ? ያቀረብኩትን አዲስ አሳብ ሰዎች ባይቀበሉትስ? በኃይልና በሥልጣን ስሰብክና ሳስተምር ሕዝቡ ቅር ቢለውስ? መልዕክቴ ኃይለኛ ሆኖ አንዳንድ ሰዎችን ቢያስቀይማቸውስ?" እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ናቸው፥ እንድንሠራቸው እግዚአብሔር በልባችን ያሳደረውን አንዳንሠራ እንቅፋት የሚሆኑብን ወይም ወደ ኋላ የሚጎትቱን። በፍላጎታችንና ሥርተን በምናመጣው መካከል ድልድይ ሲሆን የሚችል፥ ተስፋ በመቁረጥና አገልግሎታችንን በመቀጠል መካከል መሆን የሚችለው የእግዚአብሔር የክብር መገለጥ ነው።

(4) የእግዚአብሔር በክብር መገለጥ፥ "አልችልም" የሚለውን ፍርሃቱንና ጥያቄው መልስ ሰጠው። ሙሴ ለጥያቄው ሁሉ መልስ ቢያገኝም፥ "እሺ! እኔን ላከኝ" በማለት ፈንታ የራሱን ችሎታ በመጠራጠር "እባክህ ጌታ ሆይ! ወደዚያ እትላከኝ ቀድሞም ሆነ ወይም አሁን አንተ ከእኔ ጋር መነጋገር ከጀመርህበት ጊዜ አንስቶ የመናገር ችሎታ የለኝም፤ እኔ አንደበቴ የሚኮላተፍና አጥርቼ ለመናገር የማልችል ነኝ አለው" (ዘጸ. 4፥10)። ማንኛውም መንፈሳዊ መሪ የተጠራበትን ዓላማ ለመፈጸም የራሱን ብቃትና ችሎታ የሚጠራጠርበት ጊዜ አለ። "በቂ



ትምህርት የለኝም፤ ለአገልግሎት የሚያበቃ በቂ ዝግጅት የለኝም። ከእኔ የበለጡና የተሻሉ ብዙ ሰዎች አሉ" በማለት ከጥሪያቸው ለመሸሽ የሚሞክሩ ሰዎች አሉ።

(5) የእግዚአብሔር በክብር መገለጥ ለሙሴ ሙሉ ድፍረትን ሰጠው። አሮንና ሚርያም በቅናት የተነሳ በወንድማቸው ላይ ነቀፋ በሚያሰሙበት ጊዜ፥ ነቀፋቸውን ወደ እግዚአብሔር አቀረበ (ዘኁልቁ 12፥1-16)። የእግዚአብሔርን በክብር መገለጥ ያየ ሰው ምልክቱ፥ "የዋህነቱ" ነው። ለሚደርስበት ነቀፌታ አይደናገጥም፥ ወይም ራሱን ከነቀፋ ለመከላከል አይፍጨረጨርም። በእግዚአብሔር ፍርድና ሥልጣን ሥር ራሱን ያደርጋል። አንዳንድ የሚመራቸው ሰዎች "አሁንስ አበዛኸው" ሲሉት፥ አይደናገጥም፤ ወይም ወደ ኋላ አያፈገፍግም። እግዚአብሔርን በማወቅ ላይ ጸንቶ ይቆማል። እግዚአብሔር ራዕይን ሲሰጥ፥ ድፍረትንም ይሰጣል። ነብዩ ኢሳያስ የእግዚአብሔር ክብር ሲገለጥ በማየቱ ኃይለኛ የሆነውንም ቃል ለመናገር ሙሉ ድፍረት ነበረው። "ኢሳይያስ ይህን ያለው የመሲሕን ክብር ስላየ ነው..." (የዮሐ. 12፥41)። ሙሴም በፈርኦን ፊት ቆሞ ኃይለኛ ቃል መናገር የቻለው የእግዚአብሔርን ፊቃድና የክብሩን መገለጥ ስላየ ነው።

ሙሴ በሕይወቱ መማር ያለበትን ነገር የተማረ ሰው ነበር። በጣም የተማረ ሰው በመሆኑ፥ በቃልም ሆነ በተግባር እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት እውጥቶ ለመምራት ብቃት ነበረው።

## 6. የእግዚአብሔርን "ራዕይ" ለመቀበል የሚያስችል ጸጋ ተሰጥቶናል

እግዚአብሔር ወደ ጠራቸው አገልግሎት ሰዎችን ለማሰማራት በንፈልግ፥ የሰዎች ሁኔታ ብዙ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሆኖ እናገኘዋለን። "ሰዎች ምነው እንዲህና እንዲያ ቢሆኑ" ብለን የምንመኝበት ጊዜ አለ። መርሳት የሌለብን እውነት ቢኖር፥ ሰዎች ራዕዩን መቀበል የሚያስችላቸውን ጸጋ ከእግዚአብሔር የተቀበሉ መሆናቸውን ነው። ኃጢአት ወደ ሰው ልብና አዕምሮ ውስጥ ሲገባ፥ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ችሎታ አቅጣጫውን እንዲለውጥ ያደርጋል። ይህንን በመረዳት፥ እግዚአብሔር በውስጣቸው ባስቀመጠው ጸጋ አብረናቸው ልንሠራ እንችላለን። መረዳትና መቀበል ያለብን፥ የእግዚአብሔር ሰዎች ራዕይ ለመቀበል የሚያስችል በውስጣቸው ጸጋ እንዳላቸው ነው። የእርሱን ዓላማ መፈጸም የምንችል ሰዎች እንድንሆን ብቃትን ሰጥቶናል። በእኛ ሕይወት ውስጥ የሚሠራው ሥራ፥ ራዕዩንና ዓላማውን በሕይወታችን መሙላት ነው። በቅድሚያ

መረዳት ያለብን እውነት ቢኖር፥ ከእግዚአብሔር ውጪ እውነተኛ ራዕይ እንደሌለና እንዲሁም ሁላችንንም ራዕዩን ለመሸከም የሚያበቃንን ኃይልና ችሎታን በውስጣችን ያኖረ መሆኑን ነው። ጳውሎስ ይህንን እውነት ሲገልጽ፥ *"...አዕምሮአችሁ በእነዚህ ከሁሉ በሚበልጡና ክብርን በሚያስጡ መልካም ነገሮች የተሞላ ይሁን..."* (ኤፌ. 4፥8) ይላል። ይሄም እግዚአብሔር ለሰዎች ያሰው ፈቃድና ምኞት ምን እንደሆነ ያሳየናል። የእግዚአብሔርን ሰዎች ስንመለከት፥ ማንነታቸውን ለማወቅ ገና በእናታቸው ማህጸን ውስጥ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ በአዕምሯችን ውስጥ ልንስላቸው ይገባል። የክርስቶስን ፈቃድና ዓላማ መፈጸም እንዲችሉ አድርጎ እንደሠራቸው ማመን አለብን። መንፈሳዊ መሪዎች የሆኑ ሁሉ፥ የሚመሯቸው ሰዎች ስለራሳቸው ይህንን እውነት እንዲያውቁ ማድረግ አለባቸው። የእግዚአብሔር ራዕይ ለነርሱ ምን እንደሆነ ሲረዱ፥ "የተፈጠርኩት፥ ወደ ዓለም የመጣሁት ለዚህ ነው" ማለት ይጀምራሉ። ስለራሳቸው ይህን እውነት ካላወቁ ሁል ጊዜ እረፍት የሌላቸው፥ ግራ የተጋቡ እንደሆኑ ይቀራሉ። በቀላሉ በአዕምሮ ጭንቀት በመያዝ፥ "ለምን ተፈጠርኩ?" በማለት ሁልጊዜ ሲያማርሩና ሲበሳጩ ይታያሉ።

መንፈሳዊ መሪዎች ራሳቸው ራዕይ ከሌላቸው፥ እንኳን የሌሎች ልብ በእግዚአብሔር ዓላማና ራዕይ መሙላት ቀርቶ ራሳቸው ግራ የተጋቡና ዓላማ ቢስ ይሆናሉ። በአደራ ከእግዚአብሔር የተቀበሏቸውን ሰዎች በማሳደግና ባለ ራዕይ እንዲሆኑ በማድረግ ፈንታ፥ "ከዓመት ወደ ዓመት የማያድጉ ሕጻናት ጠባቂዎች" ሆነው ይቀራሉ። ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን በሰዎች ልብ ውስጥ ታላላቅ ራዕይን ይሞላ ነበር። አንድ ጊዜ በመንገድ ሲሄድ ጴጥሮስና ወንድሙን እንድርያስን አይቶ "ኑ ተከተሉኝ! እኔን ብትከተሉኝ አሳ በማጥመድ ፈንታ ሰው አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ" አላቸው። እነርሱ በራሳቸው ሕይወት ውስጥ ያላዩትን አይቶ ወደ ከፍተኛ ራዕይ እንዲሸጋገሩ አደረጋቸው። አዲስና ታላቅ ራዕይ ሰጣቸው። እግዚአብሔር በነርሱ ሕይወት ለመፈጸም የሚፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ገባቸው።

## 7. ራዕይ ያላቸው ሰዎች

ከእግዚአብሔር ራዕይን የተቀበሉትን ሰዎች የሕይወት ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንበብ ደስ ያሰኛል። ራዕይ እንዴት እንዳገኙ፥ በውስጣቸው እንዴት ሥር እንደሰደደና እንዲሁም በሕይወታቸው ምን ዓይነት ለውጥ እንዳመጣ መረዳት ያስችለናል። በብሉይ ኪዳን የዮሴፍ ታሪክ እግዚአብሔር የሚሰጠው ራዕይ በሰው ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ነው። ዮሴፍ ያደገው እንደማንኛውም ተራ ልጅ ሆኖ ነው። የመንፈሳዊነት ዝንባሌ የሚታይበት ልጅ እንደነበረ ግልጽ ነው። አንድ ቀን ህልም አየ። ይሁን እንጂ፥ ያየው ሕልም ትርጉሙ በላልገባው "ቅዠት ነው" ብሎ ቢተወው ኖሮ ዘመኑን ሙሉ የበግ እረኛ ሆኖ ይቀር ነበር። ራዕይ በሰው ሕይወት ሊፈጠር የሚችለው በዚህ ዓይነት ነው። እግዚአብሔር በጠቅላላ ዕቅዱ ውስጥ



የእነርሱ ድርሻ ወይም ሥፍራ ምን እንደሆነ ማየት ይችላሉ። ዮሴፍ ህልሙን ለአባቱ ተናግሮ ትርጉሙ ምን እንደሆነ ሲሰማ፥ እንደማንኛውም ሰጋዊ ሰው፥ "በወንድሞቼ ላይ አለቃ ልሆን ነው። ወንድሞቼ ለእኔ ይሰግዳሉ" ሳይል እንዳልቀረ እንገምታለን። ይሁን እንጂ፥ ይህን ዓይነቱን ሥጋዊ መንፈስ እግዚአብሔር ከውስጡ ፍቆ ማውጣት ነበረበት። ይህንንም ለማድረግ ዮሴፍን በብዙ ችግርና መከራ ውስጥ እንዲያልፍ ማድረግ ነበረበት። ወንድሞቹ ተናደውበት ጉድጓድ ውስጥ በጣሉትም ጊዜ፣ ቀደም ሲል የተሰጠው ራዕይ ከእግዚአብሔር የመጣ በመሆኑ፣ ራዕይ ሳይፈጸም የዮሴፍ መጨረሻ እንደማይሆን ዮሴፍ ምን ያህል ተረድቶት እንደነበረ የምናውቅበት መንገድ የለንም። በሌላ በኩል ደግሞ ዮሴፍ በመከራና በችግር ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በውስጡ ያስቀመጠውን ራዕይ ከሕይወቱ ፍቆ ለማስወጣት ምን ያህል ጊዜ እንደሞከረ አናውቅም። እግዚአብሔር ግን የሰጠውን ራዕይ እየደጋገመ ያስታውሰው ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረው የጸሞና ጊዜም እግዚአብሔርን "ጌታ ሆይ! በውስጤ ያኖርከው ራዕይ ለምን ጠንካራ ይሆናል? ጉድጓድ ውስጥ ተጣልኩ። እንደ ባሪያ ተሸጥኩ። ወህኒ ቤት ተጣልኩ። ቤተሰቦቼን እንደገና ማየት የምችል አይመስለኝም። ይሁን እንጂ፥ በውስጤ ያኖርከው ራዕይ ሊጠፋ ያልቻለበት ምክንያቱ ምን ይሆን?" ብሎ እንደሚጠይቅ እንገምታለን። በመከራና በችግር ውስጥ እንዲያልፍ በማድረግ እግዚአብሔር ዮሴፍን በሚፈልገው ዓይነት ዓላማውን መፈጸም እንዲችል ይቀርጸው ነበር።

የዮሴፍ ሕልም (ራዕይ) በተግባር ሲውል ወይም እውነት ቢሆን፥ ወንድሞቹ ጠልተው በእግሩ ሥር ወድቀው ሲሰግዱለት፥ እግዚአብሔር መጀመሪያ የሰጠው ራዕይ፣ ወንድሞቹ በእግሩ ሥር ወድቀው ከመስገድ በላይ የሆነ ትልቅ ዓላማ እንደነበረው ሳይገነዘብ አልቀረም። ዮሴፍ የተቀበለው ራዕይ ለቤተሰቡ መዳኛ፥ በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ጅማሬ ምክንያት ሆነ። ሰድሳ አራት ሰው ያለበት አንድ ቤተሰብ፥ አድጎ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ሆነ። የተለያዩ ነቢያትና እንዲሁም የሚጠበቀው መሲህ በዚሁ ቤተሰብ ምክንያት ሊወጣ ቻለ። ዓለም በለ እግዚአብሔር ትክክለኛ የሆነ መረዳት እንዲያገኝ ሆነ። ዮሴፍ የተሰጠው ራዕይ (ሕልም) የተረዳው በጣም ጥቂቱን ይሁን እንጂ፥ ራዕዩ የሰው አዕምሮ ቢገምተው ከሚችለው በላይ ነበር። እግዚአብሔር ራዕይ ሲሰጠን፥ መጀመሪያ ላይ ያ የሰጠን ራዕይ ከምን ዓይነት ደረጃ ላይ እንደሚደርስ አናውቅም። እንዲሁም ምን ያህል ሰዎች በእኛ ራዕይ ምክንያት እንደሚባረኩ አናውቅም።

### 7.1. ራዕይ ያለው መሪ፥ ሕዝቡ "ዓላማ" እንዲኖረው ያደርጋል

- እግዚአብሔር ለሙሴ ታላቅ የሆነ ራዕይ ሰጠው። ያም የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር፥ ወደ ከነአን እንዲመራቸው ነበር (ዘጸ. 3፥8)። ግልጽ የሆነ ራዕይ ያለው መሪ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ክብር እንዲያይ የማድረግ ጸጋ አለው። ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ራዕይ ይዞ

ወደ ሕዝቡ ሄደ። ሕዝቡም ራዕዩን ተቀብለው፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እስከ ሆነ ድረስ እንደሚከተሉት ፈቃዳቸውን ገለጹለት። የእግዚአብሔርን ክብር ካዩ በኋላ፥ ምድራዊ የሆነውን የራሳቸውን ፍላጎትና ዓላማ ትተው እግዚአብሔር ያቀደላቸውን ዓላማ ለመፈጸም በፈቃደኛነት ተነሱ። በእግዚአብሔር አጠቃላይና ሰፊ ዕቅድ ውስጥ በመሆናቸው ደስ አላቸው። የእግዚአብሔርን ራዕይ ስንከተል፥ ከግብጽ የሚያወጣን ብቻ ሳይሆን፥ ግብጽን ከውስጣችን ያወጣል። የእግዚአብሔርን የከብሩን መገለጥ፥ እርሱ ለእኛ ያለውን ዓላማና ዕቅድ ካላየን፥ እግዚአብሔር የእኛ እንደሆነ ከመረዳት በቀር፥ እኛ ለእግዚአብሔር እንደምንኖር አናውቅም።

## 7.2. ራዕይ ያለው መሪ፥ ሕዝብን ማስተባበር ይችላል

◆ ራዕይ ሲኖር ሕዝቡ እርስ በርሱ እንዲተባበር፥ ጉልበቱን፥ ችሎታውንና የተለያየ ስጦታውን ለአንድ ዓላማ በማዋል ደስ ብሎት እንዲሠራ ያስችለዋል። ራዕይ ያለው መሪ ከሌለ ሕዝቡ እርስ በርሱ የተከፋፈለ፥ ሁሉም በየግሉ ለራሱ ደስ ያለውንና የሚመስለውን የሚያደርግ ይሆናል። ሕዝቡን አንድ የሚያደርግ ዓላማ ከሌለ፣ ሁሉም ደስ ያለውን ስለሚያደርግ፥ ሕዝቡ መረን የወጣ ይሆናል። ሠለሞን "ከእግዚአብሔር መመሪያ የማያገኝ ሕዝብ ሥርዓት የጎደለው ይሆናል.." (ምሳሌ 29፥18) ያለው ለዚህ ነው። በመሳፍንት ዘመን የነበሩ ሰዎች ራዕይ ያለው መሪ ስላልነበራቸው፥ ሕዝቡ የፈለገውን ያደርግ ነበር። "በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ አልነበረም፤ እያንዳንዱም ሰው ለራሱ ደስ ያለውን ነገር ሁሉ እንደፈለገ ያደርግ ነበር" (መሳፍንት 21፥25) ይላል። ሰው ለራሱ ደስ ያለውን ብቻ ያደርግ የነበረበት ሌላው ምክንያት በዚያን ዘመን የእግዚአብሔር ቃልና እንዲሁም ከእርሱ የሚገለጥ ራዕይ የታጣበት ዘመን በመሆኑ ነበር። "...በዚያን ጊዜ ከእግዚአብሔር የሚነገር የትንቢት ቃልም ሆነ ወይም ከእርሱ የሚገለጥ ራእይ እየታጣ በመሄዱ ብርቅ ሆኖ ነበር" (1 ሳሙ. 3፥1)።

## 7.3. ራዕይ ያለው መሪ ለሕዝቡ ጽናትን ይሰጣል

◆ እስራኤል በመሪያቸው እማኝነት የማይታየውን አምላክ በማየት መታገስን ቻሉ። "እግዚአብሔር በላከው ነቢይ አማካይነት የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ መርቶ አወጣቸው፤ በዚያም ነቢይ አማካይነት ተንከባከባቸው" (ሆሴዕ 12፥13) ይላል። ራዕይ ያለው መሪ ሕዝቡ ዓላማውን ይዞ ወደ ፊት እርምጃውን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲቀጥል ያደርጋል። ራዕይ ያለው መሪ ያላቸው ሕዝቦች፣ የሚወስዱትን እያንዳንዱን እርምጃ ባያውቁትም፡ መጨረሻ ላይ የት እንደሚደርሱ



ግን ያውቁታል። ግልጽ የሆነ ራዕይ ያለው መሪ፥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ምን እንደሚፈልግ የሚያውቅ መሪ፥ በራሳቸው ፈቃድና ዓላማ ከባዘኑበት መልሶ፥ እግዚአብሔር በሚፈልገው አቅጣጫ ሊመራቸው ይችላል።

## 7.4. ራዕይ ያለው መሪ፥ የሕዝቡ ጉዞ ቀጣይ እንዲሆን ያደርጋል

◆ ከእግዚአብሔር ራዕይን የተቀበለው ሙሴ፥ የተመደበለትን ዘመን ጨርሶ እግዚአብሔር ሲወስደው፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የነበረው ራዕይ ከሙሴ ጋር አልጠፋም። ሕዝቡ የተከተለው ሙሴን ሳይሆን፥ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራዕይ በመሆኑ፥ ሙሴ ባይኖርም እርሱ የጀመረውን ሥራ በማቆም ፈንታ ወደ ፊት ቀጠለ። እውነተኛ ራዕይ የሌላቸው መሪዎች፥ አንድን እንቅስቃሴ መርተው በተለያየ ምክንያት አገልግሎታቸው ሲያቆም፥ የተከተሉት የመሪውን ችሎታ አይተው በመሆኑ፥ እርሱ ሲቀር እነርሱም ይቀራሉ። ሙሴ ሲሄድ፥ እያሱ በእርሱ ምትክ ሆኖ ሕዝቡን መምራት በመቻሉ፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዟቸውን እንዲቀጥሉ ሆነ። ሕዝቡ ራዕዩን እንጂ ሙሴን ስላልተከተሉ፥ ኢያሱን "የነገርከንን ሁሉ እንፈጽማለን፤ ወይም የምትልከንም ስፍራ ሁሉ እንሄዳለን፤ ለሙሴ ሁልጊዜ ስንታዘዘለት እንደነበረ ሁሉ፥ ለአንተም እንታዘዛለን፤ እግዚአብሔር አምላክህ ከሙሴ ጋር እንደነበረ፥ ከአንተም ጋር ይሁን! የአንተን ሥልጣን የሚቃወምና ትእዛዝህን ሁሉ የማይፈጽም ቢኖር በሞት ይቀጣ፤ ብቻ አንተ አይዞህ! በርታ!" አሉት (ኢያሱ 1፥16-18)።

## 8. ራዕይ የሚሰጠው ጥቅም

ራዕይ ምንም ያህል ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም፥ የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይኸውም፥

### 8.1. "ራዕይ" ለአገልግሎታችን መመሪያ ይሰጣል

አማኞች ራዕይ ሲኖራቸው የሚያደርጉትን ወይም የሚሰጡትን አገልግሎት ለማንና እንዲሁም ለምን እንደሚያደርጉት ያውቃሉ። በአገልግሎታቸው ብዙዎችን እንደሚደርሱና እግዚአብሔርም በአገልግሎታቸው እንደሚከብር ይረዳሉ። በተጨማሪ በሕይወታቸው ከዚህ በፊት አስበውትና አድርገውት የማያውቁትን ትልቅ ነገር ለማድረግ ውስጣቸው ይቀሰቀሳል። የበለጠ ለማድረግ እንጂ በወቅቱ ባላቸውና በሚያደርጉት ነገር ረክተው አይቀመጡም።

## 8.2. "ራዕይ" በእግዚአብሔር እንዲተማመኑ ያደርጋቸዋል

በዕቅዱ ውስጥ ተከታዮቹ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ መስጠት የሚችሉበትና እንዲሁም እነርሱ የሚያደርጉት ነገር እንዳለ ስለሚያውቁ፣ "ራዕይ" በአገልግሎት ቀሊቃሽነት አለው። ተከታዮቹ ራዕዩ ምን እንደሆነ ማየት ሲችሉ፣ መሪው ራዕዩን በተግባር ለማዋል የሚያደርገውን ጥረት ሲመለከቱ፣ ባላቸው ኃይልና ጉልበት ለመንቀሳቀስ፣ የጸጋ ስጦታቸውን ለመጠቀም ፍላጎታቸው ከፍ ይላል። የአገልግሎት ዕድል በማጣት እጆቻቸውን አጣምረው የተቀመጡ ሁሉ፣ ከዚህ በፊት ይሆናል ብለው ባላሰቡትና ባልገመቱት ሁኔታ አገልግሎታቸውን ለመፈጸም ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ይታያል።

## 8.3. "ራዕይ" እርስ በርስ ያስተባብራል

"ራዕይ" ሲኖር፣ ራዕዩን በተግባር ለመፈጸም ሕዝቡ አንድ ልብ ይሆናል። መሪው ራዕዩን ለምዕመናኑ ሲያካፍል መጀመሪያ ላይ የእርስ በርስ ግፊት፣ መለያየት፣ ጠብና ጭቅጭቅ ሲኖር ይችላል። ነገር ግን ራዕዩን መሪው እንደሚገባው መግለጽ ሲችል፣ የቀድሞቹንም ሆነ አዳዲስ ሰዎችን ራዕዩ ስቧቸው ከምንጊዜውም የበለጠ እንዲቀራረቡና እርስ በርሳቸው እንዲፈላለጉ ይሆናል።

## 8.4. "ራዕይ" ውሳኔ ለማድረግ ይረዳል

"ራዕይ" ከዓላማና ከእምነት መመሪያ ጋር አንድ ዓይነት ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት አገልግሎት መስጠት እንዳለባት፣ ያላትን ገንዘብ እንዴት መጠቀም እንዳለባት፣ ምዕመኑን በልዩ ልዩ አገልግሎት ውስጥ እንዴት ማሳተፍ እንዳለባት ውሳኔ ለመስጠት ቀላል ይሆንላታል። ከላይ በዘረዘርናቸው ነገሮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ነው። ግልጽ የሆነ "ራዕይ" ሲኖር ግን በቀላሉ ውሳኔ መስጠት ይቻላል።

## 8.5. "ራዕይ" ዕድገትን መለካት ያስችላል

ራዕይ ሲኖር አገልግሎታችን በምን ዓይነት ሁኔታ እየተካሄደ እንደሆነ፣ እንዲሁም ፍሬ ያለው መሆኑና አለመሆኑን መመዘን ወይም መለካት ያስችላል። ራዕይ ሲኖር አገልግሎታችንን መለካት መቻላችን ብቻ ሳይሆን፣ ተጠያቂነትም እንዲኖረን ያደርጋል። ከየት ተነስተን የት እንደ ደረስን ለማየትና ለመረዳት ያስችለናል።



## 9. እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ያለው ራዕይ ምንድነው?

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ሦስት ክፍል ያለው ዓላማ ወይም ራዕይ አሉት። የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ከነዚህ ሦስት ክፍሎች ሌላ በንፍስ ወከፍም ሆነ በጋራ የሚከተሉት የተለያዩ ግቦች ሊኖሯቸው ይችላል። እነዚህን ዓላማዎች በተግባር ለማዋል ሲጥሩ፣ የእግዚአብሔርን ፍላጎትና ፈቃድ መፈጸማቸው ሲሆን፣ በነዚህም ራዕዮች እግዚአብሔርን በምድር ላይ እያከበሩት ነው። ራዕዩን ሳይከተሉ በተለያየ መንገድ ቢያከብሩት፣ በሚፈልገውና በሚፈቅደው መንገድ ማክበራቸው አይደለም። ሦስት ክፍል ያለው የእግዚአብሔር ዓላማ (ራዕይ) የትኞቹ ናቸው?

*1ኛ/ በተናጥል ወይም በግል ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል፣ ማወቅና በሁሉም ነገር እርሱን መምሰልና እርሱን መከተል ነው።*

*2ኛ/ የክርስቶስ ከሆኑት ወንድሞችና እህቶች ጋር አንድነት እንዲኖረን ነው።*

*3ኛ/ የምስራቹን ቃል ላልደረሳቸው ሁሉ እንድናዳርስ ነው።*

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ዓላማ የምትፈጽመው እርሱን በማክበር፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ከፍ በማድረግ ሲሆን፣ ይሄም ከላይ በገለጽናቸው በሦስቱ የእግዚአብሔርን ዓላማዎችን በመፈጸም ነው። በዚህ በጣም ተለዋዋጭ በሆነ ዓለም ውስጥ፣ የዘመኑ አብያተ ክርስቲያናት የምዕመናኑን መንፈሳዊ ጥያቄና ፍላጎት ማሟላት የሚችሉ መሪዎች ያስፈልጋቸዋል። መሪዎቿ ባለራዕዮች ብቻ ሳይሆን፣ ራዕያቸውን ተከትለው በድፍረት መምራት የሚችሉ መሪዎች መሆን አለባቸው። መንፈሳዊ መሪዎች የሚያደርጉትን የሚያውቁ፣ ወዴት መሄድ እንዳለባቸው፣ ለማድረግ ያሰቡትን ነገር እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ የሚያውቁ መሆን አለባቸው። "ራዕይ" ለነዚህ ሁሉ መመሪያ ይሰጣል። ከማንኛቸውም ዓይነት ድርጅቶች ይልቅ ለቤተ ክርስቲያን "ራዕይ" በጣም አስፈላጊ ነው። ራዕይ ሕይወትን ይሰጣል። ራዕይ ከሌለ፣ ለጊዜው አይታወቅ እንጂ፣ አንድ ቀን እንቅስቃሴው መሞቱ የማይቀር ነው። መምራትና ማደራጀት (ማስተዳደር) የተለያዩ ናቸው። መምራት "ራዕይን" ይጠይቃል። ማስተዳደር (ማደራጀት) ግን ራዕዩን በተግባር ላይ ማዋል ነው። *በቲቨን ኮቪ (Steven Covey)* የተባለው ጸሀፊ የነዚህን ሁለት አሳቦች ልዩነት ሲገልጽ፣ *"ማደራጀት የዕድገትን መሰላል መውጣት ሲሆን፣ አመራር ግን መሰላሉ በትክክለኛ አቅጣጫ መሆኑን የሚመለከት ነው"* አለ።

## 10. የቤተ ክርስቲያን መጋቢና "ራዕዩ"

የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ መሪ "መጋቢው" ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትመራበት አጠቃላይ የሆነ ራዕይ እንዲኖረው ያስፈልጋል። መመሪያ የሚሆነውን ራዕይ ማውጣት ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለይቶ ማወ

ቅን የሚጠይቅ ቢሆንም፥ ማንኛውም ሰው በሂደት ውስጥ ሊማረውና ሊለምደው እንደሚችል የታወቀ ነው። እንደ ጸጋ ስጦታ፥ ሁላችንም እንዲኖረን ልንመኘው ወይም ልንፈልገው የሚገባ ነው። ለምሳሌ፥ "የወንጌላዊነት ስጦታ" ያላቸው፥ ስጦታው ከሌላቸው የበለጠ ፍሬያማ እንደሚሆኑ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ፥ ስጦታው የሌላቸው፥ ስጦታው እንዳላቸው ሰዎች ጥሩ አድርገው ባይሠሩትም፥ የወንጌሉን ቃል ላልሰሙት ማሰማት ኃላፊነት እንዳለባቸው የታወቀ ነው። እንዲሁም ልግስና ማሳየት ያለባቸው "የመስጠት ስጦታ" ያላቸው ብቻ ባይሆኑ፥ ሁላችንም መስጠት እንዳለብን እናውቃለን። ሁላችንም እምነት ያለን ብንሆንም፥ "የእምነት ስጦታ" ያላቸው ግን፥ እግዚአብሔርን ከእኛ የበለጠ የማመንና በእርሱ የመተማመን ችሎታ አላቸው። ልክ እንደዚሁ ሁላችንም "ራዕይ" ሊኖረን ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ስጦታው ያላቸው ከእኛ የበለጠና የተሻለ ራዕይ ሊኖራቸው ይችላል። መጋቢዎች ሁሉም የወንጌላዊነት አገልግሎት እንደሚሰጡ ሁሉ፥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ "ራዕይ" ማውጣትም ከአገልግሎታቸው አንደኛውን ክፍል የያዘ ነው። "ባለራዕይ" ስንል፥ ስለ ራዕይ ዝም ብሎ የሚያወራ ማለት አይደለም። ነገር ግን "ራዕይን" የሚያወጣ ነው። ስለ ራዕይ የሚያወራ ሀሳቡ ሊኖረው ይችላል። ራዕዩን በሥራ የሚተረጉም ግን ውጤታማ ነው። ስለ ራዕይ የሚያወሩትን ሰዎች ከመስማት ይልቅ፥ ራዕያቸውን በተግባር ከሚያውሉት እንማር። ባለራዕዮች ናቸው ስለተባለ ብቻ ዝም ብለን የሚያደርጉትን ሁሉ ኮፒ እናድርግ። ውጤታማ መሆን የምንችለው "ራሳችንን ስንሆን" እንጂ፥ ሌሎችን ኮፒ ስናደርግ አይደለም።

ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ከሚመራ መጋቢ አልማርም እንበል። "እኔ ያለኝ ቤተ ክርስቲያን ትንሽ ነው፤ እርሱ ግን ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ስላለው እርሱ ማድረግ የሚችለውን እኔ ማድረግ አልችልም" እንል ይሆን? እርግጥ ነው ትልቅ ቤተ ክርስቲያን እንዳለው ብዙ ገንዘብ፥ ብዙ ምዕመን፥ ብዙ የጸጋ ስጦታ ያላቸው ሰዎች እንዲሁም እነርሱ ያላቸውን ዓይነት ዕድል ላይኖረን ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ካለው ሰው መማር አንችልም ማለት አይደለም። እርሱ የሚመራበት መመሪያ ምን እንደሆነ አውቀን፥ ለእኛ በሚስማማን ዓይነት ሁኔታ ልንጠቀምበት እንችላለን። ብዙ ጊዜ መጋቢው ራዕዩን የሚያመነጭና የሚያዳብር ይሁን እንጂ፥ ራዕዩን የሚያዳብረው መጋቢው ብቻ አይደለም። መጋቢ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች ራዕዩን ለማዳበር ተሳታፊነት ከሌላቸው፥ መጋቢው ምን እያደረገ ወይም ምን በማድረግ ላይ እንደሆነ በቂ መረዳት ላይኖራቸው ይችላል። ሽማግሌዎቹ በራዕዩ ተሳታፊነት ሲኖራቸው፣ የሚያደርገውን እንዳያደርግ ባያስቆሙትም፥ ከጎኑ ስለማይሰለፉ ብቻውን መጓዱት ይሆንበታል። ሽማግሌዎች ራዕዩን ለማዳበር ተሳታፊዎች ባለመሆናቸው አንዳንድ ችግር ቢፈጠር፥ የችግሩ ምክንያት መጋቢው እንጂ ሽማግሌዎቹ እንዳልሆኑ ግልጽ ነው። ራዕዩን በማዳበር ጥሩ ውጤት ለማግኘት፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ሽማግሌዎቹን ማዳመጥ፥ ምን እንደሚያሳስባቸው ለማወቅ፥ የሚያቀርቡት አሳብ እነርሱ የሚፈ



ልጉትን ዓይነት ባይሆንም፥ በጥሞና የሚሰጡትን አሳብ ማዳመጥ አለባቸው። የሽማግሌዎቹ አሳብ ሳይጨመርበት ጥሩ አድርገው ሊሰሩት ይችሉ ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ ለብቻ የተሰራው ሥራ ውጤቱ ከሌሎች ጋር በሕብረት እንደተሠራው ጥሩ ላይሆን ይችላል። ሌሎችን ተሳታፊ በማድረጋቸው፣ ሊሠሩት ያሰቡት ዕቅድ ለጊዜው ወደ ኋላ ቢጎትትም፥ ከሌሎች ጋር የግድ አብረው መሥራት አለባቸው። አንዳንድ መጋቢዎች ምንም ዓይነት ራዕይ ሳይኖራቸው ዝም ብለው ማስተማር ይፈልጋሉ። ራዕይ ማውጣትና ማዳበር የማይችሉ ከሆነ፣ ለሚችሉት ኃላፊነቱን ለመስጠት ፈቃደኞች መሆን አለባቸው። እነርሱ ራዕይ ለማውጣትም ሆነ ለማዳበር ፈቃደኞች ካልሆኑ፣ ችሎታውና ዝንባሌው ያላቸው ሌሎች ያወጡትን ራዕይ እነርሱ በተግባር ላይ ቢያውሉት ጥሩ ውጤት ማግኘት ይችላሉ። የራሳቸውን ድካምም ሆነ ያላቸውን አቅም ተገንዝበው ችሎታው ያላቸው እንዲሠሩት ዕድል መስጠት ያስከብራቸዋል እንጂ አያስንቃቸውም።

ራዕይ መጋቢው ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ጠቃሚና አስፈላጊውን መልስ ይሰጣል። ይኸውም፥

- ***10.1. ወዴት ለመሄድ ነው?*** –በደንብ የተገለጸና የዳበረ "ራዕይ" አቅጣጫና እንዲሁም መድረሻ በመስጠት ወዴት እየሄድን እንደሆነ ይነግረናል። ጥርት ባለ ሁኔታ ያወጣነው "ራዕይ" በሚቀጥሉት ሦስት ወይም አምስት አመታት ውስጥ እግዚአብሔር እንዳለቻለን የት እንደምንደርስ ያሳውቀናል። እርግጥ ነው እግዚአብሔር አቅጣጫችንን ሊያስለውጠን ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ሌላው ቢቀር በወቅት በመንቀሳቀስ ላይ እንደሆንን እንረዳለን። ብንሳሳት አቅጣጫችንን ሊያስተካክል ይችላል።
- ***10. 2. ከምንፈልገው ደረጃ የሚወስደን ማን ነው?*** – "መልካም ራዕይ" ዕቅዱን በተግባር ላይ የሚያውሉት መሪዎቻችን እነማን እንደሆኑ ያሳውቀናል። መሪዎቹ ስማቸው ባይጠቀስም፥ ኃላፊነታቸውና የሚኖራቸው ሥልጣን በዕቅዱ ውስጥ መገለጽ አለበት። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፥ ቤተ ክርስቲያን መሪዎቿን ለይታ ማወቅ አለባት። ብዙ ጊዜ ሽማግሌዎችና የቤተ ክርስቲያኒቱ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ለመሪነት ብቃት ያላቸውን ሰዎች ለይተው ማወቅ አለባቸው።
- ***10.3. ከምንፈልግበት ደረጃ (ሥፍራ) የምንደርሰው እንዴት ነው?*** – "ራዕይ" ተሳታፊዎቹ ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በደንብ አድርጎ ይገልጻል። አዲስ አገልግሎት መጀመር ካለብን፥ "ራዕዩ" ይነግረናል። ያለውን አገልግሎት የምንገመግም ከሆነ አሁንም "ራዕዩ" በግልጽ ይነግረናል። የአገልጋዮችን ቁጥር፥ እንዲሁም በጀት ከፍ ማድረግ የሚያስፈልግ ከሆነ "ራዕዩ" ይገልጽል

ናል። በደንብ የተዘጋጀ "ራዕይ" ከየት ተነስቶ፥ የት ለመድረስ እንደ ሆነ ምዕመኑ ሁሉ እንዲያየው ማድረግ ይችላል።

- ***10,4. ከምንፈልግበት ደረጃ ስንደርስ፥ መድረሳችንን በምን እናውቃለን?*** –"መልካም ራዕይ"፥ ራዕዩ በተግባር ሲገለጽ፥ አገልግሎቱ ምን እንደሚመስል ተሳታፊዎቹ ሁሉ ሊያውቁት ይችላሉ። በመካከሉ አንዳንድ ሰውጦች አሁንም ሆነ ቆይቶ ሊመጣ ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ዓላማው ምን እንደሆነ ሁሉም ሊያውቀው ያችላል።

መጋቢ "ራዕዩን" ሲያወጣ በእግዚአብሔር እንጂ በራሱ መተማመን የሰበትም። ከእግዚአብሔር ያልሆነ ዓላማ ወይም ዕቅድ ማውጣት የለበትም። የራሱን ፍላጎትና ምኞት የእግዚአብሔር እንደ ሆነ አድርጎ ማቅረብ የለበትም። "ራዕዩ" መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን አለበት። ይኸውም፥ ሌሎችን የሚያንጽ፥ እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፥ ሌሎችን ለአገልግሎት የሚያስታጥቅ፥ እንዲሁም ወንጌል ሳልደረሳቸው ለማድረስ መሆን አለበት።

## ምዕራፍ ፲፩

# አድማጭነትና አዎንታዊ ነቀፋን የመቀበል ልብ

የክርስትና ሕይወት ሁልጊዜ አንድ ቦታ የሚቆም ባይሆን፣ ዕድገት ያለበት ሕይወት ነው። ጳውሎስ *"ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተናገርን ራስ የሆነውን ክርስቶስን ለመምሰል በሁሉ ነገር እናድጋለን"* ይላል (ኤፌ. 4፥15)። ሐዋርያው ጴጥሮስም፣ *"ይልቅስ በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እርሱንም በማወቅ እደጉ..."* (2 ጴጥ. 3፥18) በማለት ወደ ዕድገት እንድንመጣ ይጠራናል። የምናድገውም ከእርሱ ጋር ባለን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳችን በሚኖረን ግንኙነትም ነው። እርስ በርሳችን ያለን ግንኙነት እንዳያድግ እንቅፋት ሊሆኑ ከሚችሉት ነገሮች አንደኛው፣ እኛ በሌሎች ላይ የምንወረውረው፣ ሌሎችም በእኛ ላይ የሚወረውሩት ጎጂ የሆነ ነቀፋ ነው። በይጣን በብዛት ከሚጠቀምባቸው ልዩ ልዩ መሣሪያዎቹ መካከል አንደኛው መንቀፍ ሲሆን፣ ሁለተኛው መክሰስ (ራዕ. 12፥10) ነው። ነቀፋ ሰዎችን እርስ በርሳቸው የሚከፋፍል፣ ጽኑ የነበረውን አንድነታቸውን የሚያበላሽ ነው። ታዲያ ብዙዎች በዚህ ጎጂ በሆነ መሣሪያ የሚጠቀሙት ለምን ይሆን? መንፈሳዊ መሪዎች የአመራር ብስለት እንዳላቸው የሚታወቁበት አንደኛው መንገድ የሚወረወርባቸውን ነቀፋ በአግባቡ መጠቀም

መቻላቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሌላውን በመገንባት ፈንታ የሚያፈርስ፣ በመትከል ፈንታ የሚነቅል፣ ነቀፋ በሌሎች ላይ ከመጠቀም ራሳቸውን መግታት የቻሉ እንደሆን ነው።

ነቃፊ ምላስ በጣም ጎጂ ነው። ደስታን ያጠፋል። ትዳርን ያናጋል። ፍቅርን ያቀዘቅዛል። ብዙዎችን ተስፋ ያስቆርጣል። የብዙዎችን እርምጃ ወደ ኋላ ይጎትታል። ነቀፋ የብዙዎችን ስሜት ጎድቶ በብዙዎች ሕይወት ውስጥ የአዕምሮ ጭንቀትን ያስከትላል። ብዙዎች የዝቅተኛነት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል፤ የብዙ ሰዎችን መልካም ግንኙነትም ሆነ አንድነት ያበላሻል። ብዙዎቹን ከክርስቲያን ሕብረት እንዲሸሹ ያደርጋል። "ነቀፋን" እግዚአብሔርም በጣም የሚጠላው ነው። እስራኤላውያንን ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያጋጫቸው የነበረው አንደኛው ምክንያት በእርሱ ላይ ያለሙት የነበረው "ነቀፌታ" (ማጉረምረም) ነበር (ዘጸ. 32፥9-10)። ሰው በሌላው ላይ የሚወረውረው ነቀፋ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ቢያውቅም፣ ምላሱን በአግባቡ የማይጠቀምበት ምክንያት ምን ይሆን? ሌላውን መንቀፍ ልማድ ሆኖበት ይሆን? "ልክ አይደለም" ብሎ ያሰበውን ለማስተካከል ይሆን? ከመስመር የወጣውን ለመመለስ ከሆነ፣ ከመንቀፍ ሌላ የተሻለ መንገድ እንዳለ ካለማወቅ ይሆን? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለእነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክረናል።

*ለመሆኑ ነቀፋ" ምንድነው? "ነቀፋ" (criticism) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል፣ "የዌብስተር መዝገበ ቃላት" (1) ፍርድ ወይም ብያኔ መስጠት፣ (2) ስሁተት መፈለግ ይለዋል።* ስለዚህ ነቀፋ፣ *ጥሩ ያልሆነ አስተያየት መስጠት፣ በሌላው ላይ መፍረድ፣ የሌላውን ስህተት ሆን ብሎ መልቀም፣ ሌላውን መክሰስ፣ መገሰጽ ወ.ዘ.ተ. ማለት ነው።* ሁለት ዓይነት ነቀፋ አለ። አንደኛው አፍራሽ ሲሆን፥ ሁለተኛው ግን ገንቢ ነው። አፍራሽ የሆነ ነቀፋ ስለሚሰነዝሩ ሰዎች *"ሼንስተን" (Shenstone)* የተባለ ጸሐፊ፥

> *"ነቃፊዎችን፣ የወይኑን ዛፍ በማነከ (በመቆረጣጠም)፣ የወይን ዛፍን መከርከም የሚያስገኘውን ጥቅም ካስተማረችው አህያ ጋር ባነጻጸራቸው ቅር እንደማይላቸው አምናለሁ" አለ።*

ብዙ ጊዜ ነቃፊዎቹ እኛ በንሆን፣ ነቀፋችንን "ገንቢ" እንለዋለ። ተነቃፊዎቹ እኛ በንሆን ደግሞ "ጎጂ" (አፍራሽ) እንለዋለን። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ገንቢ ያልሆነ ነቀፋ የሚወረወርባቸው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ ራሳቸውም ገንቢ ያልሆነ ነቀፋ አብረዋቸው በሚያገለግሉና በሚመሯቸው ሰዎች ላይ የሚወረውሩበት ምክንያት ምን ይሆን?

## 1. መንፈሳዊ መሪዎች ሌላውን የሚነቅፉበት ምክንያት

አንዳንድ ሰዎች ሌላውን የሚነቅፉት ለምንድነው? ለመጉዳት ሳይሆን፣ ለመጥቀም ብለው የሚነቅፉ አሉ። የሚወዱት ሰው ልክ ያልሆነ ነገር ሲሠራ ወይም ሲሳሳት



እርሱን ለማቅናት ብለው ይጠቀሙበታል። ልጆቻቸው ጥሩ ጠባይ ይዘው እንዲያድጉ የሚፈልጉ ወላጆች፣ አንዳንድ ትክክል መስሎ ያልታያቸውን ነገር ልጆቻቸው ደጋግመው ሲያደርጉ ሲያዩ፥ ያንን ለማስተካከል ወይም ለመለወጥ ሲሉ ይነቅፋሉ። "ልጄን የምነቅፈው በለምወደው ነው" የሚለውን አባባላቸውን ለንለማ፣ በልጆቻቸው ላይ የሚወረውሩት ነቀፋ "የፍቅር ምልክት" እንደሆነ አድርገው እንደወሰዱት እንገምታለን። ወላጆች ልጆቻቸውን ስለሚወዷቸው ስለ ልጆቻቸው ጠባይ ማሰብ ብቻ ሳይሆን በጣም ስለሚጨነቁ፣ ልጆቻቸው ጥሩ ጠባይ ይዘው እንዲያድጉ እንደሚፈልጉ እናውቃለን። ይሁን እንጂ፣ ለማስተካከል የሚወስዱት እርምጃ፥ ልጆቻቸውን ከመጥቀም ይልቅ የበለጠ የሚጎዳቸው መሆኑን የተገነዘቡት አይመስሉም። ወላጆች ነቀፋን እየደጋገሙ በልጆቻቸው ላይ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ ልጆች ወላጆቻቸውን ከመፍራት ይልቅ፣ "መንቀፍ አመላቸው ነው" በማለት ችላ ብለው ያልፏቸዋል። ይሄም በወላጆችና በልጆች መካከል ያለውን ግንኙነት እያሻከረው ይመጣል። አንዳንድ ልጆች በወላጆቻቸው ችላ የተባሉ ከመሰላቸው፣ የወላጆቻቸውን እንክብካቤ (attention) ለማግኘት ሲሉ ሆን ብለው እየደጋገሙ የሚያጠፉ መሆናቸውን የሥነ ልቦና ምሁራን ይገልጻሉ። ስለዚህ ወላጆች ይህንን እውነት ተረድተው፣ ልጆቻቸውን በአግባቡ በማስተማር ፈንታ ነቀፋ በማብዛት ስሜታቸውን እንዳይጎዱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። በወላጆች እየተነቀፉ የሚያድጉ ልጆች፣ የራሳቸውን የግል ኑሮ መኖር ሲጀምሩ፣ ምንም ያህል ገንቢ ቢሆን፥ ልባቸው መራራ ሳይሆን ነቀፋን ተቀብለው በአግባቡ ማስተናገድ አይሆንላቸውም።

አንዳንድ ቀጣሪዎች (አሠሪዎች) ነቀፋን የአስተዳደር ዘዴ አድርገው ሲጠቀሙበት ይታያሉ። ከመንቀፍ ሌላ በሁተትን ማረም የሚቻልበት መንገድ ያለ የማይመስላቸው አሉ። በእነርሱ ላይ ደርሶ ካላዩት፣ ነቀፋ ምን ያህል ጎጂነት እንዳለው አያውቁም። እየተነቀፉ የኖሩ ሰዎች ስለ ራሳቸው ያላቸው ግምት ክጣም ዝቅተኛ ነው። የሚያሳዝነው ስለራሳቸው ዝቅተኛ ስሜት ያላቸው መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ራሳቸውን ከነቀፋ ለመከላከል ሲሉ ሌላውን ያለአግባብ የሚነቅፉ መሆናቸው ነው። አንዳንዶችም መንቀፍ ልማድ የሆነባቸው ይመስላሉ። አጠገባቸው ያለውን ሰው ሁልጊዜ ከድካሙ በስተቀር ብርታቱ አይታያቸውም። ሌላውን የሚያዩት ሁልጊዜ በጥቁር መነጽር ነው። ዓለማውያን ብቻ ሳይሆኑ፣ መንፈሳዊ መሪዎችም ሌላውን ከመንቀፍ ነጻ አይደሉም። ራሳቸው መነቀፍን ባይወዱትም፣ ሌላውን ሰው ሲነቅፉ "ነቀፋዬ ይጎዳው ይሆን?" ብለው ራሳቸውን አይጠይቁም። አንዳንድ መሪዎች ሁልጊዜ ሌላውን መንቀፋቸው፣ የሚወረውሩት ነቀፋ የሚፈልጉትን ነገር የሚያስገኝላቸው ይመስላቸው ይሆን? አንዳንድ ሰዎች ነቀፋ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ቢያውቁም፣ ሌላውን የሚነቅፉበት ምክንያት ምን ይሆን?

ከተለጣቸው የሥራ ድርሻ አንደኛው "መንቀፍ" መስሎ የሚታያቸው፣ ትክክል ያልሆነ ነገር ሲያዩ ያንን የማስተካከል (የማረም) ኃላፊነት ያለባቸው የሚመስላቸው፣

እንዲሁም ያንን ማስተካከል የሚችሉት በሌላ መንገድ ሳይሆን በመንቀፍ ብቻ መሰሏቸው ብዙ ጊዜ ሌላውን የሚነቅፉ አሉ። እንዳንዶቹ ደግሞ ከእነርሱ እሳብ ጋር አብረው የማይሄዱትን ወይም "ይቃወሙኛል" ብለው የሚያስቧቸውን ሰዎች ሁሉ ይንቅፋሉ። እንዳንድ መሪዎች ደግሞ የበላይነታቸውን ለማሳየት ሲሉ ብቻ ሌላውን የሚነቅፉ አሉ። "ይህን አድርጋ፤ ያን አታድርግ" የሚል ትእዛዝ መስጠት እለቃ ወይም የበላይ መሆናቸውን የሚያሳውቅላቸው ይመስላቸዋል። ስለሆነም ይህን ዓይነቱን ፍላጎታቸውን ለማርካት፥ ወይም ዋና መሆናቸውን ለማሳየት ሁልጊዜ ከሰዎች ሕይወት መብራት እብርተው ጉድፍ (ድካም) የሚፈልጉ ይመስላሉ። መንፈሳዊ መሪዎች እግዚአብሔር በመሪነት ሥፍራ ሲያስቀምጣቸው ገንቢ ባልሆነ መንገድ በመንቀፍ የሚመሩትን ምዕመን ስሜቱን እንዲጎዱ እይደለም። እንደ እገልጋይ (እሽከር) በመመልከት ፈንታ ራሳቸውን እንደ እለቃ የሚመስከቱ ከሆነ፥ የሌላው ሰው ስሜት መጎዳት ይህን ያህል ላይሰማቸው ይችላል። ለተወሰነ ጊዜ በመሪነት ሥፍራ ይቀመጡ እንጂ፤ እንዲህ ዓይነቶቹ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመምራት ብዙ ዕድሜ አይኖራቸውም። እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች፥ ከእግዚአብሔር በአደራ የተቀበሉትን ሕዝብ በጥንቃቄ መያዝ እንዳለባቸው የተረዱ፤ ነቀፌታ በመሰንዘር እማኞችን ወደ መንፈሳዊ ዕድገት ማምጣት የማይቻል መሆኑን የተረዱ ናቸው። መንፈሳዊ መሪ "እሽከር" ወይም "ባሪያ" እንጂ እለቃ እለመሆኑን የተረዳ ከሆነ፤ ሌላውን በመንቀፍ ራሱን ለማሳደግ እይሞክርም። ይህ አሳብ ምዕራፍ 11 ላይ በሰፊው የተገለጸ ስለሆነ፥ ምዕራፉን በሙሉ በጥንቃቄ ማንበብ ይጠቅማል።

እንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች በመሪነት ችሎታቸው የማይተማመኑ ከሆኑ፤ የራሳቸውን ድካም ለመሸፈን *"የአቤሴሎምን ዘዴ (ቴክኒክ)"* ይጠቀማሉ። አቤሴሎም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ለመንጠቅ ሲታገል፥ "የአባቴ ዙፋኑ ለእኔ ይገባኛል" በሚልበት ዘመን፤ ተንኮል የተሞላበት ከፍተኛ እንቅስቃሴ በሕዝቡ መካከል ያደርግ ነበር። በኢየሩሳሌም ከተማ በር ቆሞ የአባቱን አስተዳደር እየነቀፈ፤ "እኔ ንጉሣችሁ ብሆን፥ በአባቴ እገዛዝ ሥር ሆናችሁ የሚደርስባችሁን ዓይነት ችግርና መከራ አይደርስባችሁም ነበር" በማለት የሕዝቡን ልብ ወደ ራሱ ለመሳብ ይሞክር ነበር። ይሁን እንጂ፤ የወሰደው እርምጃ አባቱን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም ደስ ስላላሰኘ፤ የተመኘውን በማግኘት ፈንታ ታላቅ እወዳደቅ ወደቀ። ብዙ የፖለቲካ ሰዎች *"የአቤሴሎምን ዘዴ (ቴክኒክ)"* በአሁኑ ጊዜ በሰፊው ሲጠቀሙበት እናያለን። የተወዳዳሪያቸውን ስም በማጥፋት፥ ያላደረገውን "አደረገ"፥ ያልሆነውን "ሆነ" በማለት፤ በውድድሩ አሸናፊ ሆነው ለመገኘት ከፍተኛ ትግል ሲያደርጉ ይታያሉ። ይህን ዓይነቱ ሁኔታ በዓለም ውስጥ በመሆኑ ይህን ያህል አይደንቀንም። የሚያሳስበን ግን ተመሳሳይ ሁኔታ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሆነ እንደ ሆነ ብቻ ነው።



እንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ከፖለቲካ ሰዎች ባላነሰ ሁኔታ *"የአቤሴሎምን ዘዴ (ቴክኒክ)"* በአሁኑ ጊዜ ሲጠቀሙበት ማየት ለእንዳንዶቻችን ይህን ያህል እንግዳ ነገር አይደለም። በአመራር፥ በትምህርት፥ ባለው የክርስትና ሕይወት ልምምድና በችሎታው ከእነርሱ የተሻለ የመሰላቸውን ሰው የሚዋጉበት የራሳቸው የሆነ ረቂቅ መንገድ አላቸው። እንደኛውና ትልቁ መንገዳቸው፥ ያ ሰው መሮትና ሰልችቶት ቤተ ክርስቲያኑን ጥሎ እስኪሄድ ድረስ ያልሆነውን "ሆነ" ያላደረገውን "አደረገ" ብሎ በማውራትና በማስወራት፤ ጠልተው ለማስጠላት የነቀፋ ዝናብ ያወርዱበታል። ሁኔታው መሮት "በቃኝ" ብሎ ጥሎ ከሄደ፥ "የእኛ ጌታ ከመካከላችን ነቀለልን" በማለት ትልቅ ሀቤት ያደርጋሉ። እውነተኛነት የሌላቸው እንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሮጠ መቅደም የማይችሉትን ሰው፥ መጥፎ ስም ለመስጠት፥ ጠልተው በማስጠላት ጠልፈው ሲጥሉት ይሞክራሉ። ይህን ዓይነቱ ዘዴ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያውያን መካከል በጣም እየተለመደ መጥቷል። ስዚህ ነው ችሎታውና ዕውቀቱ ያላቸው ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ሸሽተው ለብቻቸው መኖርን የመረጡት ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው። እንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ሰው ሁሉ የራሱ የሆነ አቋም ሳይኖረው፥ በማንኛውም ነገር እነርሱን እንዲመስል ይፈልጋሉ። በእምነታቸው፥ በሕይወት ፍልስፍናቸው፥ በአስተዳደር ስልታቸው የእነርሱን ካልመሰለ፥ ሌላውን እንደጠላት ስለሚያዩት ምክንያት እየፈለጉ ያንን ሰው ይነቅፉታል። እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች ግን ከእነርሱ የተለየ እሳብ ያለውን ሰው በማሳደድ ፈንታ፤ በተፈጥሮና በመንፈስ ቅዱስ ከተሰጠው የጸጋ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መታነጽ በአግባቡ ይጠቀሙበታል እንጂ "ለምን እንደ እኔ እልሆንከም፤ ለምን እንደ እኔ እላሰብከም? ለምን እኔን እልመሰልከም?" በማለት ያለአግባብ አይነቅፉትም።

## 2. ከመንቀፍ የተሻለ ሌላ ጥሩ መንገድ አለ

የመንቀፍ ልማድ ኀልቶ የሚታይባቸው ሰዎች ራሳቸውን ለመከላከል ሲሉ *"ዕርዳታ ለሚያስፈልገው ሰው አሳብ ወይም ምክር መስጠት የለብንም? የልጆቻችንን መጥፎ ባሕሪ ማረም ወይም ማስተካከል አንችልም? በእኛ ሥር ሆነው የሚሠሩትን ሠራተኞች አስፈላጊውን መመሪያ መስጠት የለብንም? ስሀተት መሆኑን ሲያወቅን፥ "አሜን! ልክ ነው" ብለን መቀበል አለብን እንዴ?"* ብለው መጠየቃቸው አይቀርም። ይህን ዓይነት ጥያቄ የሚያቀርቡ ሰዎች ስነቀፋና ሀሳብ በመስጠት መካከል ያለውን ልዩነት ካለመረዳት ነው ወይስ ራሳቸውን ለመከላከል ሲሉ የሚሰጡት ምክንያት ነው? እንዳንዶች የሚነቅፉበት ምክንያት ትክክል መሆኑን ለማሳመን ብቻ ያለእግባብ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል የሚጠቅሱ አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነብያት፥ እስተማሪዎች፥ ስባኪዎች ሕዝቡን በኃይል ይነቅፉ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን። ይሁን እንጂ፥ ነብያትና እስተማሪዎች ሕዝቡን ለምሳሌና እንዲሁም በልዩ ልዩ መንገድ የጽድቅን

መንገድ ካስተማሩትና ካስረዱት በኋላ "ዕምቢ" ቢሉ፥ እምቢታቸው አደጋ የሚያስከትል ባቸው መሆኑን በማስጠንቀቅ በኃይልና በሥልጣን ይናገራቸው እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። ኢየሱስ ነቃፊዎች እንዳንሆን አስጠንቅቆናል። ለምሳሌ በተራራው ስብከቱ፥ *"..ማንንም ሰው 'አንተ የማትረባ' ብሎ የሚሳደብ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ 'ደደብ' ብሎ የሚሳደብ ሁሉ ለገሃነመ እሳት ፍርድ የተገባ ይሆናል"* አለ (የማቴ. 5፥22)። እንዲሁም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ቁጥር 1 ላይ *"በእናንተ ላይ እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ"* አለ። መሳደብና መፍረድ፥ ሁለቱ "የነቀፋ" ክፍሎች ናቸው። ኢየሱስ እንዳንነቅፍ የሚያዘን ከሆነ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ላይ እንደምናየው ፈሪሳውያንን ለምን ነቀፋቸው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እርግጥ ነው ኢየሱስ ፈሪሳውያንና ጻፎችን በኃይል ነቅፏቸዋል። የነቀፋቸውም ያለ ምክንያት እንዲሁ አልነበረም። ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል ፈሪሳውያን ኢየሱስን ሲያሳድዱት ቆይተዋል። እነርሱን ለመመለስ፥ ወደ ትክክለኛው እምነት ለማቅናት ያልተጠቀመው መንገድ የለም። በማስተማር፥ ልዩ ልዩ ተአምራት እንዲያዩ በማድረግ ሊመልሳቸው ሞክሯል። ምንም ነገር ቢያደርግ እነርሱን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊያመጣቸው አልቻለም። በምድር የተመደበለትን አገልግሎት ጨርሶ በመስቀል ሊሞት የቀረው ትንሽ ጊዜ ብቻ ነበር። እነዚህ የእርሱ ጠላቶች የነበሩት ፈሪሳውያንና የአይሁድ መሪዎች በእርሱ ላይ ክስ ለመመስረት ምክንያት ይፈልጉበት ነበር። ሲነቅፋቸው፥ ያንን እንደ በደል ቆጠሩበት። ሊያጠፉት ምክንያት የሆናቸውና የቀሰቀሳቸው ይሄው ነው። ሌላውን ወደ እውነት ለማምጣት ሁሉን መንገድ ተጠቅሞ ውጤት አለማምጣቱን ሲያይ ለመጨረሻ ጊዜ ሞት እንኳን የሚያስከትልበትም እንኳን ቢሆን ያንን መንገድ ተጠቀመበት።

በአሁኑ ዘመን ላለነው ሰዎች፣ ተሳስቶ የሄደ የሚመስለንን ለመመለስና ለማስተካከል፣ እንዲለወጥ የምንፈልገውን ሰው ከመንቀፍ ውጪ ሌላ ጠቃሚ የሆነ መንገድ (ዘዴ) ይኖረን ይሆን?

## 2.1. በመንቀፍ ፈንታ፥ ሌላውን ሰው እንዳለ መቀበል

ኢየሱስ "ኃጢአትን" ይጥላ እንጂ፥ ኃጢአተኛውን አይጠላም። ይሁዳ አስቆሮቱ የልቡን ክፋት ቢያውቅም፥ ከደቀ መዛሙርቱ እንደ አንዱ አድርጎ እንደመረጠው፣ ልቡን እንዲያስተካል እስከ መጨረሻው ድረስ ዕድል በጥቶት እንደነበረ እናውቃለን። የልቡን ሁኔታ ማቴዎስ በአይሁዳውያን ዘንድ በጣም የተጠላ ቀራጭ ቢሆንም፣ የልቡን ሁኔታ በደንብ የሚያውቀው ጌታ፥ ደቀ መዝሙሩ አድርጎ ተቀበለው። ጴጥሮስም ኢየሱስን "ፈጽሞ አላውቀውም" ብሎ ቢክደውም፣ ለጴጥሮስ ሁለተኛ ዕድል ሰጠው። ኢየሱስ የመጣው ከኃጢአታችን ሊያድነን ቢሆንም፥ ነቀፌታን የማዳኛ መንገድ አድርጎ አልተጠቀመበትም። ሌሎችን መቀበል ማለት ምንም ዓይነት ለውጥ ሳያሳዩ፥ ልክ እንዳሉ



መቀበል ማለት ነው። መንፈሳዊ መሪ የሚመራውን ሰው "በምታደርገው ነገር አልስማማም፤ አንተን ግን እንዳለህ እቀበልሃለሁ" የማለት አቅም ሊኖረው ይገባል። በመንቀፍ ፈንታ ሰዎችን እንዳሉ ስንቀበላቸው፥ የመለወጥ ተስፋቸው ሰፊ ነው። ስንነቅፍ፥ ሌላውም መልሶ ይነቅፈናል፤ እንዳለ ስንቀበለው ግን፥ እኛንም ይቀበለናል። ነቃፊን ስንነቅፈው፥ እኛንም በተራው በነቀፋው መልሶ ይነቅፈናል። ኢየሱስ እኛን ልክ እንዳለነው እንደተቀበለን እኛም ሌሎችን ልክ እንዳሉ መቀበል መቻል አለብን። ሌላውን ለመለወጥ ከፈለግን፥ በቅድሚያ በመሸሸ ፈንታ እንዲጠጋን ማድረግ አለብን። ወደ እኛ እንዲቀርበን ካላደረግነው ልንለውጠው አንችልም። ሰዎች እንዳሉ ከማይቀበሏቸው ሰዎች ጋር ህብረት ማድረግ አይፈልጉም።

የሚወደን ልክ እንዳለነው ይቀበለናል፤ የሚጠላን ግን በትንሹም በትልቁም ምክንያት እየፈለገ ሁልጊዜ ይነቅፈናል። መለወጥ የሚያስፈልገን ከሆነ፣ ስለ ወዳጆችን እንጂ ስለ ጠላታችን ስንል አንለወጥም። ነቀፋ ሲያበላሽ እንጂ ማንንም ሲያለማ አላየንም። ነቀፋ በዎችን ከነበሩበት የባሰ መጥፎ እንዲሆኑ ሲያደርጋቸው፥ እንዳሉ ሲቀበሏቸው ግን ሌላው ቢቀር መወደዳቸውና መፈለጋቸውን ስለሚያሳያቸው በመሸሸ ፈንታ ፍቅር ወዳ ሳያቸው ሰው ይጠጋሉ። ሰዎች መወደዳቸውን ሲያውቁ፥ ከውስጥ መለወጥ ይጀምራሉ። እግዚአብሔርም የሚጠቀምበት መንገድ ይህን ዓይነቱን ነው። መንፈሳዊ መሪዎችም ይህንኑ መንገድ ቢጠቀሙ በአመራራቸው ጥሩ ውጤት ያስገኝላቸዋል። እርግጥ ነው አንዳንድ ሰዎችን መቀበል ቀላል አይደለም። ችግራችን ብዙ ጊዜ የምናተኩረው በሰዎች ላይ በመሆን ፈንታ፣ በሚያጠፉት ጥፋት ላይ ብቻ ስለሚሆን ነው። "የምታደርገውን አልወደውም፤ አንተን ግን እወድሃለሁ" የሚለውን መልዕክት ማስተላለፍ መቻል አለብን። በሰው ድካም ላይ ብቻ ትኩረት የሚሰጡ ሰዎች፥ ያ ደካማ የተባለው ሰው፥ ምንም ያህል ጥሩ ነገር ቢሠራ፥ የሚሠራውን ጥሩ ነገር ማየት አይችሉም። አንዴ ከሰረቀ፥ ሁል ጊዜ ሌባ ነው ብለው የሚያምኑ በዎች አሉ። ሰዎችን እንዳሉ መቀበል በንልፉ በኃጢአት ውስጥ ሲኖር የሚያዩትን ክርስቲያን፣ ከዚያ ሰው ጋር በሰላም ለመኖር ሲሉ ብቻ ዝም ይበሉ ማለታችን አይደለም።

## 2.2. በመንቀፍ ፈንታ ትክክለኛ የሆነውን ማስተማር

በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ክርስቲያኖች በቅድስና መኖር እንዳለባቸው አያስተምሩም። *"በጸጋ ስለዳኑ ከዚህ ውጪ ይህን አድርግ፥ ያን አታድርግ የሚል ሸክም አንጫንባቸውም"* የሚለው ትምህርት እያየለ መጥቷል። በቅድስና የሚያምን መንፈሳዊ መሪ (መጋቢ) አማኞች በኃጢአት ውስጥ ሲኖሩ፥ ለምሳሌ በሕግና በስርዓት ካላገቡት ሰው ጋር አንድ ቤት ሲኖሩ፥ አንድ አልጋ ላይ ሲተኙ እያየና እያወቀ ዝም ቢል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂነት እንዳለበት ስለሚያምን፥ "ቅር እንዳይሰኙብኝ፥ እንዳይቀየሙኝ" በማለት ዝም ሊል አይገባም። በግልም ሆነ ከመድረክ ላይ ስለ ቅድስና

የመስበክና የማስተማር ግዴታ አለበት። ይህን በማድረጉ መንፈሳዊ መሪው (መጋቢ) ዋጋ እንደሚያስከፍለው፣ "የሰበከው፣ ያስተማረው እኔን ለመንካት ብሎ ነው" በማለት እንደሚያስወቅሰው፣ አንዳንዶቹም ጠላት እንደሚሆኑበት ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ፣ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ከሆነ፣ *"ከሰው ጋር ተስማምቼ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቼ ከምኖር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምቼ ጥቂት ሰዎች ቢጠሉኝ ይሻለኛል"* የሚለውን አሳብ ይመርጣል። "ነቀፋ" በአግባቡና በሥርዓት ከሆነ፣ ይጠቅማል እንጂ፣ አይጎዳም። መስመሩን ያልለቀቀ፣ በጥላቻ ከተሞላ ልብ የወጣ አይሁን እንጂ፣ ቅድስናን በቤተ ክርስቲያን ለማምጣት መንፈሳዊ መሪ በጥበብና በፍቅር ጌታን እንዲመስሉ፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የሚያሳድግላቸውን ቃል አይናገር፣ አያስተምር ማለት እንዳልሆን ልናውቅ ይገባል።

ኢየሱስ የተራራውን ስብከት ሲጀምር፣ *"እናንተ ክፉ ሰዎች"* በማለት ፈንታ፣ *"በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው..."* (የማቴ. 5፥1) አለ። እንዲህም ሲል ብጹዓንነት የሚጀምረው ፍጹም አለመሆናቸውን አውቀው እርዳታ ሲፈልጉ እንደሆነ ለመግለጽ ነው። አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን ችግር ውስጥ የሚከቱት ካለማወቃቸው የተነሳ ብቻ ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹን እውነቱን ወይም ትክክለኛውን ማስተማር እንጂ፣ መንቀፉ አይጠቅምም። በማስተማርና በመንቀፍ መካከል ትልቅ ልዩነት እንዳለ መረዳት አያቅተንም። ከተወሰነው ፍጥነት በላይ የሚነዳውን ልጃችንን፣ *"መኪና ማንም ተራ ሰው መንዳት ስለሚችል፣ መኪና መንዳት መቻልህ ይህን ያህል ለዋቂ አያሰኝህም። እንዲሁም ከተወሰነው ፍጥነት በላይ መንዳትህ 'እዩልኝ ባይ' መሆንህን እንጂ ጀግና አያሰኝህም"* ብንለው በነቀፋችን ስሜቱን ጎዳነው እንጂ አላስተማርነውም። ይህን ከማለት ይልቅ፣ *"ስትነዳ በጣም ትፈጥናለህ። መፍጠንህ ጉዳት አለው። ቀስ ብለህ ብትነዳ 1ኛ፣ ነዳጅ ብዙ አታቃጥልም፣ 2ኛ፣ መኪናህ ዕድሜ ይኖረዋል፣ 3ኛ፣ አብረውህ የሚሄዱ ሰዎች አደጋ ይደርስብናል ብለው በለማይሰጉ ደስ ታሰኛቸዋለህ፣ 4ኛ፣ በራስህም ሆነ በሌሎች ላይ አደጋ አታደርስም"* ብንለው፣ በቀስታ መንዳት የሚያመጣውን ጥቅም አስተማርነው ማለት ነው። ስለዚህ መንፈሳዊ መሪ ከመንቀፍ ይልቅ ትክክለኛውን ነገር ማስተማር አለበት። ውሸት የሚያወራውን ሰው "ውሸታም" ከማለት ይልቅ፣ ክርስቲያን እውነትን መናገር እንዳለበት ማስተማሩ፣ ውሸት አውሪውን ማረምና ማስተካከል ያስችላል።

## 2.3. በመንቀፍ ፈንታ መወያየት

ኢየሱስ በመወያየት ያምናል። እውነተኛ ቢሆንም፣ አምላክ በመሆኑ የእርሱ ሃሳብ ከሰዎች ሃሳብ የተሻለና የበለጠ መሆኑን ቢያውቅም፣ "አትጠይቁኝ፤ አትከራከሩኝ" አይልም ነበር። አንድ ጊዜ አንዲት ግሪካዊት ሴት ልጇዋ በእርኩስ መንፈስ ተይዛባት ከኢየሱስ እርዳታ ለመለመን መጣች። ኢየሱስም ጥያቄዋን በምቶ ***"የልጆችን ምግብ ወስዶ ለውሾች መስጠት አይገባም"*** (የማር. 7፥27) በማለት መልስ ሰጣት። ይህን ሲል *"የተጠራሁት ለአ*



***ይሁዳውያን ነው"*** ማለቱ ነበር። ሴትዮዋም ያለው ገብቷት፣ ***"አዎን ጌታዬ ታዲያ እኮ ውሾችም በገበታ ሥር ሆነው ከልጆች የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ'*** ስትል መለሰችለት (የማር. 7፥28)። ኢየሱስ ከሴትየዋ ጋር የነበረውን ውይይት አልጠላውም። "እምነትሽ ታላቅ ነው" በማለት ካደነቃት በኋላ ለልጇ የጠየቀችውን ፈውስ ሰጣት። እግዚአብሔርም ውይይትን አይጠላም። ***"ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ ባለቀይ ቢቀላ እንደ በረዶ ይነጻል፤ እንደ ደም ቢቀላም እንደ ባዘቶ ነጭ ይሆናል"*** ይላል (ኢሳ. 1፥18)። እግዚአብሔር መወያየትን፣ መወቃቀስን የማይፈራ ከሆነ፣ ሰዎች ውይይትን የሚፈሩበት ምክንያት ለምን ይሆን? ኢየሱስ ገና የ12 ዓመት ወጣት ልጅ በነበረበት ወቅት በቤተ መቅደስ ተገኝቶ ጥያቄ ሲጠይቅ፣ እንዲሁም ለሚጠየቀው ጥያቄ መልስ ይሰጥ እንደነበረ እናስታውሳለን። የራሱን አሳብ መናገር፣ "እኔን ብቻ ስሙኝ" የሚል ሳይሆን፣ ተቃዋሚዎች አሳባቸውን እንዲገልጹ፣ ጥያቄ ቢኖራቸው እንዲጠይቁ ዕድል ይሰጣቸው ነበር። ሕዝብ በተሰበሰበበት ነጻ ሆኖ ይከራከራቸውና ይከራከሩት ነበር። የሞት ፍርድ ሲፈርዱበት በፈራጆቹ ፊት በቀረበበት ወቅት ስለ ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ተጠይቆ ሲመልስ ***"እኔ ለዓለም በግልጽ ተናገርሁ፤ አይሁድ በተሰበሰቡበት ምኩራብና በቤተ መቅደስም ሁልጊዜ አስተማርሁ፤ በስውር የተናገርሁት የለም"*** አላቸው (የዮሐ. 18፥20)። ኢየሱስ ያስተምርና ይሰብክ የነበረው በግልጽ ስለነበረ፣ መከራከርም ሆነ ሊጠይቅ ለሚፈልግ ሁሉ ዕድሉን ይሰጥ ነበር። "ውይይት" በሰዎች መካከል ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር፣ እንዲሁም ሰዎች የሚሰማቸውን ስሜት እንዲገልጹ ያስችላቸዋል።

ብዙ ጊዜ ሰዎች በሌላው ላይ የሚፈርዱት፣ አስተያየት የሚሰጡት፣ ነቀፋም ካላቸው የሚነቅፉት፣ አንዱን ወገን ሰምተው፣ "አጠፋ" የተባለው ሰው የሚሰጠውን ገለጻ ሳይሰሙ፣ አንዳንዶም የአሉባልታ ወሬ ሰምተው ይሆናል። ይሄ ብዙ ጊዜ መንፈሳዊ መሪዎችን ችግር ላይ ሲጥላቸው እናያለን። በህጻንነቴ ትክክል ባልሆነ ምክንያት የተቀጣሁትን ምክንያት ፈጽሞ አልረሳውም። አንዲት የጎረቤት ሴት፣ የጠፋባትን ሞረድ እንደሚገባው ሳትፈልግ፣ እናታችን ዘንድ መጥታ "ሞረዴን አጣሁት፣ እዚህ አካባቢ ካንቺ ልጆች በስተቀር ወፍ ዝር አላለምና፣ የወሰዱት ያንቺ ልጆች ናቸው" አለቻት። እናታችንም እኛ መውሰዳችንን ሳትጠይቅ፣ ወይም "እነዚህ ልጆች የቢላ ሞረድ ምን ሊያደርግላቸው ይወስዳሉ?" ብላ ራሷን ሳትጠይቅ፣ "ልታሰድቡኝ ነው?...." ብላ ሰውነታችን እስኪደማ ድረስ ባርጩማ ገረፈችን። በማግስቱ ጥዋት ያቺ የጎረቤት ሴት፣ ጠፋ ያለችውን ሞረድ ፍራሿ ሥር ማስቀመጧን ረስታ እንጂ፣ ያልጠፋ መሆኑን ለእናታችን መጥታ ነገረቻት። እናታችንም በአንራችን ልጆችን ይቅርታ የመጠየቅ ባህል ስለሌለ፣ ይቅርታ ሳትጠይቀንም፣ "ልጆቼን ያለአግባብ ገረፍኳቸው" በማለት ሳታዝን እንዳልቀረች እገምታለሁ። እናታችን ለቀረበብን ክስ እኛ የምንሰጠው መልስ ምን እንደሆነ ሳትሰማና የመናገር ዕድል ሳትሰጠን፣ በግርፋት አንድንቀጣ ፈረደችብን።

ውይይት ማለት "መስማት–መናገር፣ መናገር–መስማትን" ያካተተ ነው። አንዱ ሰሚ፣ ሌላው አዳማጭ ብቻ ከሆነ "ውይይት" አይባልም። ሰዎች የመወያየት ዕድል ቢሰጣቸው፣ ከችግራቸው ውስጥ ለአብዛኞዎቹ መፍትሄ ማግኘት ይችሉ ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነትነት ያላቸውና የሌላቸው ብዙ ዓይነት ወሬዎች ይወራሉ። መንፈሳዊ መሪው (መጋቢው) በየጊዜው የሚነፍሰውን ወሬ ሰምቶ "አጠፋ" የተባለውን ሰው የነቀፋ አስተያየት ቢያሰማ፣ የሰጠው አስተያየት ወይም ነቀፋ ተመልሶ ከተነቀፈው ሰው ጆሮ ሲደርስ፣ "ይህን ዓይነት አስተያየት የሚሰጠው፣ በእኔ ወገን ያለውን መቼ ሰማና ነው" በማለት ሌላው ቅሬታ እንዲኖረው ያደርጋል። መንፈሳዊ መሪ ከመንቀፉ ወይም አስተያየት ከመስጠቱ በፊት የተነቀፈው ሰው የሚለውን መስማት አለበት። "ሽማግሌው እከሌ፣ ሚስቱን ደበደበ" የሚል ወሬ ቤተ ክርስቲያን ሲወራ፣ ወሬው ዞሮ ዞሮ በፓስተሩ ሚስት አማካኝነት ከፓስተሩ ጆሮ ይደርሳል። ፓስተሩ ሁኔታውን ሳያጣራ፣ የሚመለከተውን ሰው ሳያነጋግር፣ አንድ ዕሁድ ከስብከቱ መጨረሻ ላይ፣ "... እከሌ ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የማይጠበቀውን በማድረጉ፣ ከሽምግልና ወርዷል.." ብሎ ያውጃል። ለዚያ ሽማግሌ ቅርብ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች፣ የቀረበበት ክስ እውነትነት የሌለው መሆኑን የሚያውቁ ተናደው፣ እነርሱም በተራቸው "ለምን ይህን ታደርጋለህ?" ብለው ሳይጠይቁትና ሳያነጋግሩት፣ ቤተ ክርስቲያኑን ጥለው ይወጣሉ። መውጣት ብቻ ሳይሆን፣ የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን ይጀምራሉ። አንዳንዶች ቤተ ክርስቲያኑን ጥለው የወጡትን ተከትለው ይሄዳሉ። በዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ትከፈላለች። በአሁኑ ዘመን በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች መካከል ቤተ ክርስቲያን የምታድገው "በማባዛት" ሳይሆን፣ "በማካፈል" መሆኑ ስለታወቀ፣ የቤተ ክርስቲያን መከፈል ብዙዎቹን አያስደንቅም። ከላይ እንዳየነው፣ የዚህ ሁሉ ችግር ዋና ምክንያት፣ የመንፈሳዊ መሪው (የመጋቢው) ማስተዋል ማጣት ነው። ሁለቱን ወገን ሳይሰሙ፣ አንዱን ወገን ብቻ ሰምቶ መፍረድ ከፍተኛ ስህተት ላይ ይጥላልና በቤተ ክርስቲያን ደረጃም ሆነ በግል ሕይወት ችግር እንዳይደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። የሚመለከተውን ሰው ጠርቶ ማነጋገር፣ ሌላውን አላግባብ ከመንቀፍና ከመፍረድ ያድነናል። መንፈሳዊ መሪ በመንቀፍ ፈንታ፣

ሌሎችን ከነድካማቸው የመውደድና የመቀበል ልብ ይኑረው።

ጊዜ ወስዶ ትክክለኛውንና እውነቱን ያስተምራቸው።

ሌላውን ወገን ሳይሰማ ፈራጅ እንዳይሆን፣ ጠይቆ ለመረዳት ጊዜ ይውሰድ።

የተሳሳተውን ለማስተካከል እንጂ፣ የሰውን ድካም ለመግለጽ አይሁን።

ድካማቸውን ብቻ ሳይሆን፣ብርታታቸውንም ያሳያቸው።

በጌታ ፊት በጸሎት ያቅርባቸው።



## 3. መንፈሳዊ መሪ "ነቀፋን" ታግሶ ማለፍ መቻል አለበት

መንፈሳዊ መሪ የሚመራቸውን ምዕመናን ለማረምና ለማስተካከል፣ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ተመልክተናል። በዚህኛው ክፍል ደግሞ ራሱ የሚደርስበትን ነቀፋ እንዴት ታግሶ ማለፍ እንዳለበት እንመለከታለን። መንፈሳዊ መሪ ነቀፋ ሲደርስበት ነቀፋውን ለመቋቋም ምን ማድረግ አለበት?

### 3.1. ከነቀፋ ምንጊዜም ነጻ መሆን እንደማይችል ማወቅ አለበት

በዓለም ውስጥም ሆነ በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ ያለ ማንኛውም መሪ፣ ከነቀፋ ነጻ አይደለም። "ማንም እንዳይነቅፈኝ" በማለት ነቃፊዎችን ማስቆም ስለማይችል፣ የሚደርስበትን ነቀፌታ እንዴት ታግሶ ማለፍ እንዳለበት፣ እንዲሁም የሚሰነዘርበትን ነቀፌታ ለጥቅሙ እንዴት ማዋል እንዳለበት ማወቅ አለበት። መንፈሳዊ መሪ የሚያገለግላቸውን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ማስደሰት ስለማይችል፣ ምን ጊዜም ቢሆን የሚነቅፉት ሰዎች አይጠፉም። በዚህ ዓለም ላይ "ነቃፊና ተነቃፊ" ሰው እስካለ ድረስ፣ እንከን የማይገኝበት እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ ሥራ ቢሠራም፣ መንፈሳዊ መሪ በአንድም ሆነ በሌላ መነቀፉ አይቀርም። የዚህን እውነተኛነት ለማሳየት አንድ ጸሀፊ ጥሩ አድርጎ አቅርቦታል።

*"ገንዘብ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግ ከታየ፣ 'የገንዘብ ፍቅር ያሰከረው ነው' ይባላል። ገንዘብ ለማግኘት ባይጥር ደግሞ 'ህሞቱ የፈሰሰ ሰነፍ ነው" ይባላል። ገንዘቡን ቢያጠራቅም 'ንፉግ' ይባላል። በማጠራቀም ፈንታ ቢያጠፋው 'ገንዘብ አባካኝ' ይባላል። ደሃ ቢሆን 'የማይሰራ ሰነፍ' ይባላል። ሀብታም (ባለጸጋ) ቢሆን፣ 'ሀብታም የሆነው አጭበርብሮ ነው' ይባላል። ቤተ ክርስቲያን ቢሄድ፣ 'ግብዝ' ይባላል። ቤተ ክርስቲያን ባይሄድ 'ኃጢአተኛ ነው' ይባላል። በወጣትነት ዕድሜው ቢሞት፣ 'ወደ ፊት ትልቅ ዕድል ነበረው' ይባላል። ዕድሜ ጠግቦ በእርጅናው ዘመን ቢሞት፣ 'ለሕብረተሰቡ ሸክም ነበር' ይባላል። ነቀፋ ያልደረሰበት ሰው ቢኖር፣ ያ ሰው በዚህ ዓለም ውስጥ ገና ያልተወለደ መሆን አለበት" አለ።*

ይህን እውነት የተረዳ መንፈሳዊ መሪ፣ ደስታውንና ሰላሙን ለመጠበቅ፣ ምንም ያህል ጥሩ አድርጎ በመሥራት አገልግሎቱን ለመፈጸም ቢሞክር፣ ነቃፊዎች ምን ጊዜም እንደማይጠፉ ማወቅና መቀበል አለበት። የታወቀው ሰባኪ የነበረው ዲ. ኤል. ሙዲ ከአንድ ትልቅ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስብከቱን ጨርሶ ሊወጣ ሲል፣ አንዱ ጠጋ አለና ትምህርቱን ካደነቀ በኋላ፣ *"ይቅርታ አድርግልኝና በስብከትህ ውስጥ አሥራ አንድ የሰዋስው ስህተቶችን ፈጽመሃል"* አለው። ዲ. ኤል. ሙዲም ለጥቂት ሰከንድ ጸጥ ብሎ

*ካሰበ በኋላ፥ "እውነትህን ነው፤ ተሳስቼ ይሆናል። መሠረታዊ ትምህርቴ ይህን ያህል ጠንካራ አይደለም። ይሁን እንጂ፥ ክርስቶስን ለማገልገል የማውቀውን ለዋሰው ሁሉ ተጠቅሜአለሁ። አንተስ ችሎታህን ለጌታ አገልግሎት ምን ያህል ተጠቅመህበታል?"* ብሎ ጠየቀው።

## 3.2. የተነቀፈበትን ነቀፋ መገምገም አለበት

ነቀፋ ያስቆጣል እንጂ ማንንም ደስ አያሰኝም። ይሁን እንጂ፥ መንፈሳዊ መሪ በነቃፊው ላይ ከመቆጣቱ በፊት ቆም ብሎ ማለብና ረጋ ብሎ ራሱን አንዳንድ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለበት። ነቀፋው ተገቢ መሆኑና አለመሆኑን፥ በፍቅር መንፈስ የመጣ መሆን አለመሆኑን መመርመር አለበት። ነቀፋው ምን ያህል እውነት ነው፣ አስፈላጊ ነው ወይ፣ አግባብ ያለው ነው ወይ፣ በምን ዓይነት መንፈስ የተወረወረ ነው፣ በማለት ራሱን መጠየቅ አለበት። ልቡ በንዴት ከተሞላ፥ ለነቃፊዎች አግባብ ያለው መልስ ለመስጠት እንኳን አቅም ያጣል። የተሰነዘረበት ነቀፋ አግባብነት የሌለው ከሆነ፥ ችላ ብሎ ማለፍ መቻል አለበት። ብዙ ጊዜ ሰዎች በኃይል ሲናደዱና ራሳቸውን ለመከላከል ሲሞክሩ፥ ሌላው ቀርቶ ሊረዷቸው የሚሞክሩትንም ሰዎች ሳያውቁ የመጉዳት ዝንባሌ እንዳላቸው የታወቀ ነው። ያም የበለጠ መራራ ያደርጋቸዋል። አንዳንድ ሰዎች ነቀፋ ካልደረሰባቸው፤ "ሁሉም መልካም ነው" በማለት ይዞታቸውንም ሆነ ድካማቸውን ለማወቅ ምንም ዓይነት ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም። ነቀፌታው ትክክል ይሁንም አይሁንም፥ የሰሙት ነቀፌታ ድካማቸውን እንዲመረምሩ ካደረጋቸው፤ በማዘን ፈንታ ደስ ሊላቸው ይገባል።

## 3.3. ለተነቀፈበት ነቀፋ መልስ ለመስጠት መቸኮል የለበትም

ነቀፋ እንደጦር በኃይል ይወጋል። ቶሎ መልስ ለመስጠት ከሞከርን፥ የተወረወረብን ጦር ወደ ውስጣችን ሰርጉዶ በመግባት የበለጠ እኛኑ ይጎዳናል። "ጥርስን በጥርስ፥ ዓይንን በዓይን" ብለን ምላሽ ለመስጠት፥ ወይም ራሳችንን ለመከላከል ከሞከርን፥ መጠገን እስከማይቻል ድረስ ሌላውን ከመጉዳት ወደ ኋላ አንልም። የሚጠላን ሰው ጎጂ የሆነ ነቀፋ በመወርወር ሊያጠቃን ሲሞክር፥ ለነቀፋው አጸፋውን ለመመለስ፥ የወጋንን ሰው መልሰን "በነቀፋ ጦር" በመውጋት ፈንታ "ራስን የመቆጣጠር ጋሻ" ማንሳቱ ወይም መጠቀሙ የተሻለ ይሆናል። ምንጊዜም ቢሆን በችኮላ መልስ ለመስጠት መሞከር ጎጂነት አለው። ምክንያቱም በችኮላ የምንመልሰው መልስ ብዙ ጊዜ ስህተት ላይ ሊጥለን ስለሚችል ነው። ነቀፋ ሲደርስብን፥ አጸፋውን ለመመለስ በመሞከር ፈንታ "ነቀፋው ይጠቅመኛል ወይስ ይጎዳኛል?" በማለት ረጋ ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። ለጥቅማችን ከሆነ ከውስጣችን ተቆርጦ መውጣት ያለበትን እንዲቆርጥ እንፍቀድለት። እኛን ለመጉዳት የተወረወረ የነቀፋ ጦር ከሆነ፥ ወደ ውስጣችን እንዲገባ እንፍቀድለት። መገንባት ጊዜ



ይፈጃል ማፍረስ ግን በጣም ቀላል ነው። ነቃፊዎች ሲነቅፉ አጿራጩን መንገድ መጠቀማቸው ነው። ቸኩለን እርምጃ ባለመውሰድ፥ የጥቃት እርምጃቸውን እናዘግይባቸው።

## 3.4. ነቀፋውን ለጥሩ ነገር ይጠቀምበት

ነቀፋ፥ "መራራ" ወይም "ጣፋጭ" ሊያደርገን ይችላል። ነቀፋውን ስንሰማ፥ "ጊዜያቸውን ሰውተው ማወቅ ያለብኝን ነገር እንዳውቀው ማድረጋቸው፥ እንዴት ዓይነት ጥሩ ሰዎች ቢሆኑ ነው?" ማለት እንችላለን። ይሄን ዓይነቱ አመለካከታችን ጣፋጭ እንድንሆን ያደርገናል። ነቀፋ መትቶ የሚጥለን፥ ወይም ገፋ-ገፋ አድርጎ ወደ ፊት እንድንሄድ የሚያደርገን ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ነቀፋ ሲደርስባቸው፥ የተነቀፉበት ነገር ልክ አለመሆኑን ለማስመስከር ጥሩ አድርገው ይሠራሉ። ያም ዕድገታቸውን ያፋጥነዋል። ቴዲ ሩዝቬልት (Teddy Roosvelt) በልጅነታቸው "ባለ አራት ዓይን" እንዲሁም "ሴታ ሴት" የሚል የቅጽል ስም ተሰጥቷቸው የሚሳቅባቸውና የሚቀለድባቸው ልጅ ነበሩ። የጓደኞቻቸው መሳቂያ በመሆናቸው በመመረርና በማዘን ፈንታ፤ በአካል ተሟልተው በኃይል በመሥራታቸው፥ ራሳቸውን ለማሳደግ በመቻላቸው "የአሜሪካ ፕሬዝደንት" ለመሆን በቁ። በዚህ ዓይነት ነቃፊዎቻቸውን ማሳፈር የቻሉ ታላላቅ ሰዎች በዓለም ላይ ብዙዎች መጥተው ዘመናቸውን ጨርሰው አልፈዋል። ቁም ነገሩ ያለው "የሰዎች ነቀፋ ወደ ፊት እንዲሄድ ያደርገኛል እንጂ፥ ወደ ኋላ አይጎትተኝም" የሚለው ውሳኔ ላይ ነው። መንፈሳዊ መሪ ነቃፊዎቹ በሚወረውሩበት ነቀፋ ተሰነፉ ቆርጦ አገልግሎቱን አቋርጦ በመውጣት ፈንታ፥ ነቀፋውን ለጥቅሙ ሊያውለው ይገባል። የተነቀፈበት ነገር እውነት ከሆነ፥

*መራራ ቢሆንም፥ እውነቱን እንዳለ ይቀበል።*

*ራሱን ለመከላከል ሲል በመዋሸት ፈንታ፥ ስለ ድካሙ ንስሀ ይግባና ራሱን ያስተካክል።*

*ድካሙን የነገረውን ሰው በመጥላት ፈንታ፥ ከልቡ ያመስግነው።*
*ወዲያው መለወጥ የሚችለው ነገር ከሆነ ወዲያው ይለወጥ።*
*መለወጥ ካልቻለ ራሱን ከመራራነትና ከተበታይነት ይጠብቅ።*

*ለመለወጥ ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ፥ የመለወጥ ዕቅድ ያውጣ።*

*በቀላሉ ተሰነፉ እንዳይቆርጥ የተነቀፈበትን ብቻ ሳይሆን፥ ያገኘውንም መልካም አስተያየት ይቁጠሩ።*

*"ካላወቀው ይህን ዓይነት ስህተት እሠራለሁ" በማለት በራሱ ስህተት መሳቅን ይለማመድ።*

መንፈሳዊ መሪዎች፣ ጥሩ መሪ ለመሆን ሲነቀፉ፣ እውነቱን ለመቀበል፥ አስተያየታቸውን ለለገሷቸው ሰዎች ምስጋናቸውን ይግለጹ። ራሳቸውን ለማሻሻል፥ ልባቸውን ከመራራነት ለመጠበቅና በራሳቸው ስሁተት ለመሳቅ ፈቃደኞች ይሁኑ። በመጨረሻ "የማይነቀፍ፣ የማይሠራ ሰው ብቻ መሆኑን" ይወቁ። ኤ. ደብሊው. ቶዘር ፤

*"ሀቀኛ (እውነተኛ) የሆነውን ነቀፋ አትፍራ። ነቃፊህ ተሳስቶ እንደሆነ፥ ትረዳዋለህ። አንተ ተሳስተህ እንደሆነ፥ እርሱ ይረዳሃል። በዚህም ሆነ በዚያ አንድ ሰው ዕርዳታ ማግኘቱ አይቀርም" አለ።*

## 4. እግዚአብሔርን እንጂ፥ ነቃፊዎችን አንፍራ

አንድ ቀን ሁላችንም እንድናገለግለው በጠራን ጌታ ፊት እንቆማለን። ጳውሎስ *"ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ እያንዳንዱም ሰው በሥጋው ለሠራው በጎ ወይም ክፉ ሥራ ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል። እንግዲህ ጌታን መፍራት ምን ማለት እንደ ሆነ ስለምናውቅ፥ ሰዎች የምንናገረውን እንዲቀበሉ ለማድረግ እንጥራለን። የእኛ ማንነት በእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጠ ነው፤ ደግሞም በኅሊናችሁ ዘንድ ግልጽ ነው ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ"* አለ (2 ቆሮ. 5፥10-11)። የጠራንን ጌታ ለመገናኘት ዝግጁ እንሆን? ዘማሪው *"እክብሮት በተሞላበት ፍርሃት እግዚአብሔርን አገልግሉት፤ በመንቀጥቀጥም እርሱን ፍሩት"* (መዝ. 2፥11) ይላል። እግዚአብሔርን ደስ ብሎን እንድናገለግለው ይፈልጋል። *"እግዚአብሔርን በደስታ አገልግሉት..."* (መዝ. 100፥1) ይላል። በደስታ እንድናገለግለው ብቻ ሳይሆን "በመንቀጥቀጥ እርሱን እንድንፈራው" ይላል። ፍርሃትና ደስታ አብሮ ስለማይሄድ ይሄ እንዴት ሊሆን ይችላል ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እርግጥ ነው ደስታችን ሚዛኑን እንዳይለቅ "በፍርሃት" ካልተገታ፥ አገልግሎታችን በቀ ላሉ መሥመሩን ሰቶ ሊያወጣን ይችላል። በጌታ የምናገኘው ደስታ የሚያድገው ከእግዚ አብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ሲሆን፥ ፍርሃታችን ደግሞ የሚመነጨው ከእርሱ ከተቀበል ነው የኃላፊነት ስሜት ነው። በአገልግሎት ውስጥ "ፍርሃትና" እንዲሁም "ደስታ" ጠላቶች ሳይሆኑ፥ አብረው የሚሄዱ ናቸው። የሚሰጠን ኃላፊነት ደስታ የሌለበት ከሆነ፥ አገልግ ሎት ባርነት ይሆናል። እንዲሁም አገልግሎት፥ ፍርሃት የሌለበት ደስታ ብቻ ከሆነ፥ እገ ልግሎቱ ጥልቀትና እንዲሁም ዕድገት የሌለበት ይሆናል። ኢየሱስ የሚጠራን ወዳጆቼና እንዲሁም ባሪያዎቼ ብሎ ነው (የዮሐ. 15፥14-15)።

መርሳት የሌለብን እውነት፥ ለምንሰጠው አገልግሎት የመጨረሻው ፈራጃችን እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መረዳታችን፣ ሰውን እንዳንፈራ፥ ወይም እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት ፋንታ ሰውን ደስ ለማሰኘት እንዳንሞክር ይጠብቀናል። ሰውን ሁሉ ማስደሰት



ስለማንችል፥ ራሳችንን ማድከም የለብንም። ዋናው ዓላማችን እግዚአብሔርን ብቻ ደስ ለማሰኘት መሆን አለበት (1 ተሰ. 4፥1)። ከራሳችን ልምምድ እንደተረዳነው ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ማስደሰት ይቀላል። እርሱ ውስጣችንን በደንብ ስለሚያውቅ፥ በጣም ስለሚወደን፥ ሥራችንን በሀቅ ወይም በእውነት ይመዝናል። ጌታን ለማገልገል የተነሳ ሰው በወዳጆቹም ሆነ በጠላቶቹ ይነቀፋል። በሌሎች መነቀፋችን ብቻ ሳይሆን፥ እኛም ራሳችን የምንነቅፍ መሆናችንን መዘንጋት የለብንም። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ *"ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ለፍርድ ከመምጣቱ በፊት በማንም ላይ አትፍረዱ፤ እርሱ በሚመጣበት ጊዜ በጨለማ የተሰወረውን ምስጢር ወደ ብርሃን ያወጣዋል፤ ሰዎች በልባቸው የደበቁትንም አሳብ ይገልጠዋል፤ በዚያን ጊዜ እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ተገቢውን ምስጋና ያገኛል"* (1 ቆሮ. 4፥5) ሲል የሰጠውን ማስጠንቀቂያ እንርሳ። ልባችንን፥ ለምን እንደምናገለግለው፥ የምናደርገውን እንቅስቃሴ ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን መረዳት ደስ ያሰኛል። ጌታን ስናገለግል፥ በአዕምሯችን በፍርድ ወንበር የተቀመጠው ክርስቶስ መሆኑን ስናስብ፥ በሌላው ላይ ከመፍረድ ይጠብቀናል። *"ታዲያ አንተ በወንድምህ ላይ ለምን ትፈርዳለህ? ለምንስ ወንድምህን ትንቃለህ? ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና..."* (ሮሜ 14፥10)።

"በወንድሞቻችን ላይ መፍረድ የለብንም" ስንል ከወንድሞቻችን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አይኖረንም ማለት አይደለም። እርዳታችን ቢያስፈልጋቸው እንረዳቸዋለን። አደጋ ላይ መሆናቸውን ስናይ፥ እንዲሸሹ ማስጠንቀቂያ እንሰጣቸዋለን። ቢበድሉን፥ "በደላችሁን" ብለን እውነቱን እንነግራቸዋልን። ንስሀ ገብተው ይቅርታ ከጠየቁን፥ ይቅርታ እንሰጣቸዋለን። በጠቅላላው ሊረዳቸው ወይም ሊጠቅማቸው የሚችለውን በጎ የሆነውን ነገር ለእነርሱ ከማድረግ ወደ ኋላ አንልም። ውስጣዊ ሕይወታቸውን የማየት ችሎታና አቅም ያለን ይመስል፥ "ይህን ያደረጉት፥ ይህን አስበው ነው" በማለት ልንፈርድባቸው አይገባንም።

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ብንመረምር፥ መጥተው ካለፉት፥ እሁንም ካሉት ታላላቅ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መካከል ሳይነቀፍ፥ በሀሰት ሳይከሰስ ያለፈ አንድም የለም። የታወቀው እንግሊዛዊው ሰባኪ፥ ስፐርጀን (Spurgeon) እርሱን በመቃወምና በመተቸት የተጻፉትን መጽሔቶችን ሁሉ ሰብስቦ አንድ ላይ በማስጠረዝ የግል ቤተ መጽሐፍቱ ውስጥ እንዲቀመጥ ማድረጉ ይታወቃል። እነዚያ እርሱን እየነቀፉ የጻፉት ሰዎች ተረስተዋል። የስፐርጀን ጽሁፎችና ትምህርቶች ግን እስከ ዛሬ ዓለምን ሞልተውታል። እንዲሁም ዶክተር ካምፔል ሞርጋን (Dr. Campbell Morgan) የተባሉት ታላቅ ሰባኪ፥ ተቺዎች ላቀረቡባቸው ትችት መልስ ለመስጠት ሲሞክሩ፥ ጤናቸው በወቅቱ ጥሩ ስላልነበረ፥ መድረኩ ላይ ተዝለፍልፈው እንደ ወደቁ ታሪክ ይናገራል። እኚህ ሰው ተቺዎቻቸውን የሚያስተናግዱት ሁልጊዜ በዚህ ዓይነት ሳይሆን፥ "በና ይጠሩል... እስከዚያው

ድረስ ረጋ ብዬ አገልግሎቴን እቀጥላለሁ" በማለት ነበር። መንፈሳዊ መሪዎች በነቃፊዎቻቸው ምክንያት ከመደናገጥ፣የያዙትን ጥሎ ሸሽቶ ከአገልግሎት ከመውጣት ይልቅ የዶክተር ካምፔልን ምሳሌነት ተከትለው ረጋ ብለው አገልግሎታቸውን መቀጠል ይገባቸዋል።

## 5. የተነቀፍንበት ነቀፋ እውነት ከሆነ

ዓይነቱና መጠኑ የተለያየ ይሁን እንጂ ወደድንም ጠላንም ሁላችንም ነቀፋ ሊደርስብን እንደሚችል ተረድተናል። ነቀፋው ወደ ጆሯችን ሲደርስ፣ "ይሄ ነቀፋ እውነትነት አለው? ነቀፋው ይህን ያህል ክብደት ያለው ነገር ነው? መስጠት ያለብኝ መልስ ምን ዓይነት ነው?" ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። ነቀፋው ጥሩ አመለካከት ካለው እውነተኛ ሰው ከሆነ፣ የተነቀፍንበት ነቀፋ እውነትነት ያለው ከሆነ፣ ነቀፋውን ችላ ብሎ ከማለፍ፣ ወይም የነቀፈንን መልሰን ከመንቀፍ፣ በነቀፌታው ለመጠቀም ልናደርጋቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ።

### 5.1. የነቀፈንን ሰው ምስጋናችንን እንግለጽለት

ሲነቀፍ መስማት ደስ የሚለው ሥጋ የለበሰ ሰው ይኖራል ብለን አናምንም። ሁላችንም ስንመሰገን እንጂ፣ ስንነቀፍ ለመስማት ጆሯችንን ከፍተን አንሰጥም። ይሁን እንጂ፣ ምንም ያህል ከባድ ይሁን እንጂ፣ የሚነገረንን ነቀፋ መስማት አለብን። ነቀፋን በብዙ አቅጣጫ ለጥቅማችን ልናውለው እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ ራሳችንን ድካም የሌለብን ፍጹሞች የሆንን አድርገን የምናስብበት ጊዜ አለ። በዚህ ወቅት ነቀፋ ሚዛናችንን እንድንጠብቅ ይረዳናል። በአገልግሎታችን የበለጠ ፍሬያማ መሆን እንድንችል ስለ እኛ የሚነገረውን፣ እውነት የሆነውን ለመስማት ፈቃደኞች መሆን አለብን። የሰማነው ነቀፋ ቢቆረቁረንና ቢመረንም፣ ነቀፋውን ያሰማንን ሰው በማመስገን እናስደንቀው። ይህንን በማድረጋችን እውነቱን ለመቀበል ልባችን የተዘጋጀ እንዲሆን እናደርገዋለን። ሁለተኛ፣ የተወረወረብንን ነቀፋ እናለሰልሰዋለን። መንቀፍ ደስ የሚላቸው እንዲያውም ልማድ የሆነባቸው ሰዎች አሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹን መያዝ ያለብን በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? ይውጣላቸው ብለን፣ በማሻሻል ወይም መንገዳችንን በመለወጥ ፈንታ በንዴት ተሞልተን በተቃራኒ መንገድ እንሄድ ይሆን? ይህን በማድረግ ፈንታ፣ "ስለ ነገርከኝ በጣም አመሰግንሃለሁ፤ የነገርከኝ ነገር ራሴን እንዳይ ስላደረገኝ በጣም ጠቅሞኛል" እንበላቸው። ዕድገታች ንን የማይፈልጉ ከሆነ፣ የሚጠቅመን ከመሰላቸው ሁለተኛ ነቀፋቸውን አያበሙንም። የምንበሳጭ ከሆነ፣ ነቀፋቸው የጎዳን ስለሚመስላቸው፣ ደጋግመው ሊጠቀሙበት ይችሉ ላሉ። የእኛን ዕድገት ፈልገው የምንነቀፍበትን ነገር የሚነግሩን ከሆነ፣ ያ የነገሩን ነገር እውነት ከሆነ በምስጋና እንቀበላቸው። በመቆጣትና ራሳችንን



በመከላከል ፋንታ፣ "ስለ ሰጠኸኝ አስተያየት አመሰግንሃለሁ። በጣም አስብበታለሁ፤ ለመለወጥ እሞክራለሁ"በማለት እናመስግናቸው።

### 5.2. የተነቀፍንበት ነቀፋ እውነት ከሆነ "አሜን" ብለን እንቀበለው

በአሁኑ ጊዜ የድብብቆሽ ሕይወት የሚኖሩ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ዘንድ ትክክል ያልሆነ የሕይወት አቋም ይዘው የሚኖሩት፣ ኃጢአታቸው በሰው ዘንድ የታወቀ መስሎ ስለማይታያቸው ብቻ ነው። የሚፈሩት እግዚአብሔር ኃጢአቴን ያወቀ እንደሆነ ብለው ባይሆን፣ ሰዎች ያወቁ እንደ ሆነ ብለው ነው። እግዚአብሔር ማወቁ የሚያስጨንቃቸው ቢሆን ኖሮ፣ ከኃጢአታቸው አንድ ቀን እንኳን አያድሩም ነበር። ዳዊት የሰው ሚስት ነጥቆ፣ ባሏን አስገድሎ ኃጢአቱን ደብቆ ለመኖር ለተወሰነ ጊዜ ሞክሯል። በዚህ ጊዜ ውስጥ በአዕምሮ ጭንቀት እየተሰቃየ እንጂ ደስ ብሎት እንዳልኖረ በጻፋቸው መዝሙሮች ላይ ጠቅሷቸዋል። እንደ ዳዊት የበው ባል እያስገደሉ እንጂ፣ ትዳር ኖሯቸው ከሌላው ሰው ሚስት ጋር እያመነዘሩ የሚኖሩ ይኖራሉ። በዚህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ እየኖሩ፣ እውነቱን የሚያውቅ፣ "እያየሁና እየሰማሁ ዝም አልልም" የሚል ድፍረት ያለው ሰው፣ "የምትኖርበት ኑሮ ልክ አይደለም። ንስሀ ገብተህ ተመለስ" ቢለው፣ የተናገረው ነገር እውነት ቢሆንም፣ እውነቱን ከነገረው ሰው ጋር መጋጨቱ እንደማይቀር እርግጠኞች ነን። "ብዙዎቹ በኃጢአት መኖሬን ቢያውቁም፣ እስካሁን ፊት ለፊት መጥቶ ያለሁበትን ሁኔታ እንደ አገተ የነገረኝ ማንም የለም። በጣም አመሰግንሃለሁ" በማለት ፋንታ ያንን ሰው እንደ ጠላት ያየዋል። ነብዩ ናታን ዳዊትን "ያ ሰው አንተ ነህ" ብሎ በደሉን ፊት ለፊት በግልጽ ሲነግረው፣ ናታንን "መአት አውሪ" ብሎ ከአጠገቡ በማባረር ወይም በማስገደል ፈንታ ዳዊት ለናታን "እግዚአብሔርን በጣም በድያለሁ" አለው (2 ሳሙ. 12፥13)።

ዳዊት ነብዩ ናታን የነገረው ነገር እውነት እንደሆነ ስላመነ፣ ራሱን ለመከላከል፣ ከናታን ጋር መጣላትና መጨቃጨቅ አላስፈለገውም። "እውነት ነው እግዚአብሔርን በድያለሁ" አለ። ፕሬዚደንት ክሊንተን ኃጢአቱ ለመላው የአሜሪካ ሕዝብ ሲገለጽ፣ "ከዚህች ሴት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት አልፈጸምኩም..." አለ። በቅርቡ የብዙ ሕዝብ መንፈሳዊ መሪ የነበሩት ቴድ ሃገርድ የግብረ ሰዶማዊ ተግባር ለብዙ ጊዜ ሲፈጽሙ ኖረው፣ ኃጢአታቸው ሲገለጥ፣ እንደ ዳዊት "እግዚአብሔርን በድያለሁ" በማለት ፈንታ ራሳቸውን ለመከላከል ሞክረው ነበር። የቀረበባቸው ክስ የማያጠራጥር መረጃ የነበረው በመሆኑ፣ ማበወር እንደማይችሉ ሲያውቁት፣ "እግዚአብሔርን...ቤተ ክርስቲያኔን... ቤተሰቤን በድያለሁ" አሉ። የቀረበብን ነቀፋ እውነት መሆኑን እያወቅን ራሳችንን ለመከላከል ብንሞክር፣ እግዚአብሔር ሊያስተላልፍልን የሚፈልገውን እውነተኛ መልዕክት "አልቀበልም" ማለታችን እንደሆነ እንወቅ። ነቀፋው ከየትም አቅጣጫ ይምጣ፣ ሌላው ቀርቶ ከሚጠሉን ሰዎች እንኳን ቢመጣ፣ የተነገረብን ነቀፋ ልባችንን መርምረን እውነት መሆኑን ካወቅን፣ የሚቆረቁረን እንኳን ቢሆን እንቀበለው። ድካማችን (ኃጢአታችን)

ከላይ የገለጽነውን ዓይነት እንኳን ባይሆንም፥ እውነትነት ያለው ነቀፋ ከሆነ፣ ነቀፋውን መቀበል ብቻ ሳይሆን፣ የነገረንንም ሰው ከልባችን ልናመሰግነው ይገባል።

## 5.3. መለወጥ የምንችለው ነገር ከሆነ እንለውጠው

ስብከታችንን ከሚያዳምጡ ሰዎች መካከል አንዱ ደፍሮ "ስትሰብክ ያለቦታው ከመጠን በላይ ትጮኸለህ፤ ብዙ ትወራጫለህ... አንዳንድ ጊዜ በጣም ስትጮኽ፣ ስርህ ሲግተረተር ሳይ፣ የሚበጠስ እየመሰለኝ እጨነቃለሁ...እፈራለሁ" የሚል አስተያየት ብንሰማ፣ ይህን ዓይነቱን አስተያየት የምናስተናግደው እንዴት ይሆን? "ስሰብክ የምጮኸው መንፈስ ቅዱስ ሲነካኝ ነው... ጌታን በነጻነት ባመሰግነውና ባከብረው እንጂ እንድታሠር አልፈልግም..." በማለት አስተያየቱን ያሰማንን ሰው አመናጭቀን ችላ ብለነው እናልፋለን? ሰውዋ የማንፈራ፣ ለምን ተነካሁ ብለን በቀላሉ ቅር የማንሰኝ ከሆንን፣ ለጥቅማችን እንዲውል የተነገረን መሆኑን አምነን የበለጠ እንድናስብበት እንሆናለን። አስተያየቱን ያሰማንን ሰው፣ ሊጎዳን ሳይሆን ሊጠቅመን እንደሆነ በማመን "አመሰግንሃለሁ... እስከ ዛሬ ፊት ለፊት እንዳንተ መጥቶ የነገረኝ ሰው የለም... እስቲ አስብበታለሁ..." በማለት መልስ እንሰጣለን። ልንከደው የማንችለው እውነት ከሆነ፣ መለወጥ የምንችልበትን መንገድ እንፈልጋለን። ያን አስተያየቱን ለሰጠን ሰው ራሳችንን የበለጠ ተጠያቂዎች በማድረግ፣ "...በዚህና በዚህ ቀን እሰብካለሁና እስቲ በማኝና እንደ ቀድሞ በጣም እጮኽ እንደሆነና ሌላም መሻሻል አለበት የምትለውን ጠቁመኝ" ብንለው የበለጠ እንጠቀማለን እንጂ አንጎዳም። ስንሰብክ ከመጠን በላይ በኃይል መጮኽ ከፋቱ ሳይታየን ይችላል። ለሚበሙን ሰዎች ግን ላያስደስት ይችላልና ያንን ማስተካከል ይህን ያህል ከባድ አይሆንም።

አንዳንድ ጊዜ ሌላው በው ሊለውጠው የማይችለውን ነቀፌታ የሚያቀርቡበት ጊዜ አለ። አንዳንድ ሰው ሲያኝክ አፉን ከፍቶ ያኝካል። አንደ እኔ ዓይነቱ ደግሞ ሲያኝክ "ጯ! ጯ!" እያደረገ ያስጮኻል። በዚህ ሁኔታ ላይ አስተያየት ሰጪዎች ያሉት እውነት ከሆነ፣ አስተያየታቸውን በበጡት ሰዎች ላይ ከመቆጣት ይልቅ "አመሰግናለሁ ስለ ሰጠኸኝ አስተያየት። ይሁን እንጂ፣ ይህን ዓይነቱን ነገር ለረጅም ጊዜ ስለማመድ የቆየሁ በመሆኔ በቀላሉ ልለውጠ የምችለው ነገር አይደለም። መሞከሬ ግን አይቀርም" በማለት መልካም መልስ ብንሰጥ፣ አስተያየቱን በሚሰጠን ሰው ላይ ቅሬታና መራራነት እንዳይኖረን ራሳችንን እንድንጠብቅ ያደርገናል። በሕይወታቸው ብዙ መነቀፍ ከደረሰባቸው ታላላቅ ሰዎች መካከ የአብርሃም ሊንከንን ያህል ነቀፋ የደረሰበት ሰው የለም። ለሚነቅፏቸው ሰዎች የሚሰጡት መልስ፣ "የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ" የሚል ነው። በተራቸው ሌላውን የመንቀፍ ምክንያት ሲኖራቸው፣ ምንም ዓይነት ቅሬታና መራራነት በልባቸው እንዲኖር ስለማይፈልጉ፣ ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጋሉ።



ሰው ሁሉ በተፈጥሮ የተለያየ ነው። አንዳንዱ በሕይወቱ የደረሰበትን፣ የሆነለትን በጎ ነገር አይረሳም። የደረሰበትን መልካም ያልሆነ ነገር ግን አያስታውስም። ሌላው ደግሞ የሆነለትን በጎ ነገር ከማስታወስ ይልቅ፣ ያልሆነለትን ነገር ማስታወስ ይቀለዋል። የመድረክ ሰው ከሆኑት ሰዎች መካከል ከአንድ ሺ አድማጮች መካከል ሁሉም በአሰባሰባቸው ተደስቶ አንድ ሰው ቅሬታውን ቢያሰማቸው ዓለም በላያቸው ላይ የተደባቸው መስሎ የሚበግቸው ሰዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። "በጣም ጥሩ መልዕክት ነው" በማለት ያመሰገኗቸውን ብዙ ሰዎች በማበብ ፈንታ፣ "በስብከትህ ላይ የአንድ የእንግሊዝኛ ቃል ተጠቀምክ" በማለት አስተያየት ስለሰጣቸው ሰው በማሰብ፣ ቀኑን ሙሉ ጨፍግገቸው የሚውሉ፣ "ሁለተኛ አልሰብክም... መስበክ ስጦታ ያለኝ አይመስለኝም...." በማለት የሚደመድሙ አሉ። መንፈሳዊ መሪዎች ምን ጊዜም ቢሆን ከነቀፋ ነጻ መሆን አይችሉም። የሚደርስባቸው ነቀፋ ሁሉም ከመስመር የወጣ አይደለም። አንዳንዶቹ እውነትነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ታዲያ ነቀፋውን የሚያስተናግዱት በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? ነቀፋ ሲወረወርባቸው፣ የሰሙት ነቀፋ እውነትነት እንዳለው ውስጣቸውን ይመርምሩ። እውነት ከሆነ ራሳቸውን፣ አመራራቸውን ለማስተካከልና ለመለወጥ ይሞክሩ። እውነትነት የሌለው ከሆነ፣ ልባቸውን ከመራራነት ይጠብቁ። ፍጹም እንዳልሆኑ፣ በዕድሳት ላይ እንዳሉ፣ እግዚአብሔር በእነርሱ ሕይወት የሚሠራውን ሥራ እንዳልጨረሰ፣ ገና ብዙ እንደሚቀራቸው አምነው ይጠብቁ።

## 6. ነቀፋን በአግባቡ መያዝ የማይችሉ የመሪነትን ሥፍራ አይመኙ

ነቀፋ የማንንም ሰው ስሜት የመጉዳት ኃይል አለው። ይሁን እንጂ፣ በመሪነት ወንበር ላይ የተቀመጠ ማንኛውም ሰው የሚቀምሰው መራራ ጽዋ ነው። በዓለም ውስጥ መጥተው ያለፉ ታላላቅ መሪዎች ሁሉ ከነቀፋ ነጻ አልነበሩም። ሌላው ቀርቶ ፍጹም አምላክ፣ ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ከነቀፋ ነጻ አልነበረም። አንዳንዶቹ የቀመሱት ነቀፋ መርዛምነት ያለው ነው። "ነቀፋ እንዳይደርስብኝ" ብሎ ምንም ዓይነት ጥረት ቢያደርግ፣ ራሱን ከነቃፊዎች ነጻ ማድረግ የሚችል በው የለም። መሪዎች በውሳኔ አሰጣጣቸው ፈጣን ቢሆኑ፣ "ችኩሎች"፣ ውሳኔ ለመወሰን የማይፈጥኑ ከሆነ ደግሞ "ወላዋዮች...ለመንቺዎች" በመባል ይነቀፋሉ። መንፈሳዊ መሪዎች የትኛውንም ዓይነት እርምጃ ወይም ውሳኔ ቢያደርጉ መነቀፍ የማይቀርላቸው ስለሆነ፣ ሁለት ዓይነት ምርጫ አላቸው። አንደኛው፣ "ከበደኝ! አልቻልኩም" ብለው የመሪነት ሥፍራቸውን መልቀቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው እግዚአብሔር የሰጣቸውን አገልግሎት በእርሱ ሙሉ በሙሉ ታምነው በቆራጥነት ወደ ፊት መግፋት ነው። በነቀፋ መርዝ ከተጎዱት ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች መካከል እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱት በ18ኛው ክፍለ ዘመን በአገልግሎታቸውና ረቂቅ በሆነው የሥነ መለኮት ጽሁፋቸው ታዋቂና ተደናቂ የነበሩት ጆናታን ኤድዋርድን ናቸው። ጆናታን ኤድዋርድ፣ "ኖርዝአምተን" ውስጥ

በዘመኑ በጣም ታዋቂ በነበረው ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመጋቢነት ያገለግሉ የነበሩ ሰው ናቸው። *"በመጀመሪያው ታላቁ መንፈሳዊ ንቅናቄ" (First Great* ***Awakening)*** ዘመን በመሪነታቸው በጣም ጎልተው ከሚታዩት ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች መካከል ጆናተን ኤድዋርድ አንደኛው ነበሩ። እያዘጋጁ ያወጧቸው የነበሩት መንፈሳዊ ጽሁፎቻቸው በምዕራቡ ዓለም በጣም ተደናቂነት የነበራቸው ነበሩ። በዘመኑ በስብከታቸው በጣም ተደናቂ የነበሩት፣ *ጆርጅ ኋይትፊልድን* የመሳሰሉ ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች መንፈሳዊ ምክር ሲፈልጉ፣ መፍታት ያቃታቸው የሥነ መለኮት ጥያቄ ሲኖራቸው መልስ ፍለጋ ረጅም ጉዞ ተጉዘው ወደ እርሳቸው ዘንድ ይሄዱ ነበር። በዚህ ዓይነት ተደናቂ የነበሩት ጆናታን ኤድዋርድ እንኳን ኃይለኛ የሆኑ ነቃፊዎች እንደነበሩባቸው ታሪካቸው ይመሰክራል። በአንድ ወቅት የቤተ ክርስቲያናቸው አባል የነበሩ፣ በሚሰጡት አገልግሎት ቅሬታ የነበራቸው ጥቂት ሰዎች፣ ውስጥ ውስጡን ተንኮል የሞላበት የስም ማጥፋት ዘመቻ አካሂደውባቸው፣ ከአገልግሎታቸው እንዲባረሩ አደረጉ። በሁኔታው አዝነውና ተስፋ ቆርጠው ከአገልግሎት በመውጣት ፈንታ፣ ከዚያ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ወጥተው፣ *ስቶክብሪጅ* በምትባል ከተማ ውስጥ፣ የአንዲት ትንሽ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆነው አገልግሎታቸውን ቀጠሉ። ዛሬ የጆናታን ኤድዋርድ ከሳሾች በምና ማንነት አይታወቅም፤ እርሳቸው አዘጋጅተው ያወጧቸው ጽሁፉቻቸው ግን፣ በዘመናት በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ሰዎች እያስተማረና እየባረከ ሲሆን፣ ስማቸውና ዝናቸውም በዓለም ዙሪያ የታወቀ ነው። እንግዲህ በአሜሪካ ውስጥ አሉ ከሚባሉት የሥነ መለኮት ምሁር፣ ጆናታን ኤድዋርድ እንኳን ከነቃፊዎች ነጻ ካልሆኑ፣ እኛ ነቁጥ የምናክለውማ እንዴት ከነቀፋ ነጻ መሆን እንችላለን?

ነቀፋን በአግባቡ ማስተናገድ የማንችል ከሆንን፣ ከመቶ ሰዎች ምስጋና ተቀብለን በዚያ መካከል አንድ ሰው ብቻ ነቀፋውን ቢያሰማን በብርብራችን ይወጣል። ቤተ ክርበቲያን ውስጥ ከብዙ አመስጋኞች ድምጽ ይልቅ፣ የጥቂት ነቃፊዎች ድምጽ የበለጠ ጎልቶ እንደሚሰማ የታወቀ ነው። እንዲሁም ብዙ ጊዜ ከምስጋና ይልቅ "ነቀፋ" የበለጠ ክብደት ይሰጠዋል። በአመራራቸው ብዙ አድናቂ ያላቸው ታላላቅ መሪዎች፣ ጥቂት የሆኑ ነቃፊዎቻቸውን ማስተናገድ እያቃታቸው፣ የሚወዱትን አገልግሎታቸውን ትተው የሚወጡ ብዙዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። በዙሪያቸው ብዙ ደጋፊዎች አብረዋቸው የቆሙ መሆናቸው በደንብ እንዳይታያቸው፣ የጥቂት ነቃፊዎች ጥላ ሲጋርድባቸው ማየት ለአንዳንዶቻችን ይህን ያህል አዲስ አይደለም። ገንቢ ነቀፋ ጠቃሚነት ስላለው መሪዎች ሊፈሩት አይገባም። እንዲያውም በግልጽ መጠየቅም የሚያስፈልጋቸው ጊዜ አለ። ሀሜትና አሉባልታ "ብርቱ ናቸው" የሚባሉትን መሪዎች መንፈስ እንኳን የመግደል ኃይል አለው። እርግጥ ነው ብዙ መሪዎች በሚመሯቸው ሰዎች መደነቅና መመስገንን ይፈልጋሉ። ለአገልግሎት የተነሱበትን እውነተኛ ምክንያታቸውን በመጠራጠር የሚጠይቅ አንዳንድ ሰው በመንገዳቸው ላይ ሲገጥማቸው፣ የአገልግሎት ደስታን



ማጣታቸው ብቻ ሳይሆን፣ "ለምን ይህን ያህል ዋጋ እከፍላለሁ?" በማለት ከአገልግሎት ለመውጣት ይፈተናሉ።

መንፈሳዊ መሪዎች ነቃፊዎች በሚወረውሩባቸው ነቀፋ እንዳይጎዱ ራሳቸውን የሚጠብቁበት ብልሃት ይኖር ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ብዙ ጊዜ ነቀፋ ስንሰማ፣ የሰማነው ነቀፋ ወደ ውስጣችን እንዳይገባና ስሜታችንን እንዳያደፈርስብን ቶሎ ከአዕምሯችን ለማስወጣት እንሞክራለን። በዚህ ዓይነት እርግጥ ነው ራሳችንን ከመንፈስ ጉዳት እንጠብቃለን። ይሁን እንጂ፣ ለትምህርታችን እንዲሆን የመጣልንን ነቀፌታ፣ ከአዕምሯችን በማስወጣት ሳንጠቀምበት እንቀራለን። ይህ እንዳይሆን መጀመሪያ ነቀፋውን ስንሰማ፣ ይሄ የሰማሁት ነቀፋ ምን ያህል እውነትነት አለው? በማለት በታማኝነት ራሳችንን መመርመር ወይም መጠየቅ አለብን። ስለደረሰብን ነቀፋ ማሰብ እርግጥ ነው ስሜታችንን ይጎዳዋል። ይሁን እንጂ፣ አስተዋይ መሪዎች ሌላው ቀርቶ ሊጎዳቸው ከመጣው ነቀፋ እንኳን ትልቅ ትምህርት ይማራሉ። በእግዚአብሔር ፊት በታማኝነትና በቅንነት ከተራመዱ፣ ራሳቸውን ከነቃፊዎች ለመከላከል፣ ወይም የተወራውን ወሬ ለማስተባበል ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ማባከን የለባቸውም። እግዚአብሔር *"በአንቺ ላይ እንዲደገን የተበጀ መሣሪያ ይከሽፋል፤ የሚከስሽንም አንደበት ሁሉ ትረቺያለሽ"* (ኢ.ባ. 54፥17) በማለት የሰጣቸውን ተስፋ ይዘው ሳይደናገጡ ጸንተው መቆም አለባቸው። የማንኛውም ሰው እውነተኛነት ወደ ፊት ስለሚታወቅ፣ በእግዚአብሔር ተማምኖ በሰላም አገልግሎትን መቀጠል ያስፈልጋል። ጆናተን ኤድዋርድ በነቃፊዎቻቸው ፊት እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አደረጋቸው። የነቀፏቸውና ከቤተ ክርስቲያናቸው አገልግሎት እንዲባረሩ ያደረጉ ጠላቶቻቸው፣ የእግዚአብሔርን እውነተኛ አገልጋይ በመቃወማቸው በእግዚአብሔር ፊት ከፍተኛ ኃጢአት (በደል) የሠሩ መሆናቸውን በአደባባይ ንስሀ እንደ ገቡ ታሪካቸው ይመሰክራል። በመጨረሻ ጆናታን ኤድዋርድ አሜሪካን አገር በጣም የታወቀው የፕሪንስተን ዩኒቨርስቲ ፕሬዚደንት ሆነው ተመረጡ። ዛሬ ታሪክ ጆናተን ኤድዋርድን የሚያነሳቸው፣ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ተደናቂ ከሚባሉት ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች መካከል ፊት ቀደም አድርጎ ነው። "ኦስዋልድ ሳንደርስ" የተባሉ ጸሐፊ፤

> *"ብዙ ጊዜ ሰዎች በአጠገባቸው ሆኖ የሚመራቸውን መሪ በምድር ያለውን ዘመኑ ጨርሶ በሞት እስኪለያቸው ድረስ በትክክል ሊያውቁትም። ከሞተ በኋላ ግን ወርውረው በመቃብት ድንጋይ ሐውልት ይሠሩለታል"*
> አሉ።[28]

[28] Oswald Sanders. Spiritual Leadership, Moody Press, Chicago IL 1967.

አውነተኛ መሪዎች ትክክል የሆነውን ሥራ መሥራታቸውን እንጂ፣ ዝናንና መታወቅን የሚያገኙበትን መንገድ የሚፈልጉ አይደሉም። ብዙ ጊዜ ትክክል የሆነውን ሥራ ሐቀኛ አቋም ይዞ መሥራት፣ ዝነኛ የማያደርግበት ጊዜ አለ። በአገልግሎታቸው እርግጠኞች ባልሆኑና ባልበሰሉ መንፈሳዊ መሪዎች (አገልጋዮች) ሕይወት ላይ፣ ነቀፋ ብዙ ጉዳትን ሊያመጣ ይችላል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በግልጽ የሚያውቁ መሪዎች ጠላቶቻቸው በተለያየ መንገድ ተበሩ ሊያስቀርቧቸው ሲሞክሩ፣ ከዓላማቸው ትንሽም ነቅነቅ አይሉም። የፖለቲካ መሪዎች ብዙሐኑ የሚደግፈውን ነገር እነርሱ ራሳቸው የማያምኑበት እንኳን ቢሆን ተቀብለው በተግባር ላይ ያውላሉ። እውነተኛ መሪዎች የሚወስኑት ውሳኔ ደጋፊ፣ ወዳጅ፣ የከፋ እንደሆነ ሥራቸውንም የሚያሳጣቸው ቢሆንም፣ በአመኑበት ጸንተው ይቆማሉ። አንዳንድ ጊዜ መሪዎች በተከታዮቻቸው መካከል በአንድ ዓይነት አሳብ ላይ ወደ መስማማት ለማምጣት ይሞክራሉ። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች ግን ሁሉም በሚስማማበት ነገር ላይ ትኩረት አይሰጡም። መንፈሳዊ መሪዎች አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙት "ሰዎች ምን ይላሉ?" በሚለው አሳብ ሳይሆን፣ "እግዚአብሔር ምን ይላል?" በሚለው ላይ ነው። ትልቁ ጥረታቸው ምንም ዓይነት ነቀፋ እንዳይደርስባቸው ለማድረግ ከሆነ፣ ለመሪነት ብቃት ያላቸው አይደሉም። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለው ባመኑበት ነገር ላይ የማንንም ነቀፋ ሳይፈሩና ሳያወላውሉ በአገልግሎታቸው ወደ ፊት ይቀጥላሉ።

መንፈሳዊ መሪዎች ነቀፌታን በትክክለኛው ገጽታ ማየት ይገባቸዋል። ነቀፋ የማይቀር መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በጣምም ይጎዳል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ጥሪ እንዲያስወጣቸው መፍቀድ የለባቸውም። ግፊት በዝቶባቸው "አሁንብ በቃኝ!" ብለው የመጨረሻ ውሳኔ አድርገው ከማቆማቸው በፊት እግዚአብሔር ለምን እንደጠራቸው ቆም ብለው ማሰብ አለባቸው። ምንም ዓይነት ተቃውሞ፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ወይም መስዋዕት የእግዚአብሔርን ጥሪ ከሕይወታችን የመሰረዝ (የማጥፋት) ኃይል የለውም። በነቀፋ ውስጥ ስናልፍ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ሆነናል ማለት እንዳልሆነ ማወቅ ይገባናል። ነቀፋ ሲደርስባቸው ራሳቸውን ከአገልግሎት ውጪ የሚያደርጉ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ለሕይወታቸው እግዚአብሔር ፈቃዱ ምን እንደሆነ ያልተረዱ ናቸው። እግዚአብሔር እንዲሠሩ የጠራቸው ለምን እንደሆነ በደንብ የሚያውቁ መንፈሳዊ መሪዎች ምንም ዓይነት ነቀፋና ተቃውሞ ቢደርስባቸው ትንሽም ከዓላማቸው ነቅነቅ አይሉም።

## ምዕራፍ ፱


# አገልግሎት አሳታፊነትና አነሳሽነት

"አንዳንዶች ሐዋርያት፣ አንዳንዶች ነቢያት፣ አንዳንዶችም ወንጌል ሰባኪዎች ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፤ ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ሲሆን፣ ይህም የሚሆነው፣ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስክንደርስ ነው" (ኤፌ. 4፥11-13)።

በዓለም የአመራር ሥርዓት ውስጥ በመሪነት ደረጃ ላይ የተቀመጠ ማንኛውም መሪ በአመራሩ ፍሬያማ (ስኬታማ) ሊያደርጉት ከሚችሉት ነገሮች መካከል አንደኛው፥ አብረውት የሚሠሩትን ሰዎች ችሎታና አቅም እየመዘነ ሥራን የማከፋፈል፣ ኃላፊነትን የመስጠት ችሎታና ፈቃድ ሲኖረው ነው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም፣ በአመራራቸው ፍሬያማ መሆን የሚችሉት፣ አንድ ወይም የተወሰኑ ጥቂት ሰዎች ብቻ እንዲያገለግሉ ሳይሆን፣ ምዕመናንን ሁሉ አስፈላጊው ስልጠና ተሰጥቷቸው በቤተ ክርስቲያን

ውስጥ በአገልግሎት እንዲሳተፉ ዕድል መስጠት ሲችሉ ነው። ይሄም ለምዕመናን መንፈሳዊ ዕድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ሥራ ሁሉ አንድ ሰው ወይም ጥቂት ሰዎች ብቻቸውን ሠርተው ሊጨርሱት የማይችሉት መሆኑን እያወቁ፣ አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ምዕመናኑን ከማሳተፍ ይልቅ፣ ሥራውን ሁሉ እነርሱ ብቻ መሥራት የሚፈልጉበት ምክንያት ምን ይሆን? በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ያለውን ሥራ ሁሉ እነርሱ ካልሠሩት ልክ የሚመጣ ስለማይመስላቸው ይሆን? የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን እንድትፈጽም ከእግዚአብሔር አደራ የተሰጣት ቢሆንም፣ ሥራውን ሁሉ መሪዎች ብቻ መሥራት ያለባቸው ይመስላቸው ይሆን? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለእነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክረናል። ሥራንና ኃላፊነትን ለሌሎች በማከፋፈል ፈንታ ሥራውን ሁሉ ብቻቸውን መሥራት ያለባቸው መስሎ ከሚሰማቸው መሪዎች መካከል ጥሩ ምሳሌ የሚሆንን ሙሴ ነው።

## 1. በአንድ ሰው ብቻ የሚመራ የአስተዳደር መዋቅር



ወደ ተስፋይቱ ምድር፣ ወደ ከንአን ለመግባት ጉዞ ላይ የነበሩትን አንድ ሚሊዮን ተኩል እስራኤላውያንን፣ ሙሴ ብቻውን ለማስተዳደርና ለመዳኘት የሞከረ ሰው ነው። *"...ሙሴ ሕዝቡን ለመዳኘት ተቀመጠ፤ እነርሱም በዙሪያው ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ ቆሙ"* ይላል (ዘጸ. 18፥13)። ሙሴ የመረጠው የአመራር ሥልት እርሱን ብቻ ሳይሆን ሕዝቡንም ጭምር የሚጎዳ ነበር። ችግሩ የሙሴ ብቻ ሳይሆን፣ የሕዝቡም ጭምር ነበር። በወቅቱ ለማንኛውም ነገር ሥልጣንና ጥበብ ያለው፣ ችግራቸውን ሁሉ ሊያቃልል፣ በመካከላቸው ለሚፈጠሩት ግጭቶች ሁሉ መፍትሄ ሊሰጥ የሚችለው "ሙሴ ብቻ ነው" ብለው ያስቡ ስለነበረ፣ ሕዝቡ እርሱን ለማነጋገርና ከእርሱ ፍርድ ለመቀበል ከጠዋት እስከ ማታ በመጠበቅ ከመጠን በላይ ይጉላላ ነበር። ሙሴ ከሕዝቡ የሚሰማቸውን አንዳንድ ቅሬታዎችና ክሶች በሌሎች ሰዎች ሊዳኝ እንደሚችል በወቅቱ እርሱም ሆነ




ሕዝቡ ትክክለኛ የሆነ መረዳት አልነበራቸውም። ሙሴ የነበረበትን ትልቅ ኃላፊነት ሲገልጽ፣ *"ክርክር በኖራቸው ቁጥር ጉዳያቸው ወደ እኔ ይመጣል፤ ለግራና ለቀኙ የሚሆነውን እኔ ወስኜ የእግዚአብሔርን ሥርዓትና ሕጎች እነግራቸዋለሁ"* ይላል (ዘጸ. 16፥16)። ሙሴ ይህን ዓይነቱን የአመራር ሥርዓት የመረጠበት ምክንያት ሥልጣኑ ከእጁ እንዳይወጣበት ፈልጎ ሳይሆን፣ ካለማወቅ የተነሳ ብቻ ነበር። ዛሬም ባለማወቅ የሙሴን ዓይነት የአመራር ሥልት የሚከተሉ መንፈሳዊ መሪዎች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው።

አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች በአገልግሎታቸው ይህን ያህል ደስተኞች አይደሉም። ያለፈቃዳቸው ከሚችሉት በላይ የሆነ ሥራና ኃላፊነት የተጫነባቸው መስሎ ስለሚሰማቸው፣ በየጥቃቅኑ ምክንያት ሲበሳጩ ይታያሉ። ብዙ ስለሚያጉረመርሙና ስለሚማረሩ፣ ከሚያገለግሉት ሕዝብም ሆነ አብረዋቸው ከሚያገለግሉት ሰዎች ጋር ሰላም አይኖራቸውም። በጠባያቸው በጣም አስቸጋሪዎች ይሆናሉ። ለዚህም ጎልቶ የሚታየው አንደኛውና ዋናው ምክንያት፣ ለምዕመናኑ የአገልግሎት ዕድል በመስጠትና ኃላፊነቱን በማከፋፈል ፈንታ፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ሥራ ሁሉ ለብቻቸው ሠርተው መጨረስ ያለባቸው ስለሚመስላቸው ነው። መንፈሳዊ መሪዎች ከእግዚአብሔር በአደራ የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣት የሚችሉት፣ የምዕመናኑ የተፈጥሮ ችሎታንና እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን እያዩ፣ ደስ ብሏቸው ማገልገል በሚችሉት አገልግሎት ውስጥ እየገቡ እንዲያገለግሉ ዕድል በመስጠት ነው። የመሪው ኃላፊነት አገልግሎትን ለምዕመናን ማከፋፈል ብቻ ሳይሆን፣ በአገልግሎታቸው ውስጥ አስፈላጊውን ሥልጣን መስጠትና፣ እንዲሁም ለሚሰጡት አገልግሎት ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ይሁን እንጂ፣ አገልግሎትን ለሌሎች የሚያከፋፍለው መንፈሳዊ መሪ፣ ሥራው ሳይሠራ ቢቀር ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናል ማለት አይደለም። እንዲሁም ምዕመን ሁሉ የአገልግሎት ተሳትፎ ይኑራቸው ማለት፣ መንፈሳዊ መሪው የራሱን ኃላፊነት ለሌሎች ሰጥቶ እርሱ ያለሥራ እጁን አጣምሮ ይቀመጥ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። "ጠንካራ" ስሆን የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሥር መሆን፣ በክርስቶስ ዘመን በአሕዛብ መካከል እንደነበረው "የገዢና የተገዢ" የአመራር ሥልት መከተላቸውን አንዳንድ መሪዎች የተገነዘቡት አይመስሉም። ኢየሱስ አማኞች ይህንን ዓይነቱን የአመራር ሥርዓት እንዲከተሉ የማይፈልግ መሆኑን ሲገልጽ፣ *"የአሕዛብ ነገሥታት ሕዝቦቻቸውን በኃይል ይገዛሉ፤ በእነርሱ ላይ ሥልጣን ያላቸውም በጎ አድራጊዎች ተብለው ይጠራሉ። በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይሁን..."* አለ (የሉቃ. 22፥24)።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ታላቅ መሪ ከሚባሉት ሰዎች መካከል ሙሴ አንደኛው ነው። ይሁን እንጂ፣ ሙሴ የራሱ የሆነ ድካም ነበረበት። ከድካሞቹ ውስጥ አንደኛው፣ ከአንድ ሚሊዮን ተኩል በላይ የሆነውን እጉረምራሚና አስቸጋሪ ሕዝብ ብቻውን ለመምራት

## 1. በአንድ ሰው ብቻ የሚመራ የአስተዳደር መዋቅር



መሞከሩ ነው። የሕዝቡ ቁጥር እያደገና ፍላጎቱም እየጨመረ ሲመጣ፣ የፈለገውን ማግኘት ሲያቅተው፣ ከግብጽ እየመራ ባወጣው በእግዚአብሔርና እንዲሁም በእርሱ ላይ የሚያጉረመርሙ መሆናቸውን የተገነዘበው አይመስልም ነበር። አንድ ቀን የምድያም ካህን የነበረው፣ ዮቶር የተባለው የሙሴ አማት ሙሴንና ሕዝቡን ለመጠየቅ ወደ በረሃ በመጣበት ጊዜ ባየው በሙሴ አመራር ሥልት ደስተኛ አልነበረም። *"...ሙሴ ሕዝቡን ለመዳኘት ተቀመጠ፤ እነርሱም በዙሪያው ከጧት እስከ ማታ ድረስ ቆሙ። አማቱም ሙሴ ለሕዝቡ የሚያደርገውን ሁሉ ባየ ጊዜ ምን ማድረግህ ነው? እነዚህ ሁሉ ሰዎች ከጠዋት እስከ ማታ በዙሪያህ ቆመው ሳለ ብቻህን በፍርድ ወንበር ላይ ለምን ትቀመጣለህ? አለው"* (ዘጸ. 18፥13-14)። ሙሴ የአሠራሩ ሁኔታ ለሕዝቡ ብቻ ሳይሆን፣ ለራሱም አድካሚ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ሌላ አማራጭ መንገድ እንዳለው፣ ይኸውም እርሱ የሚሠራውን ሥራ ሌሎች ሊሠሩት እንደሚችሉ የተረዳ ሰው አልነበረም። ይህንን የተገነዘበው ዮትሮ "ለብቻህ ይህን ሁሉ ሕዝብ ለማስተዳደር እንዴት ትሞክራለህ?" ብሎ ሲጠይቀው፣ ሙሴ፣ *"...ሰዎቹ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈለግ ወደ እኔ ይመጣሉ። ክርክር በኖራቸው ቁጥር ጉዳያቸው ወደ እኔ ይመጣል፤ ለግራና ለቀኙ የሚሆነውን እኔ ወስኜ የእግዚአብሔርን ሥርዐትና ሕጎች እነግራቸዋለሁ"* አለው (ዘጸ. 18፥18)። ሙሴ በበረሃ ውስጥ ሕዝቡን ለመዳኘት የመረጠው መንገድ አድካሚ እንደሆነ ዮትሮ ለመረዳት ይሄን ያህል ጊዜ አልፈጀበትም። *"አንተና ወደ አንተ የሚመጡት እነዚህ ሰዎች የምታደርጉት ነገር ቢኖር ራሳችሁን ማድከም ነው፤ ሥራው ለአንተ ከባድ ሸክም ነው፤ ብቻህን ልትወጣው አትችልም"* አለው (ዘጸ. 18፥18)። የሙሴ ድካም ሥራውን ሌሎች እንዲሠሩት አለማከፋፈሉ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች የሥራ ልምምድ እንዳይኖራቸው ዕድል የነፈጋቸው መሆኑ ነው። መሪው ሥራን ለማከፋፈል፣ ኃላፊነት ለመስጠት ፈልጎ ብቃት ያላቸው ሰዎች ቢያጣ፣ የዚህ ምክንያት ከሠራተኞቹ ድክመት የመጣ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል እንዲለማመዱ ዕድል ያልተሰጣቸው በመሆኑ ብቻ ነው። ዮትሮ የሙሴን አሠራር አይቶ መንቀፍ ብቻ ሳይሆን፣ *"ምክር እሰጥሃለሁና እኔን አድምጠኝ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን"* አለው (ዘጸ. 18፥19)። ሙሴም ትሁት ሰው ስለነበረ፣ "የዚህ ሁሉ ሕዝብ መሪ ሆኜ እንዴት አንተ እኔን ትመክረኛለ?" በማለት ፈንታ ዮትሮ የሰጠው ሀሳብ ትክክል እንደሆነ አምኖ ልክ እንደመከረው አደረገ። ሙሴ *"ከእስራኤል መካከል ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መረጠና የሕዝቡ መሪዎች፣ በሺዎች፣ በመቶዎች፣ በአምሳዎች፣ በዐሥሮች ላይ አለቆች አደረጋቸው"* (ዘጸ. 18፥25)።

ይህን ዓይነቱ ድካም በብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ ሳይሆን በአዲስ ኪዳንም ዘመን የነበረ ነው። በአንደኛው ክፍለ ዘመን በነበረችው በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ተመሳሳይ ችግር ተፈጥሮ ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥራ ሁሉ በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ሐዋርያት እንዲሠሩት ይጠበቅ ስለነበረ፣ ከአቅም ማነስ የተነሳ አንዳንድ



ሊሠሩ የሚገባቸው ሥራዎች ሳይሠሩ በመቅረታቸው፣ በምዕመናኑ መካከል አንዳንድ ቅሬታዎችን ፈጥሮ ነበር። የሙሴ አመራር ሕዝቡን ብዙ ያንገላታው ቢሆንም፣ ለችግራቸው ብልሃት እንዲፈልጉ የሚገፋፏቸው ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር ግን የሙሴን የአመራር ድክመት ለማስተካከል ዮትሮን ላከለት። በዮትሮ ምክር መሠረት ሙሴ ኃላፊነቱን ለብዙዎች እንዳከፋፈለ ተመልክተናል። በመጀመሪያቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን ችግሩ ራሱ የተሻለ ብልሃት እንዲፈልጉ አደረጋቸው። አንዳንድ ሥራዎች መሠራት ሲገባቸው ሳይሠሩ በመቅረታቸው፣ ሐዋርያት የአንዳንዶችን ቅሬታ ሰምተው አንዳንድ እርምጃዎችን ወሰዱ። *"ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሌሎችን ደቀ መዛሙርት በአንድነት ሰብስበው እንዲህ አሉ፤ እኛ የማእዱን አገልግሎት ለማከናወን ስንል የእግዚአብሔርን ቃል አገልግሎት መተው አይገባንም። ስለዚህ ወንድሞች ሆይ! ከእናንተ መካከል በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ለመሆናቸው የተመሰከረላቸውን ሰባት ሰዎች ምረጡ፤ ይህን ኃላፊነት ለእነርሱ እንሰጣለን፤ እኛ ግን በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት እንተጋለን"* አሉ (የሐዋ. 6፥2-4)። በዚህ ዓይነት ሐዋርያት በቅዱሳን ማኅበር ውስጥ ሥራንና ኃላፊነትን አከፋፈሉ።

ሐዋርያት ከላይ እንዳነበብነው ሥራውንና ኃላፊነቱን ለሌሎች ሲያከፋፍሉ፥

- *ሐዋርያት (መሪዎች) ተቀዳሚነት ያለውን አገልግሎት ይኸውም፣ በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት መትጋት ቻሉ፤*
- *የሌሎች ደቀ መዛሙርት ስጦታ ወይም ችሎታ ታወቀ (የሐዋ. 6፥3)*
- *በመካከላቸው የነበረው ግጭትና አለመስማማት ቀርቶ ሰላም ተፈጠረ፤*
- *በሐዋርያት (መሪዎች) ላይ የአገልግሎት ኃላፊነት ተቃለለ።*
- *ሕዝቡን እንደሚገባ ማገልገል ቻሉ፤*

በእኛም ዘመን እንደ ሙሴ ሁሉንም ሥራ እነርሱ ብቻ ለመሥራት የሚሞክሩ አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች አሉ። ሥራውን ሁሉ ለብቻቸው መሥራት ከአቅማቸው በላይ እንደሚሆን፣ ሁሉንም ሥራ ለመሥራት ጊዜያቸውና ጉልበታቸው ውስን መሆኑን ቢያውቁም፣ አብረዋቸው ላሉት አንዳንድ ሰዎች ሥራውንና ኃላፊነቱን ለማከፋፈል ፈቃደኞች አይደሉም። የአንዳንዶቹ ዋና ምክንያት ሥራን ማከፋፈል የሚሰጠውን ጥቅም ካለማወቅ ሳይሆን፣ ሥራውን ሌሎች እንዲሠሩ ቢያደርጉና ኃላፊነቱን ለሌሎች ቢሰጡ፣ ያላቸውን ሥልጣን ወይም ኃይል የሚያጡ ስለሚመስላቸው ነው።

ሥራን ወይም ኃላፊነት ማከፋፈል አስፈላጊ ይሁን እንጂ መንፈሳዊ መሪዎች ሌሎች እንዲሠሩት ማከፋፈል የሌለባቸው ሥራዎች ወይም ኃላፊነቶችን ለይተው ማወቅ አለባቸው። ይኸውም፦

- *መንፈሳዊ መሪው ብቻ የሚሠራቸው ምድብ ሥራዎች አሉ። የራሱን ሥራ ወይም ኃላፊነት ለሌሎች ማስተላለፍ የለበትም። እርሱ ብቻ ለሚሠራቸው ምድብ ሥራዎች ከራሱ በስተቀር ሌላ ሰው ተጠያቂ መሆን አይችልም።*
- *መንፈሳዊ መሪ ብቻ የሚወስናቸው ውሳኔዎች አሉ። እነዚያን ሌሎች ሰዎች እንዲወስኑና የውሳኔው ተጠያቂዎች ማድረግ አይችልም።*
- *ሥራውን እርሱ ብቻ የሚያውቀው ከሆነ፣ ችሎታው የሌለው ሰው እንዲሠራው ማስተላለፍ ትክክል አይደለም። ለምሳሌ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ካለበት ኃላፊነት ውስጥ ትልቁ ማስተማር ከሆነ፣ የማስተማሩን ሥራ ሌሎች እንዲሠሩት ማከፋፈል የለበትም።*
- *መንፈሳዊ መሪው ብቻ የሚፈታው ችግር ከሆነ፣ ለሌላው ሰው ማስተላለፍ አይችልም።*

የጥሩ መንፈሳዊ መሪ ምልክቱ፣ የሌሎችን መንፈሳዊ ስጦታ አውቆ ሁሉንም እንደ ስጦታው ጥሩ ውጤት ሊያመጣ በሚችልበት አገልግሎት ላይ ማሠማራት ሲችል ነው። የታወቁት መንፈሳዊ መሪ ድዋይት ኤል ሙዲ፥

> *“ሺ ሰው የሚሠራውን ሥራ አንድ ሰው እንዲሠራው ከማድረግ ይልቅ፣ አንድ ሺ ሰው ለሥራ ማሠማራት ይመረጣል” አሉ።*

መንፈሳዊ መሪ ሁሉን ሥራ ለብቻው ለመሥራት በመሞከሩ ምክንያት ሊደርስበት ከሚችል ተስፋ መቁረጥ ለመዳን፣ ሌሎችን በአገልግሎት ማሳተፍ አለበት። በሚያደርጉት ነገር ሙሉ ሥልጣን እንዲኖራቸው የሚፈልጉ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ኃላፊነትን ለሌሎች ለማካፈል ወይም ለመስጠት ፈቃደኞች አይደሉም። ሥራን ለሌሎች ማከፋፈል ደስ ቢላቸውም፣ ሥልጣኑ ግን ከእጃቸው እንዲወጣ አይፈልጉም። ይሁን እንጂ፣ ሥራቸው ውጤታማ እንዲሆን ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን፣ ከሥራው ጋር ሥልጣኑንም አብረው ለሌሎች ማከፋፈል መቻል አለባቸው። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች፣ በአካባቢያቸው ከእነርሱ በችሎታው ወይም በዕውቀቱ የተሻለ ሰው ያለ ከመሰላቸው፣ ያንን ሰው ስለሚፈሩት፣ ለዚያ ሰው ምንም ዓይነት የአገልግሎት በር አይከፍቱለትም። በምንም ምክንያት ይሁን፣ ኃላፊነትን ለሌሎች አለማከፋፈል፣ አብረውት የሚያገለግሉትን የሚጎዳ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በድርጅቱ ውስጥ ሊኖር የሚገባው ዕድገት እንዳይኖር ምክንያት ይሆናል።



## 2. መንፈሳዊ መሪዎች ሥራን ለሌሎች የማያከፋፍሉበት ምክንያት ምንድነው?

ሥራን ወይም ኃላፊነትን ማከፋፈል ብዙ ጥቅም እንዳለው ቢታወቅም አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ሌሎች በችሎታቸውና በዝንባሌያቸው መሠረት እንዲያገለግሉ ዕድል የማይሰጡበት ምክንያቱ ምን ይሆን? አንደኛውና ትልቁ ምክንያት፣ ብዙዎቹ “ሥራ ላይ ያተኮረ ሕይወት” ስላላቸው ነው። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ሁሉንም ሥራ ብቻቸውን ለመሥራት ያላቸው ጊዜም ሆነ አቅም የተወሰነ መሆኑን የሚረዱት አይመስሉም።

- *ሥራውን ወይም ኃላፊነቱን ለሌላው ሰው ቢሰጡ፣ ከእነርሱ በተሻለ ሁኔታ ይሠራው ይሆናል ብለው ይፈራሉ። የተሻለ አድርጎ ከሠራው የነርሱን ደካማነት ያሳይና ሥልጣናቸውን ወይም ሥራቸውን የሚወስድባቸው ስለሚመስላቸው ነው።*
- *ሥራውን ወይም ኃላፊነቱን ለሌሎች ካከፋፈሉ፣ ሁኔታዎች ከቁጥጥራቸው ውጪ ይሆናል ብለው ስለሚፈሩ ነው።*
- ክብርና ዝናን ስለሚፈልጉ፣ *ሥራውን ወይም ኃላፊነቱን ለሌላው ሰው ከሰጡ፣ ያ* ሰው ከእነርሱ የበለጠ ክብርን ያገኝ ይሆናል ብለው ይፈራሉ። ሌላው ከተመሰገነና ክብርን ካገኘ፣ እነርሱ ሥልጣናቸውን የሚያጡ ስለሚመስላቸው ነው።
- *ሥራውን ወይም ኃላፊነቱን ለሌላው ሰው ቢሰጡ፣ ያ ሰው ጥሩ አድርጎ አይሠራውም ይሆናል ብለው በማሰብና በመስጋት ነው። በራሳቸው እምነት የሌላቸው መሪዎች፣ በሌሎችም ላይ እምነት አይኖራቸውም። በዚህ ምክንያት ኃላፊነት ለሌላው መስጠት አይፈልጉም።*
- ሁልጊዜ *ሥራውን* እነርሱ ከሚሠሩት ሌላው ቢሠራው፣ *ሥራው* የበለጠ የተቀላጠፈ እንደሚሆን ቢያምኑም፣ ያንን *ሥራ* ሌላው እንዲሠራው ማሰልጠን አይፈልጉም። ለዚህም ትልቁ ምክንያታቸው፣ “ማሰልጠን አልችልም ይሆናል” የሚል ፍርሃት ስላላቸው ነው። “ሌላውን ማሰልጠን ጊዜ ስለሚጠይቅ፣ እኔው ራሴ ብሠራው ይሻላል” ይላሉ።
- *ሥራን ወይም ኃላፊነትን* ለሌሎች ካከፋፈሉ፣ *ኃላፊነት* ያልተሰጣቸው ሰዎች ተቀይመው የሚሸሿቸው ስለሚመስላቸው፣ ማንንም ላለማስቀየም ሲሉ *ሥራውን* ሁሉ ለብቻቸው *ለመሥራት* ይወስናሉ።
- *መንፈሳዊ መሪዎች ሥራን ወይም ኃላፊነትን* ለሌሎች እንዴት ማከፋፈል እንዳለባቸው በቂ የሆነ መረዳት ስለሌላቸው ይሆናል።

- መንፈሳዊ መሪዎች የሚመሩትን ሕዝብ "ከየት ተነስቶ የት ማድረስ" እንዳለባቸው የማያውቁ፣ ግብም ሆነ መሥሪታዊ ዕቅድ የሌላቸው ከሆነ፣ ሥራው የሚጠይቀውን ጊዜና ጉልበት ተረድተው ኃላፊነቱን ለሌሎች ማከፋፈል አይችሉም።

## 3. ምዕመን ሁሉ አገልጋይ መሆን አለበት

በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምዕመን ሁሉ አገልጋይ፣ አገልጋይ ሁሉ ምዕመን መሆን አለበት። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንጊዜም ቢሆን ተዋንያንና ተመልካች ሊኖር አይገባም። መገልገል ብቻ ሳይሆን፣ ማገልገልም ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። አማኞች አይረዱት እንጂ፣ ለእያንዳንዱ ምዕመን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተሰጥቶታል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ሁሉም በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አገልግሎቱን መፈጸም አለበት። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ይፈልጋል። ምዕመናን ሁሉ የአገልግሎት ተሳትፎ ከሌለው ግን፣ ቤተ ክርስቲያን እንደሚገባት ማደግ አትችልም። ምዕመናን ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውና ችሎታቸው እየታየ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እንዲገቡ ዕድል ሲሰጣቸው ቤተ ክርስቲያን ትታነጻለች። አንዳንድ ምዕመናን የራሳቸውን ስጦታ ለይተው ማወቅ ስለማይችሉ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአገልግሎት ሥፍራቸውን መለየት እንዲችሉ በማስተማር ሊረዷቸው ይገባል። በምዕራቡ ዓለም፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለሚጨመሩት አዳዲስ ነፍሳት ይህንኑ በሚመለከት ነጥብ በቂ ትምህርት ይሰጣል። አንዳንዶቹ እንዲያውም ይህን ትምህርት ተምረው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን ለይተውካላወቁ የቤተ ክርስቲያን አባል አያደርጓቸውም። ጤናማ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን የሚመሩ እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች፥

- ወደ ቤተ ክርስትያን የሚመጡትን አዳዲስ ሰዎች እንግድነት ተሰምቷቸው ብቸኛ እንዳይሆኑ ከተቀሩት ምዕመናን ጋር የሚቀራረቡበትን ሁኔታ ያመቻቹላቸዋል።
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን እንዲያውቁ ይረዷቸዋል።
- ሥጦታቸውን በተግባር ላይ እንዲያውሉ፣ የአገልግሎት በር ይከፍቱላቸዋል።
- አገልግሎታቸውን መፈጸም የሚያስችላቸውን ትምህርት በየጊዜው ይሰጧቸዋል።
- የቤተ ክርስቲያኒቱ አካል ሆነው፣ አገልግሎቷን ለመፈጸም እንድትችል እነርሱም የሚጫወቱት ከፍተኛ ሚና እንዳለ ያሳውቋቸዋል።
- የቤተ ክርስቲያኒቱ ራዕይና የአገልግሎት ዓላማው ምን እንደሆነ እንዲያውቁና እነርሱም ያንን ለመፈጸም ድርሻ እንዳላቸው እንዲያውቁ ያደርጓቸዋል።



የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትልቁ ሥራቸው፣ *"...ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት..."* እንደሆነ ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች በጻፈው መልዕክቱ ይገልጻል (ኤፌ. 4፥12)። ለአገልግሎት ቅዱሳንን የሚያዘጋጁት እንዴት ነው? ቅዱሳንን ለአገልግሎት መዘጋጀት ያለባቸው በሁለት ነገር ነው። ይኸውም፣ አንደኛው *"ዕውቀት" (Knowledge)* በመስጠት ሲሆን፣ ሁለተኛው *"የአሠራር ዘዴ" (Skill)* በማስተማር ነው። መንፈሳዊ መሪዎች ቅዱሳንን ለአገልግሎት በሚያዘጋጁበት ወቅት ሁለት ዓይነት እንቅፋቶች ሊያጋጥሟቸው ይችላል። አንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ላይ ብቻ የበለጠ ትኩረት ይሰጡና፣ ማገልገል የሚያስችላቸውን የአሠራር ዘዴን ማስተማር ግን ችላ ይሉታል። ምዕመናንን እንደሚገባ ሳያዘጋጁ አገልግሎት ላይ ማሰለፍ፣ ምዕመናኑ የሚያደርጉትን ባለማወቅ ምን ያህል ግራ እንደሚጋቡና ተስፋ እንደሚቆርጡ በመሪነት የተቀመጡ ሁሉ ሊያውቁት ይገባል። አብዛኛዎቹ ምዕመናኑን የሚያስተምሩት እንዴት ማመን እንደሚችሉ ብቻ እንጂ እንዴት እንደሚያገለግሉ በቂ ትምህርት አይሰጧቸውም። ሌላው ችግር መሪዎች ምዕመናኑን እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው ለማስተማር ጥረት ሲያደርጉ፣ የሚጠብቁትን ዓይነት ውጤት ቶሎ ካላዩ፣ "ከዚህ ሁሉ እኔው ራሴ ብሠራው ይቀላል" በማለት አገልግሎቱን ሁሉ ብቻቸውን መያዛቸው ነው። ጥቂት መንፈሳዊ መሪዎች ምዕመናኑ ባላቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዲያገለግሉ በማስተማርና በማሰማራት ፈንታ ሥራውን ሁሉ ብቻቸውን ለመሥራት ሲሞክሩ ከአቅማቸው በላይ ይሆንባቸውና ተስፋ ቆርጠው፣ አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑትን አገልግሎቶችን ችላ ብለው ያልፉታል። እዚህ ላይ ችግሩ ሥራው አለመሠራቱ ብቻ ሳይሆን፣ ምዕመናኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎት ተሳትፎ ሳይኖራቸው፣ ተመልካች ብቻ ሲሆኑ፣ ተስፋ ቆርጠው ከቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚርቁ መሆናቸው ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሚያዘው መሠረት መሪዎች ቅዱሳንን ለአገልግሎት የሚያዘጋጁት፣ እነርሱ በተራቸው ሌሎችን ማገልገል እንዲችሉ ነው። ይህን የሚያደርጉት፣ "የክርስቶስ አካል እንዲገነባ (እንዲያድግ)" ነው። አዎን! እግዚአብሔር የራሱ ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ይፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን የምታድግበትን ሦስት አቅጣጫ ዶክተር አንደርሰን በመጽሐፋቸው ጠቅሰዋል።[29]

1) ክርስቶስን በማወቅ የነፍሳት ቁጥር እንዲያድግ ነው (የማቴ. 28፥18-20፥ ማር. 16፥16)፣
2) ቅዱሳን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ (እንዲበስሉ) እግዚአብሔር ይፈልጋል። ጳውሎስ በምን ዓይነት ሁኔታ ማደግ እንደሚያስፈልግን ሲጽፍ፣ "...ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና

[29] Anderson, Lynn. They Smell Like Sheep, Howard Publishing Co. West Monroe, Louisiana, 1997.

ሙሉ ሰው በመሆን በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስክምንደርስ ነው" ይላል (ኤፌ. 4፥13)።

3) የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑ በአካል አንድነቷ (Organically) እንድታድግ ይፈልጋል። ይኸውም ምዕመናን እርስ በርስ ያላቸው አንድነት ወይም ግንኙነት ነው። ጳውሎስ ይህንን እሳብ በመልዕክቱ ሲገልጸው፣ "ከእርሱም የተነሳ አካል ሁሉ በሚያገናኘው ጅማት እየተያያዘና እየተጋጠመ፣ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል" (ኤፌ. 4፥16) ይላል።

እግዚአብሔር የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያኑ ጤናማ የሆነ ዕድገት ያላትና እርስ በርሷ የተያያዘች ሆና አገልግሎቷን እንደሚገባው እንድትፈጽም ይፈልጋል። መንፈሳዊ መሪዎች ምዕመናኑን ለአገልግሎት የሚያዘጋጁት መንፈስ ቅዱስ ለያንዳንዱ ምዕመን በሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መሠረት እንጂ፣ ቅርባቸው ለሆኑት አማኞች የሚያከፋፍሉት አይደለም፡

- መንፈሳዊ መሪዎች ለምዕመናን የሚሰጧቸው ሥራ ማንኛውንም ዓይነት ሥራ መሆን የለበትም፥
- ለአማኞች የሚሰጣቸው አገልግሎት (ሥራ) ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸው ጋር አብሮ የሚሄድና በዚያ መስክ ተሰልፈው ለማገልገል ፈቃደኝነታቸው ታይቶ መሆን አለበት፤
- በተመደቡበት አገልግሎት ውስጥ ጥሩ አድርገው ማገልገል እንዲችሉ ሥራውን እንዴት እንደሚሠሩ የአሠራር ዘዴ ከመንፈሳዊ መሪዎች መማር አለባቸው።

የማገልገል ችሎታም ሆነ ፈቃደኝነት ያላቸው ብዙ አማኞች በየቤተ ክርስቲያኑ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ይኖራሉ። የማገልገል ዕድል ተሰጥቷቸው ማገልገል ቢችሉ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጉ ነበር። በተጨማሪ ምዕመን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው ስጦታ መሠረት የአገልግሎት ተሳታፊ ቢሆኑ፣ በአገልግሎት በጣም ለሚደክሙና ለሚባዝኑ አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ምን ያህል ትልቅ ዕርዳታ ይሆኑ ነበር! ሁሉም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ተሳትፎ ቢኖራቸው፣ በቤተ ክርስቲያኒቷ እንቅስቃሴ ውስጥ ሥፍራ እንዳላቸው ተሰምቷቸው ደስ ብሏቸው ስለሚያገለግሉ፣ በጥቂት መሪዎች ላይ ብቻ ሥራው ሁሉ አይከመርም ነበር። ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው፣ አገልግሎቱ የግድ መካሄድ ስላለበት ብቻ ስጦታውና ችሎታው የሌላቸው መሪዎች በየአገልግሎቱ ውስጥ ሁሉ እየገቡ ማገልገል ይጀምራሉ። ምዕመን ሁሉ ለማገልገል ፈቃደኞች ቢሆኑ ኖሮ ሥራው ችሎታውና ስጦታው ባላቸው ምዕመናን መሠራቱ ብቻ ሳይሆን፣ መሪዎችም ከአገልግሎት ብዛት የተነሳ መጨነቃቸው ይቀር ነበር። ምድራዊ ወላጆች



ትልቁ ኃላፊነታቸው ልጆቻቸው የተፈጥሮ ስጦታቸውንና ዝንባሌያቸውን እንዲያውቁና እንዲያዳብሩ ማደፋፈር ሲሆን፣ ልክ እንደዚሁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ምዕመናን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን እንዲያውቁና እንዲያዳብሩ፣ እንዲሁም እያንዳንዱ የአካል ክፍል አገልግሎቱን እንዲሰጥ ማደፋፈር አለባቸው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲመክረው፣ *"ከብዙ ምስክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ"* ይለዋል (2 ጢሞ. 2፥2)።

## 4. የመንፈሳዊ መሪ ዋና ተግባሩ ምንድነው?

መንፈሳዊ መሪዎች ዋናው ኃላፊነታቸው ምዕመናንን በአገልግሎት ማዘጋጀትና መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው የጸጋ ስጦታ መሠረት አገልግሎት ላይ ማሰማራት ነው። ጥያቄው ግን ይህን የሚያደርጉት በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? አንደኛውና ትልቁ ክርስቶስ የሠራበትን መንገድ መከተል ነው። ሰዎች አዲስ መሪ ሲመርጡ፣ ከዚያ ሰው የሚጠብቁት ምንድነው? የታወቁት ጸሀፊ ፒተር ድራክር (Peter Drucker) *"የመሪነት መለኪያው 'ውጤት' ነው" አሉ።*[30] መሪው አጥጋቢ ውጤት ካላሳየ ጥሩ መሪ አይባልም። በንግድ ዓለም ውስጥ ዋና ሥራ አስኪያጅ መርጠው ሲሾሙ የሥራ አስኪያጁን ጥሩ መሪነት የሚለኩት በሽያጩና በሚገኘው ትርፍ ነው። ሽያጩ ከፍ ሲል፣ አዳዲስ የንግድ ዕቃዎች ሲጨመሩ፣ አዳዲስ ገበያተኞች ሲበዙ፣ ማከፋፈያ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሲጨመሩ፣ ያኔ ሥራ አስኪያጁ ጥሩ የአመራር ችሎታ እንዳለው ይታወቃል። መልካም ውጤትን በቁጥር መለካት የሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው። በመንፈሳዊው ዓለምም ሰዎች የአገልግሎታቸውን መለካት በቁጥር የመለካት ዝንባሌ አላቸው። ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣው ሰው ቁጥር፣ የሚድነው ሰው ቁጥር፣ እንዲሁም የአሥራቱ መጨመር የቤተ ክርስቲያኑን ስኬታማነት መለኪያ እየሆነ ነው። ውጤትን በቁጥር ማስሰና መብዛት መለካት ብዙዎ ችን ውጤት እንዲያሳዩ ግፊትን እየጨመረ ነው። የሚያገኙትን ውጤት በቁጥር መለካት እንዲችሉ በብዙዎች ዘንድ ዓላማ (ግብ) አስቀድሞ ማበጀት የተለመደ ሆኗል። መሪዎች ከአሰቡበት ዓላማ (ግብ) ከደረሱ፣ ጥሩ መሪነታቸውን ያውጃሉ። ካሰቡበት ዓላማ ለመድረስ ያሉበት ድርጅት ወይም ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለ ግን አያዩም። መንፈሳዊ መሪዎች ግን ትልቁ ኃላፊነታቸው ካሰቡበት ግብ ወይም ዓላማ መድረሳቸው ባይሆን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም መቻላቸው ነው። መንፈሳዊ መሪዎች ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ሆነው፣ ካቀዱት ግብ (ዓላማ) መድረስ ይችላሉ። ከግባቸው መድረሳቸው እግዚአብሔር የባረካቸው መሆኑን የሚያሳይ ምልክት አይደለም። መንፈሳዊ መሪዎች እግዚአብሔር የሰጣቸው ኃላፊነት፣

---

[30] Drucker, F. Peter. Foreword to The Leader of the Future, edited by Francis Hasselbein, 1996.

የእግዚአብሔር ሕዝብ የእርሱን አጀ ንዳ እንዲከተሉ ማድረግ ነው። ቤተ ክርስቲያን
አዲስ ያማረ ሕንጻ ብታሠራ፣ በህንጻው ሥራ ምክንያት ግጭት፣ መራራነትና መከፋፈል
ተፈጥሮ ብዙዎች ከቤተ ክርስቲያን ቢርቁ መሪው የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚከተል
አገልጋይ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ውጤቱ እግዚአብሔርን ስለማያስከብር፣ መሪውን
ጥሩ መሪ አያሰኘውም።

## 4.1. መሪዎች ሌሎች መሪዎችን ይመራሉ

መሪዎች ተከታዮቻቸውን ይመራሉ። ታላላቅ መሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ያሉትን
መሪዎችን ይመራሉ። መሪዎች የሚያሳዝን ትልቅ ስህተ የሚሠሩት ራሳቸውን ምትክ
የሌላቸው አድርገው ሲያቀርቡ ነው። አንዳንድ ጊዜ በራሳቸው እምነት የሌላቸው አን
ዳንድ መሪዎች፣ ማንም ሰው እንዳይወዳደራቸው ለሌሎች የመምራት ዕድል ይነፍጋሉ።
አንዳንድ መሪዎች በራሳቸው ሥራ ላይ ከመጠን በላይ በመያዛቸው ምክንያት ሌሎችን
በአገልግሎት ማሳደግ እንዳለባቸው ይረሳሉ። እውነተኞች ሆነው እውነቱን ቢናገሩ
ብዙዎች ምትክ የሌላቸው መሪዎች ሆኖ መገኘትና መታየት ደስ እንደሚያሰኛቸው
ይናገሩ ነበር። ሳሙኤል በዘመኑ እስራኤል ከነበሯት መሪዎች ሁሉ ተወዳዳሪ ያልነበ
ረው፣ እግዚአብሔርን የሚፈራና የሚያከብር ጥሩ መንፈሳዊ መሪ ነበር። ይሁን እንጂ
ራሱን የሚተካ ሰው አላዘጋጀም ነበር።

- "ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ ልጆቹን ፈራጆች አድርጎ በእስራኤል ላይ ሾማ
ቸው። የበኩር ልጁ ኢዮኤል ሲሆን፣ ሁለተኛው ልጁ አብያ ነበረ፤ እነር
ሱም በቤርሳቤህ ይፈርዱ ነበር። ነገር ግን ልጆቹ የአባታቸውን ፈለግ አል
ተከተሉም፤ ተዝቢ ያልሆኑ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ከመንገዱ ወጡ፤ ጉቦ
ተቀበሉ፤ ፍርድም አጣመሙ። ስለዚህ የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ
በአንድነት ተሰብስበው ሳሙኤል ወዳለበት ወደ አርማቴም መጡ። እነር
ሱም 'አንተ አርጅተሃል፤ ልጆችህ ያንተን ፈለግ አይከተሉም፤ ስለዚህ
ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያደርጉት ሁሉ የሚመራን ንጉሥ አንግሥልን
አሉት። ነገር ግን 'የሚመራን ንጉሥ አንግሥልን' ማለታቸው ሳሙኤልን
አላስደሰተውም፤ ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ" (1 ሳሙ. 8፥1-6)።

ሳሙኤል በመጨረሻ ሕይወቱ በሁለት አቅጣጫ ደካማነት ታየበት። አንደኛው፣
ልጆቹን እንደሚገባው ኮትኩቶ ባለማሳደጉ ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ሙሴ ከእርሱ በኋላ
የሚተካውን መሪ ኢያሱን እንዳዘጋጀ፣ ሳሙኤል ግን እርሱን የሚተካው መሪ ያላዘጋጀ
መሆኑ ነው። ሳሙኤል መሪ በነበረበት ዘመን የእስራኤል ሕዝብ ያለአንዳች ተቃውሞ
ተከተሉት። በምትኩ ግን ብቃት የሌላቸውን ልጆቹን ኢዮኤልንና አብያን ፈራጆች አድ
ርጎ ሲሾማቸው፣ እስራኤላውያን ተቃውሟቸውን ማሰማት እንደ ጀመሩ ታሪክ ይመሰክ



ራል። የሳሙኤል ስህተት ዛሬም በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተደገመ ነው።
የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎችን በአገልግሎት በማሳተፍ መጪውን ትውልድ ለመሪ
ነት በማዘጋጀት ፈንታ፣ ብቻቸውን የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ሲሞክሩ ይታ
ያሉ። የአንድ መንፈሳዊ መሪ አገልግሎት ፍሬያማ መሆኑ የሚታወቅበት፣ የእግዚአብ
ሔር ሥራ በዘመናት ሁሉ እንዲቀጥል፣ እርሱን የሚተኩ ሌሎች መሪዎችን ሲያፈራና
በአገልግሎት ሲያሰታጥቅ ነው። ስለዚህ መንፈሳዊ መሪ አገልግሎቱ ፍሬያማ እንዲሆን፣
የወደፊት መሪዎችን ማፍራት፣ እንዲሁም የአመራር ልምድ እንዲኖራቸው የአገልግሎ
ትን በር መክፈት፣ ተቀዳሚ የሆነ ኃላፊነቱና አገልግሎቱ አድርጎ መውሰድ አለበት።

## 4.2. ሥራንና ኃላፊነትን ለሌሎች ያከፋፍላሉ

አሁን በአገልግሎት የተሰማራነው ሰዎች እንዴት ነው ጌታን ማገልገል የቻልነው?
የናንተን አላውቅም የራሴን ልምምድ ባካፍላችሁ። በፊንላንድ ሚሽን ውስጥ ጌታን
እንደተቀበልኩ፣ ማንም "ይህን አድርግ" ብሎ ትዕዛዝ ሳይሰጠኝ፣ በእኔ ዕድሜ ያለ ልጅ
ማድረግ ያለበትን ነገር ማድረግ ጀመርኩ። የቤተ ክርስቲያኒቱ ፕሮግራም ከመጀመሩ
በፊት እየመጣሁ ወንበሮቹን መደርደር፣ የመዝሙር መጽሐፍ ለሕዝቡ ማደል፣ ፕሮግ
ራሙ ካለቀ በኋላ የመዝሙር መጽሐፎችን ሰብስቦ ከተመደበለት ሥፍራ ማስቀመጥ፣
በጌታ ቤት የአገልግሎት ድርሻዬ አድርጌ በመቀበል በታማኝነት እሠራ ነበር። ይህንን
ትንሿን አገልግሎት በታማኝነት መሥራቴን የተመለከቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች
መጀመሪያ የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎችን በማስተርጎም እንድረዳ፣ ከዚያም ቀስ
በቀስ ምስክርነቴን በመስጠት እንዳገለግል፣ ቀጥሎ በዋናው ስብሰባ ላይ ከእንግሊዝኛ
ወደ አማርኛ ስብከቱን እንዳስተረጉም ዕድል ይሰጡኝ ነበር። ጌታ የሚያየው ትልቅ
ሥራ መሥራታችንን ሳይሆን፣ የተሰጠንን አገልግሎት በታማኝነት መፈጸማችንን እንደ
ሆነ ከላይ የገለጽኩት ልምምዴ በሕይወቴ ትልቅ ትምህርት ሰጥቶኛል። የአገልግሎታ
ችን ፍሬያማነትን ጌታ የሚለካው፣ በምንሠራው ሥራ ብዛት ሳይሆን፣ የሰጠንን በታማኝ
ነት መሥራታችን እንደሆነ የማያጠራጥር እውነት ነው። ጌታን ለማገልገል ያለኝን
ጥማት ማየት ችለው የአገልግሎት በር የከፈቱልኝ ሰዎች ዛሬ ለደረስኩበት የአገልግሎት
ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉልኝ ስለሆነ ምንጊዜም አልረሳቸውም። ሌሎች ዝንባ
ሌያችንን አይተው የማገልገል ዕድል እንደሰጡን ሁሉ፣ እኛም ለሌሎች የአገልግሎት
ዕድል መስጠት አለብን።

## 4.3. በሥራቸው ያሉትን ፍሬያማ አገልጋይ እንዲሆኑ ያሳድጋሉ

ለአገልግሎት ያለንን ጥማትና ዝንባሌ አይተው የአገልግሎት በር መክፈት ብቻ
ሳይሆን፣ በሕይወታችንና በአገልግሎታችን ዕድገት እንድናገኝ በተለያየ መንገድ ዕር
ዳታ ያደረጉልንን መንፈሳዊ መሪዎቻችንን ፈጽሞ አንረሳቸውም። ወላጆች የሆንን ልጆ

ችን ማሳደግ የሚያስከፍለውን ዋጋ እናውቃለን። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሠራናቸው ስሁተቶች ይኑሩ እንጂ፣ ልጆቻችንን ለማሳደግ ብዙ መስዋዕት ከፍለናል። ልክ እንደዚሁ በጌታ ቤት ውስጥ በማደግ ላይ ያሉትን በእግዚአብሔር ቃል እየኮተኮቱ ማሳደግ ቀላል እንዳልሆነ እናውቃለን። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ትርምስ፣ ጠርነት፣ መከፋፈል፣ ጥርስ መሳበር፣ ወዘተ. በዝቶ የሚታየው፣ በእግዚአብሔር ቃል ሳይኮተኮቱ ያደጉ አገልጋዮች የበዙበት ዘመን በመሆኑ ነው። አንዳንዶቻችን ዛሬ ሆነን የተገኘነው በአንድ ጊዜ በቅለን በአንድ ጊዜ ያደግን ሳንሆን፣ አንዳንድ ሰዎች ስለ እኛ ሕይወትና አገልግሎት ከፍተኛ ዋጋ ስመክፈላቸው ነው። እኛ ብንረሳቸው እንኳ ጌታ አይረሳቸውም።

## 4.4. በሥራቸው ያሉትን እምነት ኖሯቸው ኃላፊነትን ይሰጣሉ

እኔና ጓደኞቼ ፊንላንድ ሚሽን ጌታን ካገኘን በኋላ በቃሉ እየተኮተኮትን የምናድግበት ሰፊ ዕድል ነበረን። አንድ ነጥብ ላይ ስንደርስ፣ ገና ሳናድግ "አደግን" ብለን ይሆን፣ ወይም መሪዎቻችን "አድገዋል" ብለው እምነት ሊጥሉብንና ኃላፊነት ሊሰጡን በማመንታታቸው ይሁን አናውቅም፣ በአስተማሪዎቻችንና በእኛ መካከል ግጭት ተፈጠረ። "ሁልጊዜ ልጆች ናችሁ አትበሉን፤ እናንተ ባታምኑብን እኛ በራሳችን እምነት አለን" አልናቸውና ቤተ ክርስቲያኑን ጥለን ወጣን። ጥፋቱ የእነርሱ ሳይሆን፣ እኛ ልጆች በመሆናችን እንደሆነ እርግጠኞች ነን። ይሁን እንጂ፣ እኛ ብናበላሽም እግዚአብሔር ያንን ሁኔታ ለበጎ ተጠቀመበትና "ለሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን መወለድ" ምክንያት ከሆኑት ሰዎች መካከል አንደኛው ክፍል ሆንን። ስለዚህ በእኛ ኃላፊነት ሥር ያሉትን የአገልግሎት በር መክፈት፣ አቅማቸው በሚፈቅደው መሠረት ማገልገል እንዲችሉ በእምነት ኃላፊነት ልንሰጣቸው ይገባል። ኢየሱስ ከጸለየ በኋላ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ጊዜ ወስዶ በጥንቃቄ መረጣቸው። ሲመርጣቸውም፣ ከሦስት ዓመት ተኩል በኋላ አገልግሎቱን ለእነርሱ አደራ ብሎ አሳልፎ እንደሚሰጥ ያውቃል። የሚሰጣቸውን ኃላፊነት እስከ መጨረሻው ድረስ እንደሚጠብቁ እርግጠኛ ነበረ። ከመረጣቸው በኋላ ከአጠገቡ ሳይለዩ ቀንና ማታ ያስተምራቸው ነበር። ሲስቱ ይገስጻቸው ነበር። ሲደክሙ ያነቃቃቸው ነበር። በመጨረሻም ወንጌልን እንዲሰብኩ ኃይልንና ሥልጣኑን ከሰጣቸው በኋላ ኃላፊነቱን አስረከባቸው። ዛሬ ወንጌል ለእኔና ለእናንተ ሊደርሰን የቻለው እነርሱ በከፈሉት ከፍተኛ ዋጋ ነው። እኛም በተራችን ከእኛ ቀደም ያሉ ሰዎች የሰጡንን ወንጌል እንደሚገባው ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ አለብን። ይሄም ምርጫችን ሳይሆን፣ ግዴታችን ነው።



## 5. ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናኑን ለአገልግሎት ያዘጋጃል (ያሳትፋል)

የአብያተ ክርስትያናን ዕድገት ከሚያግዱ ልዩ ልዩ ምክንያቶች መካከል አንደኛው አዳዲስ ነፍሳት ከቆዩት የቤተ ክርስቲያን አባሎች ጋር መዋሃድ አለመቻላቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ምዕመናኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማገልገል ዕድል ማጣታቸው ነው። አዳዲስ ነፍሳት ተጋብዘውም ሆነ በተለያየ ምክንያት በየጊዜው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ። መጀመሪያ ላይ ከምዕመናኑም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተደረገላቸው ጥሩ አቀባበል ደስ ይላቸውና ደጋግመው መምጣት ይጀምራሉ። እየቆዩ ሲመጡ፣ መጀመሪያ ላይ ያዩት ፍቅር እየቀዘቀዘ ይመጣባቸዋል። ለተወሰነ ጊዜ ከማንም ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ሳይኖራቸው ቤተ ክርስቲያን እየመጡ እምልከው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ምንም ዓይነት የአገልግሎት ተሳትፎ የላቸውም። የሚቀርቡትና የሚቀርባቸው ሰው ባለመኖሩ ብቸኝነት እየተሰማቸው ይመጣል። በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ምንም ዓይነት ዕድገት አያዩም። በመጨረሻ ከቤተ ክርስቲያን ይቀራሉ። ቢቀሩም፣ "እነ እከሌ ከቤተ ክርስቲያን ለምን ቀሩ?" የሚል ፈላጊ አይኖራቸውም። በዚህ ዓይነት ብዙዎች ጠፍተው ይቀራሉ። እግዚአብሔር የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ሆና እንድታድግ ይፈልጋል። ዘላቂነት ያለው ጤናማ የሆነ ዕድገት ማሳየት የምትችለውም፣ ምዕመናኑ እርስ በርሱ ሲያያዝና ለአገልግሎት የሚያበቃ ዝግጅት ሲኖራቸው፣ እንዲሁም ምዕመኑ ሁሉ የማገልገል ዕድል ሲሰጣቸው ነው። ዕድገት የሚታይባት ጤናማ ቤተ ክርስቲያን፣ መሪዎቿ ምዕመናኑን ሁሉ አገልጋይ በማድረግ የሚያምኑና ጥረት የሚያደርጉ ሲሆኑ ነው። በማደግ ላይ ያለች ጤናማ ቤተ ክርስቲያን፦

- የሚመጡትን አዳዲስ ነፍሳት በፍቅር ተቀብላ ታስተናግዳለች፣
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን ለይተው እንዲያውቁ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንደሚገባው ታስተምራለች፣
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን አይታ በስጦታቸው እንዲሰማሩ በር ትከፍታለች፣
- በተመደቡበት አገልግሎት ፍሬያማ አገልግሎት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ስልጠና ትሰጣለች፣
- በየጊዜው ለአገልግሎታቸው ጠቃሚ የሆነውን መመሪያና ምክር ትሰጣለች፣

- አገልግሎታቸውን ከጌታ እንደተቀበሉት አድርገው እንዲይዙትና ሌሎችን እንዲያገለግሉበት ታበረታታለች፣”[31]

ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የሰጠው፣ አማኞች አገልግሎታቸውን እንደሚገባ መፈጸም እንዲችሉ ለማስታጠቅ ነው። ጳውሎስ ኤፌሶን ምዕራፍ 4 ላይ *“ነገር ግን ክርስቶስ በወሰነው መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል... (ቁ. 7) ...አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎች ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው”* ይላል (ቁ. 11)። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲሁ የበቀሉ ሳይሆኑ፣ ከጌታ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው። ኃላፊነታቸውም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሥራዎች ሁሉ እነርሱ ብቻ እንዲሠሩት ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት ማዘጋጀት ወይም ማስታጠቅ ነው። ጳውሎስ ይህን ሀሳብ በግልጽ አስቀምጦታል። *“...የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት...”* ይላል (ኤፌ. 4፥12)። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቅዱሳንን ይመግባሉ፣ ይመራሉ... ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ግን አያዘጋጁም። ዋናው ምክንያት ብዙዎች ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ የማዘጋጀት ኃላፊነት እንዳለባቸው፣ እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ባለማወቃቸው ነው።

ቅዱሳንን ለአገልግሎት ማዘጋጀት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት፣ ቅዱሳን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን አገልግሎት መፈጸም እንዲችሉ ነው። አማኞች አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙበት ምክንያትም ጳውሎስ በግልጽ እንደተናገረው፣ “የክርስቶስ አካል እንዲገነባ” ነው። ቀደም ሲል እንደገለጽነው እግዚአብሔር የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ይፈልጋል። ጳውሎስ *“ከእርሱም የተነሣ፣ አካል ሁሉ በሚያግዙት ጅማት እየተያያዘና እየተጋጠመ፣ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል”* (ኤፌ. 4፥16) ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ቤተ ክርስቲያን በሦስት አቅጣጫ ማደግ አለባት። ይኸውም፥

- ጠፍተው የነበሩት ወደ ጌታ በብዛት እንዲመጡ፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያ በቁጥር እንድታድግ እግዚአብሔር ይፈልጋል፣
- በማዕበል ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተነዱ፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ እንዳይንገዋለሉ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ይፈልጋል፣
- እርስ በርሳቸው በመያያዝና በመጋጠም እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር እንዲያድግ እግዚአብሔር ይፈልጋል።

[31] Lynn Anderson. They Smell Like Ship, Howard Publishing Co. West Monroe, Louisiana, 1997.



እግዚአብሔር ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ያለው ፍላጎት ከላይ የገለጽነውን ዓይነት ጤናማ የሆነ ዕድገት ነው። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ መሪዎች እንዲሆኑ የጠራቸው መንፈሳዊ መሪዎች ኃላፊነታቸውን እንደሚገባ መወጣት ሲችሉ፣ሚዛኑን ያልሳቀቀ፣ ጤናማ የሆነ፣ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ዕድገት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታያል። አማኝ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያለው በመሆኑ፣ እያንዳንዱ የአካሉ ክፍል ምን መሥራት እንዳለበት የሚወስነው፣ መንፈስ ቅዱስ በሰጠው ስጦታው ነው። ሁላችንም በልባችን ውስጥ አንድ ዓይነት መንፈስ ይኑረን እንጂ ስጦታችን ግን የተለያየ ነው። *“...እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል”* (1 ጴጥ. 4፥10) ይላል። እግዚአብሔር ስጦታዎችን ለአማኞች የሰጠው፣ *“...ለጋራ ጥቅም”* (1 ቆሮ. 12፥7) እንዲሁም ራስን ሳይሆን፣ *“ሌላውን ለማገልገል”* ነው (1 ጴጥ. 4፥10)።

አማኞችን ለአገልግሎት ለማስታጠቅ (ማዘጋጀት)፣ እግዚአብሔር የሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምን እንደሆነ መጀመሪያ ማወቅ ያስፈልጋል። ክፍት የአገልግሎት ሥፍራ ሲኖር፣ መንፈሳዊ መሪው ቅርቡ የሆነውን ሰው “በዚህ አገልግሎት ውስጥ ገባና አገልግል” ማለቱ ብቻ አጥጋቢ ውጤት አያመጣም። ምዕመናኑን ለአገልግሎት የሚያዘጋጀው መንፈሳዊ መሪ፣ ምዕመናኑ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታውን እንዲያውቅ አስፈላጊውን ዕገዛ ማድረግ ተቀዳሚ ሥራው መሆን አለበት። ስለዚህ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ ቤተ ክርስቲያኑ ጤናማ የሆነ ዕድገት እንዲኖራት፣

1ኛ/ አማኞች ውጤት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ በአገልግሎት ውስጥ ማሳተፍ፣

2ኛ/ እንዲያገለግሉ የተሰጣቸው የአገልግሎት መስክ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውና ለዚያ አገልግሎት ያላቸው ፍቅር በቅድሚያ ማገናዘብ፣

3ኛ/ የተመደቡበትን አገልግሎት እንደሚገባው መፈጸም እንዲችሉ አስፈላጊውን ሥልጠና መስጠት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያለባቸው ኃላፊነት ነው።

በየቤተ ክርስቲያኑ ልዩ ልዩ ስጦታ እያላቸው፣ ምንም ሳያደርጉ እጃቸውን አጣምረው የተቀመጡ አማኞች ጥቂቶች አይደሉም። “ተሳትፎ ይኑራቸው” በማለት ብቻ ያለስጦታቸው፣ ደስ በማይላቸውና በማይወዱት አገልግሎት ውስጥ ማሰለፍ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ሌላው ጥሩ አድርጎ ሊሠራው የሚችለውን አገልግሎት፣ ስጦታው በሌለው ሰው ማስያዝ ይሆናል። አማኞች ባላቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መሠረት የአገልግሎት ተሳታፊ ሲሆኑ፣ ደስ ብሏቸው ያገለግላሉ። የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ሁሉ እንደ ስጦታው የሚያገለግል ከሆነ፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ትከሻ ላይ ሊነሳ የሚችለውን የኃላፊነት ሸክም መገመት አያዳግተንም። ሁሉም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ድርሻ ሲኖረው፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓላማ ተካፋይ፣ የአካሉ ክፍል ወይም የሕብረቱ አባል እንደሆነ ይሰማዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን *“ከብዙ ምስክር*

*ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ሊታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ"* (2 ጢሞ. 2፥2) ሲል የመከረው ይህንኑ አሳብ ይዞ ነው። የቤት ክርስቲያን መሪዎች ትልቁ ኃላፊነታቸው የተማሩትን፣ ራሳቸው ያወቁትን እውነት "ለማስተማር ብቃት ላላቸው እምነት ለሚጣልባቸው ሰዎች አደራ መስጠት ነው። እነርሱም በተራቸው ለሚ ታመኑ አደራ መስጠት አለባቸው። ብቃታቸው የሚለካበት አንደኛው መንገድ "የሚታ መኑ" መሆናቸው ነው። ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ ከሰዎች ጋር የነበረው ግንኙነት የተለያየ የቅርበት ደረጃ ነበረው።

(1) ኢየሱስ ከሚያገለግላቸው ሰዎች ጋር የነበረው አንደኛው ዓይነት ግንኙነት፣ በብዙ ሺ የሚቆጠሩትን ሰዎችን ቃሉን ሲያስተምር፣ ሲመግብ የነበረው ዓይነት ግንኙነት ነው። *"በዚያን ጊዜ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ እርስ በርስ እስኪረጋገጥ ድረስ ተሰብስቦ ሳለ...እንዲህ እያለ ያስተምር ነበር..."* (ሉቃ. 12፥1) ይላል። በዚህ ዓይነት አገልግሎቱ ብዙ ነፍሳትን እንደነካና ብዙዎች እንዳመኑ አንጠራጠርም። ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ "ፍጹም አምላክ" ብቻ ሳይሆን፣ "ፍጹም ሰውም" በመሆኑ፣ እንደ ሰው በዚያን ወቅት ውስን በመሆኑ፣ ከብዙ ሕዝቡ ጋር በአንድ ጊዜ በጣም የተቀራረበ ግንኙነት ማድረግ አይችልም ነበር። ይህን በመሰለ ግንኙነት ውስጥ ያንን ሁሉ ሕዝብ ለአገልግሎት ማዘጋጀት፣ ደቀ መዝሙር ማድረግ አይችልም ነበር። የዘመኗ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም አንዳንዶች በአንድ ጊዜ በብዙ ሺ የሚቆጠሩትን ሰዎች የማስተማር ስጦታም ሆነ ዕድል ያላቸው ሊኖሩ ይችላሉ። ብዛት ያላቸውን ሰዎች ወደ ጌታ ማምጣት፣ በሕይወታ ቸው የሚታነጹበትን ትምህርት መስጠት ይችላሉ። ኢየሱስ መልዕክቱን ለማስተ ላለፍ ከተጠቀመባቸው መንገዶች አንደኛው በመሆኑ፣ በዘመናችንም ትላልቅ ስብሰባዎችን ማካሄድ ልክ አይደለም ማለት አንችልም። ይሁን እንጂ፣ መልዕክ ታችንን ለማስተላለፍ ሁልጊዜ ትላልቅ ስብሰባዎችን ብቻ ማካሄድ አለብን ማለት እንዳልሆነ ማወቅ ያስፈልገናል። ኢየሱስ ሁልጊዜ ትላላቅ ስብሰባዎችን (ክሩሴዶ ችን) ብቻ ማድረግ በቂ እንዳልሆነ ስለሚያውቅ፣ ይህንን መንገድ ብቻ አልተጠ ቀመም።

(2) ኢየሱስ ከሚያገለግላቸው ሰዎች ጋር የነበረው ሁለተኛው ዓይነት የቅርበት ደረጃ በመቶ የሚቆጠሩትን ሰዎች ሲያገለግል የነበረው ዓይነት ቅርበት ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን በኢየሩሳሌም ተሰብስበው የነበሩት መቶ ሃያዎችን (የሐዋ. 1፥15) ያገለገለበት ሁኔታ ነው። ኢየሱስ በመስቀል ሞቶ ከተነሳ በኋላ ጴጥሮስ በመቶ ሃያዎቹ መካከል ቆሞ እንደተናገረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"...ጴጥሮስ መቶ ሃያ በሚሆኑ ወንድሞች መካከል ቆሞ እንዲህ አለ..."* ይላል (የሐዋ. 6፥1)። እነዚህ መቶ ሃያ ሰዎች ክርስቶስ ከሞተ በኋላ የተገኙ አዳዲስ ነፍሳት (ሰዎች) ሳይሆኑ፣ ከክርስቶስ ጋር የቆዩ እንደነበረ ግልጽ ነው። እነዚህን መቶ ሃያዎቹን



ሲያገለግል የነበረው ግንኙነት ብዙ ሺ ሕዝብ ሲያገለግል የነበረውን ዓይነት አልነበረም። በመጠኑ ከሚያገለግላቸው ሰዎች ጋር ቅርበት ነበረው። በዚህ ደረጃ የሚያገለግላቸው ሰዎች እንደ መጀመሪያው ዓይነት ብዙ ሕዝብ ባይሆንም፣ መልዕክቱን በተወሰኑ ሰዎች ላይ ማሳረፍ ይችል ነበር። በዘመኗ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አባሎችን በሙሉ ሳይሆን የተወሰኑ አማኞችን፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ስላላት ራዕይ፣ ስለ ገንዘብ አቅሟ፣ እንዲሁም ምዕመናንን ሁሉ በአገልግሎት እንዴት ማሳተፍ እንደምትችል ለመወያየት ብርቱ ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን የተወሰኑ አማኞች እየሰበሰቡ ማስተማር፣ ማወያየት የቤተ ክር ስቲያንን ዕድገት ያፋጥናል።

(3) ኢየሱስ ከሚያገለግላቸው ሰዎች ጋር የነበረው ሦስተኛው ዓይነት የቅርበት ደረጃ ቁጥራቸው ሰባ ሁለት ከማይበልጡ ሰዎች ጋር የነበረው ግንኙነት ነው። አንድ ጊዜ ሰባ ሁለት ሰዎችን መርጦ ለወንጌል ስርጭት ልኳቸው እንደነበረ እናስታው ሳለን። *"ከዚህ በኋላ ጌታ ሌሎች ሰባ ሁለት ሰዎችን መርጦ ሾመ፤ ወደሚሄድበትም ከተማና ስፍራ ሁሉ እንዲቀድሙት ሁለት ሁለት አድርጎ ላካቸው፤ እንዲህም አላቸው..."* (ሉቃ. 10፥1) ይላል። ይሄኛው የቅርበት ደረጃ ከላይኛዎቹ የተሻለ ይሁን እንጂ፣ አሁንም በዚህ ደረጃ በጣም በተቀራረበ ሁኔታ ከሁሉም ጋር ግንኙ ነት መፍጠር አይችልም ነበር። በአሁኑ ዘመንም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ለተለየ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተወሰኑትን አሰልጥነው ለተፈለገው አገልግሎት ያዘጋጁቸዋል። እንደ ኢየሱስ የራሳቸው የሆኑ "ሰባዎች" የተለያየ ኃላፊነት የሚሰጧቸው ደቀ መዛሙርት አሏቸው።

(4) ኢየሱስ ከሚያገለግላቸው ሰዎች ጋር የነበረው አራተኛው የቅርበት ደረጃ ከ12ቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር የነበረው የተቀራረበ ግንኙነት ነው። እነዚህ 12ቱ ደቀ መዛ ሙርት በሦስት ዓመት ተኩል የአገልግሎት ዘመኑ ከአጠገቡ ያልተለዩት ናቸው። *"ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ አሥራ ሁለቱን ሾማቸው፤ ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው"* ይላል (የሐዋ. 3፥14)። አስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙ ርት፣ ኢየሱስ በሄደበት ሁሉ አብረው በመሄድ፣ እርሱ በተገኘበት ሥፍራ ሁሉ በመገኘት፣ በቅርብ ሆነው ሕይወቱን እያዩ እንዲማሩ ዕድል በመስጠት ወደ ፊት ለሚጠብቃቸው አገልግሎት እንደሚገባው ያዘጋጃቸው ናቸው።

(5) ኢየሱስ ከሚያገለግላቸው ሰዎች ጋር የነበረው አምስተኛው የቅርበት ደረጃ፣ ከሦ ስቱ ደቀ መዛሙርት፣ ይኸውም ከጴጥሮስ፣ ከዮሐንስና ከያቆብ ጋር የነበረው የቀ ረበ ግንኙነት ነው። ከነዚህ ከሦስቱ ጋር የነበረውን ዓይነት ቅርበት ከተቀሩት ደቀ መዛሙርቱ ጋር አልነበረውም። በከፍተኛው ተራራ ላይ ክብሩን የገለጸላቸው ለሦ ስቱ ብቻ ነበር። እንዲሁም በጌቴሴማኒ የደም ላብ እያላበው ሲጸልይ ይዟቸው የሄ

ደው እነዚህን ሦስቱን ብቻ ነበር። የዘመኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከኢየሱስ ተምረው ቅዱሳንን ለአገልግሎት ማዘጋጀት አለባቸው። ይሁን እንጂ፣ እንደ ኢየሱስ ሰዎች ስለሆኑ ቅርብ የሆነ ግንኙነት ሊመሠርቱ የሚችሉት ከተወሰኑ ሰዎች ጋር ብቻ ነው። ይህም ማለት መንፈሳዊ መሪዎችም አገልግሎታቸው እየሰፋ ሲማጣ፣ ከተወሰኑት ጥቂት ሰዎች ጋር ቅርበት ያለው ግንኙነት በመፍጠር ለአገልግሎት እነርሱን ማስታጠቅ አለባቸው። አንድ ጸሀፊ *"ማንኛውም ሰው እርሱ ከሚያውቀው የበለጠ ዕውቀት ካለው ከተማረ፣ እርሱ ደግሞ የሚያውቀውን ከእርሱ ያነሰ ዕውቀት ያለውን ካስተማረ፣ ሰው ሁሉ ተማሪም አስተማሪም መሆን ይችላል"* አለ።

(6) ኢየሱስ ከሚያገለግላቸው ሰዎች ጋር የነበረው ስድስተኛውና የመጨረሻው የቅርበት ደረጃ ከአንድ ሰው ጋር ብቻ የነበረው ግንኙነት ነው። ያም ኢየሱስ በጣም ያቀረበውና የወደደው ሰው ዮሐንስ ነበር። *"...ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር..."*(ዮሐ. 13፥23) ይላል። እርግጥ ነው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሁሉ ይወዳቸው ነበር፤ ቢሆንም ዮሐንስን የበለጠ ይወደው እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። ኢየሱስ ከላይ እንደገለጽነው ሰዎችን የሚቀርብበትና ወደ ራሱ የሚያቀርብበት የተለያየ ደረጃ ካለው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም በተለያየ ደረጃ የሚያቀርቧቸውና የሚቀርቧቸው ሰዎች ቢኖራቸው ሊደንቀን አይገባም። ይሁን እንጂ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን እውነት የተረዱት አይመስሉም።

ኢየሱስ መንፈሳዊ መሪ የሚሆኑትን ለተጠሩበት አገልግሎት ብቁ እንዲሆኑ ሲያዘጋጃቸው (ሲያስታጥቃቸው) የተጠቀመው ምን ዓይነት ዘዴ (ሞዴል) ነው?

## (ሀ) ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በመቀራረብ ራሱን አሳያቸው

በአሁኑ ጊዜ ያሉት መንፈሳዊ መሪዎች ቅዱሳንን ለአገልግሎት ለማዘጋጀት ኢየሱስ የተከተለውን ሞዴል እንዴት መጠቀም ይችላሉ? ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ያስታጠቃቸው የራሱን ሕይወት በማካፈል ነው። እርሱ ያሰለጠናቸው ደቀ መዛሙርቱ በተራቸው ሌሎችን አሰለጠኑ። የኢየሱስ ሞዴል ምን ዓይነት ነበር? ኢየሱስ ለአገልግሎት ከሚያስታጥቃቸው ደቀ መዛሙርቱ ጋር ለሦስት ዓመት የቆየ በጣም የተቀራረበ ግንኙነት ነበረው። ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ያሳልፍ ነበር። ማቴዎስ በወንጌሉ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት እንደነበረው ስድሳ ስድስት ጊዜ መዝግቧል። ዮሐንስ በባ ሦስት ጊዜ መዝግቧል።[32] ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምቾት በሌለበት ሁኔታ ብዙ ጊዜ አብሯቸው በእግሩ ተጉዟል። ኢየሱስ ሕይወቱ፣ ከእነርሱ ሕይወት ጋር የተያ

[32] Lynn Anderson.



ያዘ ስለ ነበር፣ በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ያስታጥቃቸው ነበር። ዛሬም መንፈሳዊ መሪዎች የክርስቶስን ሞዴል የሚከተሉ ከሆነ፣ ለአገልግሎት ከሚያስታጥቋቸው ጥቂት ሰዎች ጋር ሕይወታቸው የተያያዘ ወይም በጣም የተቀራረበ መሆን ያስፈልገዋል።

## (ለ) ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሞቃት የሆነ ግላዊ ፍቅር ነበረው

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የነበረው ቅርበትና ግንኙነት እንደ "አሠሪና ሠራተኛ" ወይም እንደ "ቀጣሪና ተቀጣሪ" ዓይነት የሆነ አልነበረም። በመካከላቸው የነበረው ቅርበት ወይም ግንኙነት ኢየሱስ እንደ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ (CEO)፣ ደቀ መዛሙርቱ ደግሞ ዝቅ ብለው እንደሚያገለግሉ ተራ ሠራተኞች አልነበሩም። ኢየሱስ *"ከእንግዲህ ወዲህ ባሪያዎች አልላችሁም፤...ነገር ግን ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ስለ ገለጽሁላችሁ ወዳጆች ብዬአችኋለሁ"* ይላቸዋል (ዮሐ. 15፥15)። ኢየሱስ አብሯቸው ተጓዘ፤ አብሯቸው በላ። ሌላው ቀርቶ እግራቸውንም ጎንበስ ብሎ አጠበ። በፍጹም ፍቅርም ወደዳቸው (ዮሐ. 13፥1)። ዋናው እረኛ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአገልግሎት ደቀ መዛሙርቱን በዚህ ዓይነት ያዘጋጃቸው (ያስታጠቃቸው) ከሆነ፣ የዘመኑ መንፈሳዊ መሪዎች ምዕመናኑን ለአገልግሎት የሚያዘጋጁት በምን ዓይነት መንገድ ይሆን? ግንኙነታቸው የተቀራረበና በፍቅር የተሞላ ነው? ወይስ ፕሮቶኮል የጠበቀ ነው። መሪው "ዋተቀባሁ... የተመረጥኩ ነኝና እንከባበር ነው የሚለው" ወይስ ሕይወቱን ከፍቶ በመስጠት...በፍቅር የተሞላ ግንኙነት በመካከላቸው ኖሮ ነው መንፈሳዊ መሪው እማኙን ለአገልግሎት የሚያዘጋጀው?

## (ሐ) ስሜቱን ሳይደብቅ፥ ልክ እንዳለ በመግለጽ ነበር

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚሰማውን እውነተኛውን ስሜቱን አይደብቃቸውም ነበር። በዮሐንስ ወንጌል 11፥35 ላይ "ኢየሱስ አለቀሰ" ይላል። ጥቅሱ በጣም አጭር ይሁን እንጂ፣ በውስጡ ትልቅ መልዕክት ይዟል። ኢየሱስን በዚያን ወቅት ያስለቀሰው ምን ነበር? ኢየሱስ ያለቀሰው የሚጠፉት ነፍሳት ግድ ብሎት ነው። እንዲሁ አልአዛር በሞተበት ወቅት ሴቶች ለአልአዛር የሚያፈሱትን ዕንባ አይቶ ስሜቱን ሳይደብቅ፣ በሕዝብ ፊት እንዳለቀሰ እናውቃለን። ኢየሱስ ስሜቱን የገለጸው በዕንባ ብቻ አይደለም። የሚያስቆጣ ነገር በገጠመውም ጊዜ ስሜቱን አሁንም ሳይደብቅ በኃይል እንደ ገለጸ እናስታውሳለን። የአባቱን ቤት መሸጫና መለወጫ ሲያደርጉት ዝም በማለት ፈንታ በጣም ተቆጣ። *"ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው"*(ሉቃ. 19፥46)። ኢየሱስ እንዲህ ሲቆጣና ስሜቱን ሲገልጽ ከዚህ በፊት አይተውት በለማያውቁ ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ወቅት ምን ተሰምቷቸው ይሆን?

ስሜትን መድረክ ላይ ገልጾ ማሳየት ትክክል መስሎ ለማይታያቸው በአሁኑ ዘመን ያሉ አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ይህ የክርስቶስ ሁኔታ ጥሩ ትምህርት ሊሆናቸው እንደሚችል አንጠራጠርም። መድረክ ላይ ሆነው ሲሰብኩ ካለቀሱ "ደካማ"፣ ከተቆጡ ደግሞ "ስሜቱን መቆጣጠር የማይችል" እንባላለን በማለት ስሜታቸውን ለመግለጽ የሚፈሩ አሉ። ማንኛውም መንፈሳዊ መሪ የሚሰማው አንድ ነገር ሆኖ ለሕዝቡ የሚያሳየው ግን ሌላ ከሆነ፣ ያ ሰው አስመሳይ እንጂ ወይም ያልሆነውን ለመምሰል የሚሞክር ሰው መሆኑ ግልጽ ነው። የእውነተኛውን የበጎች ዋና እረኛ የሆነውን ምሳሌነት (ሞዴል) መከተል የሚፈልግ መንፈሳዊ መሪ፣ እንደ ክርስቶስ በውስጡ የሚሰማውን ስሜቱን ይገልጻል። መንፈሳዊ መሪ ስሜቱን ልክ እንዳለ ሲገልጽ፣ ለአገልግሎት ለሚያዘጋጃቸው ሰዎች ምሳሌ በመሆን አስፈላጊውን ትምህርት መስጠቱ ይሆናል።

## (መ) በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሕይወቱን እንዲያዩ ዕድል ሰጣቸው

ኢየሱስ ለአገልግሎት ያዘጋጃቸው የነበሩትን ደቀ መዛሙርቱን፣ በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ውስጥ የግል ሕይወቱን ማየት እንዲችሉ ዕድል ሰጣቸው። በቤተ መቅደስ ውስጥ፣ በመንገድ ላይ፣ በተራራ ጫፍ ላይ፣ ሴቶች ውሃ በሚቀዱበት አካባቢ፣ በሠርግ ቤት ውስጥ፣ በአትክልት ሥፍራ፣ በፍርድ ቤት፣ የኢየሱስን የግል ሕይወት የማየት ዕድል ነበራቸው። ከደቀ መዛሙርቱ የሸሸገው አንድም ነገር አልነበረም። ዛሬ እኛስ ለወንጌል አገልግሎት ማሰታጠቅ (ማዘጋጀት) የምንችለው በምን ዓይነት ሁኔታ ይሆን? የመንፈሳዊ መሪዎቻቸውን የግል ሕይወት የማየትና ከዚያ የመማር ዕድል ይኖራቸው ይሆን? መድረክ ላይ ሆነው፣ ጥሩ ልብስ ለብሰው እንደ መልአክ በአማረ ቃል ሲሰብኩ (ሲያስተምሩ) ብቻ ነው? ወይስ በዓለም ውስጥ የሚኖሩትን ኑሮ የማየትና የመማር ዕድል አላቸው?

## (ሠ) "ሀቀኛ እቋም" (Integrity) ያለው መሆኑን የማየት ዕድል አገኙ

ኢየሱስ ለአገልግሎት ያዘጋጃቸው የነበሩት ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን "ሀቀኛ እቋም" ማየት ይችሉ ነበር። ኢየሱስ የሚያስተምረው ትምህርት፣ ከሚኖረው ኑሮ ጋር አብሮ የሚሄድ እንጂ የሚቃረን አልነበረም። በእቋሙ የተለዋዋጭነት ባሕሪ የሚታይበት መንፈሳዊ መሪ አልነበረም። የዕብራውያንን መጽሐፍ የጻፈው ሰው *"...እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤ ይሁን እንጂ ምንም ኃጢአት አልሠራም"* ይለዋል (ዕብ. 4፥15)። ጴጥሮስም ስለ ኢየሱስ ሲመሰክር፣ *"እርሱ ኃጢአት አላደረገም፤ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም። ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤ መከራ ሲደርስበት አልዛተም፤ ነገር ግን ለጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ"* ይለዋል (1 ጴጥ. 2፥22-23)። ሁሉም ለማስተላለፍ የሞከሩት መልዕክት ኢየሱስ የሰበከውን (ያስተማረውን) ይኖርበት እንደነበረ ነው። ዛሬ መንፈሳዊ መሪዎች እንደሚሰብኩት ይኖሩበታል ወይ? ኢየሱስ በተግባር ካሳየ በኋላ፣ ያን ለምን እንዳደረገ መግለጫ ይሰጥ ነበር። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ፣ ያደረገበትን ምክንያት ገለጸላቸው። *"...ያደረግሁላችሁን ታስተውሉታላችሁን? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ ትክክል ነው፤ እንደምትሉኝ እንዲሁ ነኝና። እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ ሳለሁ እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተም እንደዚሁ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል"* አላቸው (ዮሐ. 13፥12-14)። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በዚህ ዓይነት ትምህርት በምሳሌ ይሰጣቸው ነበር። ሕይወቱ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር አብሮ የሚሄድ በመሆኑ፣ ደቀ መዛሙርቱ በኢየሱስ ላይ ትልቅ እምነት ነበራቸው።



ዛሬስ መንፈሳዊ መሪዎች በአኗኗራቸው እምነት የሚጣልባቸው ናቸው? ወይስ "የማስተምረውን ተማሩ፣ የማደርገውን ግን አታድርጉ" የሚሉ ናቸው? ማንኛውም ሰው ከሚሰማው ነገር ይልቅ፣ በዓይኑ የሚያየውን ነገር ማመንና መቀበል ይቀለዋል። መንፈሳዊ መሪ ለአገልግሎት የሚያዘጋጃቸውን ምዕመናን በሚኖረው ኑሮ ጥሩ ምሳሌ መሆን ይገባዋል። አንድ ጸሐፊ፥

> *"ስብከትን ከመስማት ይልቅ ማየትን እመርጣለሁ፤ 'መንገዱ ያ ወይም ይኸ ነው' ብለው ምልክት ከሚሰጡኝ ይልቅ አብሮኝ የሚሄደውን ሰው እመርጣለሁ" ብሏል።*

እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች 'የሚሰብኩትን ለመኖር' በራሳቸው ብቃት እንደሌላቸው ያውቃሉ። ያልሆኑትን ሆኖ ለመታየት መሞከር፣ "የሐቀኝነት እቋም" ጉድለት እንዳለባቸው ያሳያል። በሕይወታቸው ያለባቸውን ትግል፣ ምን ያህል የእግዚአብሔር ጸጋ እንደሚያስፈልጋቸው የሚገልጹ መንፈሳዊ መሪዎች "ሐቀኛ እቋም" ያላቸው መሆናቸውን ያሳያል። "ሐቀኛ እቋም" ያላቸው መንፈሳዊ መሪዎች፣ ሥጋ ለባሽ ሰዎች መሆናቸውን፣ ከማንም የተሻሉ እንዳልሆኑ፣ የራሳቸው የሆነ ድካም እንዳለባቸው፣ የእግዚአብሔር ጸጋ በሕይወታቸው በጣም እንደሚያስፈልጋቸው ሳይሸሽጉ በግልጽ ይናገራሉ። ራሳቸውንም ለሌሎች ተጠያቂዎች ያደርጋሉ። በዚህ ዓይነት ለአገልግሎት ለሚያዘጋጁቸው ደቀ መዛሙሮቻቸው "በሐቀኛ እቋማቸው" ጥሩ ምሳሌ መሆን ይችላሉ።

## (ረ) ኢየሱስ ለአስቸጋሪዎችና ለመልካም ሰዎች የሚሰጠው ጊዜ ሚዛኑን የጠበቀ ነበር

ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ ያጋጠሙት ሰዎች ሁሉም መልካም የሚባሉ ሰዎች አይደሉም። አስቸጋሪ የሆኑ ሰዎችም ገጥመውታል። በአሁኑ ዘመን ያሉትም መንፈሳዊ መሪዎች ሁሉንም ዓይነት ሰዎች በአገልግሎታቸው ውስጥ ያጋጥሟቸዋል።

ብርቱዎችን ማሰልጠን፣ ደካማዎችን መደገፍ (መርዳት) ይገባቸዋል። ከሚሰማሟቸው፣ አገልግሎታቸውን ከሚቀበሉት ጋር መተባበር የበው ሁሉ ተፈጥሯዊ ፍላጎት እንደሆነ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ፣ አስቸጋሪ ናቸው የሚባሉትንም እንዳይገፉ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። አስቸጋሪ የሆኑትም ሰዎች የመሪዎቻቸው ፍቅርና በርህራሄ የተሞላ ልብ ያስፈልጋቸዋል። አስቸጋሪ የነበሩ ሰዎች ተለውጠው አንድ ቀን ፍሬያማ አገልጋ ዮች ሊሆኑ እንደሚችሉ መዘንጋት የለባቸውም። ይሁን እንጂ፣ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸ ውን አሟጠው ሊጨርሱባቸው ከሚችሉ አንዳንድ አስቸጋሪ ሰዎች ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው። ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ አስቸጋሪ በዎችን ሳይ ገፉ፣ ፍሬያማ የሆኑትን ደቀ መዛሙርቱን ሚዛኑን ያልለቀቀ ጊዜ በመስጠት ለአገልግ ሎት ያዘጋጅ ነበር።

ኢየሱስ የግል ሕይወቱን፣ ጊዜውን ሙሉ በሙሉ በማካፈል ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ያዘጋጃቸው ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ከኢየሱስ የተማሩትን መልሰው የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ያስተምሩ ነበር። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎችን ለአገልግሎት ማዘጋጀት ከኃላፊነታቸው አንደኛውና ትልቁ እንደሆነ በግልጽ እናያለን። የእግዚአብሔር ዕቅድ ይህን ይመስላል። የዘመኑ መንፈሳዊ መሪዎች ኢየሱስ የእርሱን ምሳሌነት እንዲከተሉ ይፈልጋል። ከእግዚአብሐር በአደራ የተቀበልነውን ኃላፊነት፣ ሌሎችን በማስታጠቅ ለወንጌል አደራ በናበቃ በእኛ ትከሻ ላይ ያለውን ኃላፊነት ማቃለላችን ብቻ ሳይሆን፣ የወንጌል መልዕክት ለሚቀጥለው ትውልድና በዓለም ዙሪያ እንዲሰፋ ማድረጋችን እንደሆነ ማወቅ አለብን። በተጨማሪ "የበጎቹ ዋና እረኛ የሆነውን ኢየሱስን ምሳሌነት እየተከተል ነው ወይ?" በማለት ራሳችንን መጠየቅና በጥንቃቄ መመርመር አለብን።

## ምዕራፍ ፲

# ግጭት አርጋቢነት

"በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን? ትመኛላችሁ ለእናንተ አይሆንም ትገድላላችሁ፣ በብርቱም ትፈልጋላችሁ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ፣ ትዋጉማላችሁ፣ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም…" (ያዕ. 4፥1-2)።

"በሰላም ተሳስራችሁ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።" (ኤፌ. 4፥3)

"የሚቻላችሁ ቢሆን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር በእናንተ በኩል የሚያስፈልገውን ሁሉ አድርጉ" (ሮሜ 12፥18)።

ሰው ተቀራርቦ ሲኖር፣ አንዳንድ ጊዜ በተለያየ ምክንያት በሀሳብ መስማማት አቅቶት መጋጨቱ የማይቀር ነው። በማያምኑት ሰዎች መካከል ብቻ ሳይሆን፣ አማኝ በሚባሉት ሰዎች መካከልም ግጭት ሊፈጠር ይችላል። ከቤተ ክርስቲያን ውጪ በሆነ ሕብረት ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ፣ በአማኞች መካከልም ግጭት ሊፈጠር ይችላል። ሰላም ይኖራል ተብሎ በሚታሰብበት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ግጭት ይኖራል? ካለስ የግጭቶቹ ምክንያቶች ምን ይሆን? አንዳንድ አስቸጋሪ